

ከገጠር እስከ ከተማ በኑሮ የተፈተነች ሕይወት

ገጽ 16



ለተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላኑ ዝግጅት ውጤታማነት

ገጽ 14

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር
DERBA CEMENT
በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
82ኛ ዓመት ቁጥር 196 መጋቢት 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# «በትግራይ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መቋቋሙ የሰላም ስምምነቱን ወደመሬት ስማውረድ የላቀ ፋይዳ አለው»

- አምባሳደር ተሾመ ቶጋ
የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ኮሚሽነር

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መቋቋሙ የሰላም ስምምነቱን በተጨባጭ ወደመሬት ለማውረድም ሆነ ብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽኑ በክልሉ የተሰጡትን ኃላፊነቶች በሚገባ ለመወጣት የላቀ ፋይዳ ያለው መሆኑን የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ አስታወቁ።

አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ ስምምነቱ ከተፈረመበት ከኅዳር ወር ጀምሮ የፌዴራል መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶችን አድርገዋል። ይሁንና ስምምነቱን በምዕሉነትና በተጨባጭ መሬት በማውረድ ረገድ ሕጋዊነት ያለው ጊዜያዊ አስተዳደር በክልሉ መቋቋሙ ወሳኝ ሚና አለው።

በተለይም ብሔራዊ ኮሚሽኑ የቀድሞ ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታትና ወደቀድሞ ሰላማዊ ሕይወታቸው እንዲመለሱ እያደረገ ያለውን ጥረት ውጤታማ እንዲሆን የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል ብለዋል።

«የነበረውን ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ማስቆም የተቻለው የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ በመሆኑ ነው፤ አሁን ደግሞ የጊዜያዊ አስተዳደሩ መመስረቱ ለክልሉ ሕዝብም ሆነ እኛ ለምንሠራው ሥራ መንግሥታዊ

«በትግራይ ጊዜያዊ የሽግግር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

## አገራቱ በቱሪዝም ዘርፍ በጋራ ለመሥራት መስማማታቸው የሁለትዮሽ ግንኙነታቸውን ያጠናክራል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ደቡብ አፍሪካ በቱሪዝም ዘርፍ በጋራ ለመሥራት መስማማታቸው ጠንካራ የእርስ በእርስ ግንኙነት ለመፍጠርና የቱሪዝም ገቢን ለማሳደግ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ተገለጸ።

የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር እና የደቡብ አፍሪካው

አገራቱ በቱሪዝም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## በሶማሌ ክልል በድርቅ ምክንያት ከ92 ሺህ በላይ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አቋርጠዋል

- 4 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዜጎች ለተረጂነት ተጋልጠዋል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተከሰተው ድርቅ ከ92 ሺህ በላይ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ማቋረጣቸውን የሶማሌ ክልል መንግሥት አስታወቀ። በአሁኑ ወቅት 4ነጥብ 2 ሚሊዮን ዜጎች ለተረጂነት መጋለጣቸውንና 250 ትምህርት ቤቶችም ወደ መዘጋት መቃረባቸውን ገልጸዋል።

የሶማሌ ክልል አደጋ ስጋት አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ ያሲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በክልሉ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት 435 ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል። በዚህም ምክንያት 92 ሺህ 639 ተማሪዎች ትምህርታቸዉን አቋርጠዋል። ሁኔታው በፍጥነት ካልተሻሻለ 250 ትምህርት ቤቶች ለመዘጋት መቃረባቸውንም ገልጸዋል።

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተከሰተው ረጅም ድርቅ በክልሉ በሚገኙ አስር ወረዳዎች ከፍተኛ የምግብና የመጠጥ ውሃ እጥረት ተከስቷል። ዳዋ ሊበን እና አፍዴራ ዞን የከፋ ችግር እንደተከሰተ ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በአሁኑ ሰዓት በክልሉ 4 ነጥብ 2

በሶማሌ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

## «በዓባይ ጉዳይ ጊዜ ያስፈበትን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ የመንዝ አካሄድ በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ አይደለም»

- ኢንጂነር ፈቂአሕመድ ነጋሽ
የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያ

ገጽ 4

AMG STEEL FACTORY
ኤ.ኤም.ጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
Our Products
GI-Coil Color Coil Tiles
Ega Sky Tiles Corrugated Sheet Curving Ridge Sky Ridge V-Gutter Accessories
Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80/ 0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

AfriSky PLC ETHIOPIA
Our Products
Billet RHS Wire Rod Re-bar CZU H-BEAM Nail Streel Structure Tanker
Akaki, Gelan
0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06



ዶክተር ተካልኝ አያሌው

# ኢትዮጵያ
## በኢጋድ አባል አገራት መካከል ነፃ የሠራተኞች እንቅስቃሴ እንዲኖር እየሠራች ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በኢጋድ አባል አገራት መካከል ነፃ የሠራተኞች እንቅስቃሴ እንዲኖር እየሠራች መሆኑን ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ግንኙነትና የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ተካልኝ አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢጋድ አባል አገራት መካከል ከፍተኛ የሠራተኛ እንቅስቃሴ አለ። ከአባል አገራቱ ብዙ ሥራ ፈላጊዎች በተለያየ መንገድ ከምሥራቅ አፍሪካ ወደ አረብ፣ አውሮፓና ደቡብ አፍሪካ አገራት ይፈልሳሉ።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ሌሎችን በማስተባበር በኢጋድ አባል አገራት መካከል ነፃ የሠራተኞች እንቅስቃሴ እንዲኖር እየሠራች ነው።

እንደ ዶክተር ተካልኝ ገለጻ፤ ነፃ የሠራተኞች ዝውውር እንዲኖር ኢትዮጵያም የራሷን ፖሊሲ እየከለሰች ነው፤ የፍልሰተኞችን አስተዳደር ፖሊሲን እያዘመነች ነው። የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።

በሌሎች አገራት የኢትዮጵያ ተሞክሮ በሞዴልነት እየተነሳ መሆኑን የገለጹት ሥራ አስፈፃሚው፤ ስለ አፍሪካ ውህደት ማውራት የሚቻለውም መጀመሪያ ነፃ የሠራተኞች ዝውውር ፕሮቶኮልን መፈረም ሲቻል ነው ብለዋል።

የአፍሪካ የፍልሰት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ አንዱ ኢጋድ ያወጣው የጅቡቲ ስምምነት ነው ያሉት ዶክተር ተካልኝ፤ በቀጣናው ነፃ የሠራተኛ እንቅስቃሴ እንዲኖርና ከአባል አገራት የሚነሱ ፍልሰተኞች በአባል አገራቱ ውስጥ ሠርተው በነፃ እንዲኖሩ፣ ሥራ እንዲይዙ፣ የትምህርት ደረጃቸው ዕውቅና እንዲያገኝ፣ እንዲሁም የፍልሰተኞችን መብት ለማስጠበቅና የፍልሰት አስተዳደርን ለማስተዳደር ትልቅ መሠረት የጣለ መነሻ ሰነድ መሆኑን ገልጸዋል።

የጅቡቲ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ኢትዮጵያ ዋና ተዋናይ ናት ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ነፃ የሠራተኛ ዝውውር ፕሮቶኮልን ብዙ አገሮች ለመፈረም ፈቃደኛ አይደሉም። ነፃ ዝውውር እንዲኖር ኢትዮጵያ በነፃ የሰዎች ዝውውር ላይ መድረኮችን በማዘጋጀት ውይይቶችን እያካሄደች ነው ብለዋል።

የጅቡቲ ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ ኢትዮጵያ በቀጣናው ያላትን ተሰሚነት ተጠቅማ ሌሎችን በማስተባበር ነፃ የሠራተኞች እንቅስቃሴ እንዲኖር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ነው። የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርም ይህን ሥራ ለመሥራት እንዲመች ተደርጎ የተዋቀረ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ተካልኝ ማብራሪያ፤ የሠራተኞችን መብት የምናስጠብቀው፣ የሕገወጥ ሰዎችን ዝውውር መቆጣጠር የሚቻለውና ድንበር አካባቢ ያለውን ችግር መፍታት የሚቻለው ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ነው።

በአጠቃላይም በኢጋድ አባል አገራት ያለውን ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አባል አገራቱ በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ ተደርሷል። የጅቡቲ ስምምነት በውስጡ ብዙ ሰነዶች ያሉትና በአፍሪካ ደረጃ ነፃ የሰዎች ዝውውር እንዲኖር ትልቅ መሠረት የሚጥል ስምምነት መሆኑን ገልጸዋል።

# ቢሮው ታዳሽ ኢነርጂን በማስፋፋት የኅብረተሰቡን ኑሮ ስመለወጥ እየሠራ ነው

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- ታዳሽ ኢነርጂን በማስፋፋት የገጠሩን ኅብረተሰብ ኑሮ ለመለወጥና ብቁ ዜጋን ለማፍራት እየሠራ መሆኑን የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ አሁን ላይ ያለው ሽፋን በአጠቃላይ አገራዊ የኤሌክትሪክና የኢነርጂ ሽፋን ከተቀመጠው አማካይ በታች እንደሆነ ተጠቅሷል።

የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የኢነርጂ ዘርፍ አስተባባሪ አቶ ጥላሁን ሽመልስ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ታዳሽ ኢነርጂን በማስፋፋት ብቁ ዜጋን ለማፍራት፤ ከተራቆተው የደን መጨፍጨፍ ለመውጣት፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከልና የተረጋጋና ለዜጎች ምቹ አካባቢን ለመፍጠር እንዲሁም የገጠሩን ኑሮ ለመለወጥ እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ጥላሁን ገለጻ፤ አብዛኛው የአማራ ክልል አካባቢዎች የምግብ ማብሰያ ቴክኖሎጂን አይጠቀሙም። ለዚህም የግንዛቤ ማነስ፣ ለዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት አለመስጠትና መሰል ምክንያቶች መንስኤዎች ናቸው።

በክልሉ በርካታ አካባቢዎች የደን መራቆት ያጋጠማቸውና ተራራማ ስፍራዎች የሚበዙባቸው እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ጥላሁን፤ የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ አጠቃቀም ችግር እና ለኢነርጂ የተሳሳተ አተያይም መኖሩንም ጠቁመዋል። በክልሉ አሁን ላይ ያለው ሽፋን በአጠቃላይ አገራዊ የኤሌክትሪክና የኢነርጂ ሽፋን ከተቀመጠው አማካይ በታች እንደሆነም ጠቅሰዋል።

አሁን እያጋጠመ ያለው የልማት መደናቀፍ ከኃይል አማራጭ ጋር በተያያዘ እንደሆነ የገለጹት አቶ ጥላሁን፤ የኃይል አማራጭን ከአካባቢ አየር ንብረት ብክለትና ከደን መጨፍጨፍ ነጥሎ ማየት ተገቢ እንዳልሆነም ጠቅሰዋል።

ለዘርፉ የበለጠ ትኩረት በመስጠት ብቁ ዜጋን ለማፍራት፤ ከተራቆተው የደን መጨፍጨፍ ለመውጣት፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከልና የተረጋጋና ለዜጎች ምቹ አካባቢን ለመፍጠር እንዲሁም የገጠሩን ኅብረተሰብ ኑሮ ለመለወጥ እየተሠራ እንዳለ ጠቁመዋል። በዚህም ክልሉ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ከፌዴራል እስከ ቀበሌ መዋቅር መዘርጋቱንም አስታውቀዋል።

አቶ ጥላሁን እንዳሉት፤ አንድ አገር እያደገ ሲመጣ ከፍተኛ የኢነርጂ ፍላጎቶች ይኖራሉ። ሆኖም ፍላጎቱ በመንግሥት ብቻ የሚመለስ ባለመሆኑ፣ በአጠቃላይ ቴክኖሎጂውንም ለማሳደግ የግል ባለሀብቶችና አጋር አካላትን ማሳተፍ ይገባል። የኃይል አማራጭ መጠቀም ቢቻል መደበኛ ኢንዱስትሪዎችም ሥራቸውን በአግባቡ የሚያከናውኑ ይሆናል።

እናቶች በታዳሽ ኃይል ባለመጠቀማቸው ዓይናቸው እየተጎዳና ለልብ ህመምና መሰል የጤና እክሎች እየተዳረጉ እንደሆነ አቶ ጥላሁን ጠቅሰው፤ ንጹህ የኃይል አቅርቦት ወሳኝ እንደመሆኑ በገጠር አካባቢ ያሉ እናቶችን ሕይወት ያገናዘበ ትኩረት ያስፈልጋል ብለዋል።

የኑሮ ጫና ለመቀነስና ከጤና ጋር ተያይዞ አማራጭ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች እንዲጠቀሙ እየተሠራ መሆኑንና ሶላር በመጠቀም በትምህርት ተወዳዳሪ የሆነ ትውልድ ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት በመከናወን ላይ እንዳሉም ጠቁመዋል።

# በክፍለ ከተማው ከተጀመሩት 26 ፕሮጀክቶች 18ቱ ተጠናቀዋል

**አመለወርቅ ከበደ**



ኢንጂነር ያህያ ዑመር

አዲስ አበባ፡- በክፍለ ከተማው ከታቀዱት 26 ፕሮጀክቶች 18ቱ መጠናቀቃቸውን የአራዳ ክፍለ ከተማ አስታወቀ።

በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የዲዛይን እና ግንባታ ሥራዎች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ኢንጂነር ያህያ ዑመር፤ ለኢትዮጵያን ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክፍለ ከተማው «አራዳን ድጋሚ» በሚል ሀሳብ ከተጀመሩ 26 ፕሮጀክቶች 18 ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል።

በአጠቃላይ ከተጀመሩት 26 ፕሮጀክቶች 18ቱ መቶ በመቶ የተናቀቁ ሲሆን፣ ስድስት ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ30 እስከ 50 በመቶ መድረሱንና የተቀሩትን ሁለት ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ለማስገባት ባለሀብቶቹ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

በክፍለ ከተማው የዘጠና ቀናት ፕሮጀክቶች እቅድ ተይዞ ወደሥራ ሲገባ ሦስት አላማዎች ተይዘው ነው ያሉት ኃላፊው፤ በክፍለ ከተማው የአገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ቀልጣፋ ማድረግ፤ ከዚህ በፊት ተጀምረው የነበሩ ነባር ፕሮጀክቶችን ፍጥነት መጨመር እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በባለሀብቶችና በመንግሥት አስጀምሮ ማጠናቀቅ እንደሆነ አስረድተዋል።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ ከዚህ በፊት በባለሀብቶች የተጀመሩ አራት ፕሮጀክቶች ሁለቱ የሸገር ዳቦ እና አትክልት መሸጫ ሱቆች ሲሆኑ፤ ሁለቱ የ70 እና 100 ደረጃ ፕሮጀክቶች ናቸው። ሁለቱ ደረጃዎች በቅርስነት የተመዘገቡ ሲሆን፤ አሁን ላይ ቆሻሻ እየተደፋባቸው የነበረው ውበታቸው ጠፍቷል።

በመሆኑም እነዚህ ደረጃዎች የነበራቸውን ይዘት ሳይለቁ እድሳት ለማድረግ ታስቦ እየተሠራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በተጨማሪም ሰዎች ተዝናንተው የሚሄዱባቸው ቦታዎች ለማድረግ ወንበሮችና መብራቶች ገብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

ከነባር አራት ፕሮጀክቶች በተጨማሪ 22 አዳዲስ ፕሮጀክቶች በኅዳር ወር ላይ በዘጠና ቀናት ለማጠናቀቅ ታቅዶ ተጀምረዋል ያሉት ኃላፊው ከነዚህም ውስጥ 10ሩ በመንግሥት፤ 12ቱ ደግሞ በባለሀብቶች የሚሠሩ ናቸው ብለዋል።

በመንግሥት የተጀመሩት 10 ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ሲሆን፤ በባለሀብቶች ድጋፍ ወደ ሥራ የገቡት ፕሮጀክቶችም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

የአቅመ ደካሞችን ቤት ለማደስ ታስቦ በሁለት ባለሀብቶች ባለ አምስት ወለል እና ባለ ሦስት ወለል ሕንፃዎች የተጀመሩ ሲሆን፣ የሥራ አፈጻጸማቸው 30 በመቶ ደርሷል። ከነዚህ በተጨማሪ በየወረዳዎቹ አምስት የፖሊስ ማዕከላትን ለመሥራት ከተጀመሩት ፕሮጀክቶች ሦስቱ ተጠናቀዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ኢንጂነር ያህያ እንደገለጹት፣ እስካሁን ወደ ሥራ የገቡት ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ወጪ 280 ሚሊዮን ብር ሲሆን፤ የተጠናቀቁት 18 ፕሮጀክቶች ወጪ 99 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ነው ብለዋል።

በሥራ ሂደቱ የሲሚንቶ እጥረት እና አንድ አንድ ባለሀብቶች ቃል በገቡት መሠረት ፈጥነው ወደሥራ መግባት አለመቻላው ተግዳሮት እንደነበረም ተናግረዋል።

በቀጣይ የተጀመሩን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ በተለይ ባለ ሦስት እና ባለ አምስት ወለል ሕንፃዎችን በማጠናቀቅ በሌሎች ወረዳዎች ላይም ባለሀብቶችን በማሳተፍ ደሃውን ማህበረሰብ ሊረዱ በሚችሉ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርገን እንሠራለን ሲሉ ተናግረዋል።

ዜና



አቶ ወንዳጥር መኮንን

# በጦርነቱ አገልግሎት ከተቋረጠባቸው ዜጎች 3 ነጥብ 3 ሚሊዮኑ ዳግም ውሃ አገኙ

## - 4ነጥብ 8 ሚሊዮን ዜጎች አሁንም የውሃ አገልግሎት ይሻሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት የተቋረጠውን የውሃ አገልግሎት መልሶ በመጠገን በተሠራው ሥራ ሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ። አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዜጎች አሁንም አገልግሎት እንደሚሹ ጠቁሟል።

የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ወንዳጥር መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የውሃ አገልግሎት የተቋረጠባቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ገንዘብ በማሰባሰብ የመጠገን ሥራ በትኩረት እየተከናወነ ይገኛል።

በአገሪቱ ተከስቶ በነበረው የሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ቀድመው ውሃ ያገኙ የነበሩ ስምንት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዜጎች የውሃ አገልግሎት የተቋረጠባቸው ሲሆን፤ ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በተደረገው የውሃ ተቋማት ጥገና ሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።

በ1ሺህ 429 የውሃ ተቋማት ላይ ውድመት መድረሱን ያስታወሱት አቶ ወንዳጥር፤ እስካሁን በተከናወነው የጥገና ሥራ ከ400 በላይ የውሃ ተቋማት አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። ጥገናው የተከናወነው ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች በተገኘ ከ900 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ መሆኑን አብራርተዋል።

ጥገና የተደረገላቸው ተቋማት ከባድ፣ መካከለኛ እና ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆኑ፤ 70 የውሃ ተቋማት ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው ብለዋል።

የወደሙት ቁሳቁሶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን የሚጠይቁና ጥገናውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ከመሆናቸው የተነሳ አገልግሎት የተቋረጠባቸውን ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ እንዳልተቻለ ገልጸዋል።

ክልሉ የተቋረጠውን የውሃ አገልግሎት ለማስጀመር እና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። እንዲሁም አገልግሎት የተቋረጠባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ክልሉ የደረሰበትን ችግር ተረድተው በትእግስት እየጠበቁ በመሆናቸው ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል።

የውሃ አገልግሎት የተቋረጠባቸውን አራት ነጥብ ስምንት ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ከመንግሥት ጀምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ማድረግ አለባቸው ብለዋል።

በክልሉ የውሃ ተቋማት ላይ የደረሰው ውድመት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገቡ እና በፍጥነት ሊተኩ የማይችሉ ቁሳቁሶች ላይ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወደ ገንዘብ ሲቀየር ሁለት ነጥብ 64 ቢሊዮን ብር መሆኑን ገልጸዋል።

የውሃ ተቋማት እንደሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጊዜ የሚሰጠው ባለመሆኑ መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ኅብረተሰቡ ርብርብ በማድረግ ሁሉንም ዜጎች የውሃ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ተማሪዎች የረመዳን ፆምን በምሳ ሰዓታቸው ሰግደው መመለስ የሚችሉበት አሠራር ይዘጋጃል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ የረመዳን ፆም ተማሪዎች በምሳ ሰዓታቸው ሰግደው መመለስ የሚችሉበት አሠራር እንደሚዘረጋ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። በከተማ አስተዳደሩ ሥር የሚገኙ 469 ትምህርት ቤቶች ተመዝነው የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ዕውቅና እና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ ከትናንት በስቲያ በሥራ አፈፃፀም ምዘና የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ትምህርት ቤቶች ዕውቅናና ሽልማት ሲሰጡ እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ተማሪዎች የረመዳን ፆምን በምሳ ሰዓታቸው ሰግደው መመለስ የሚችሉበት አሠራር ያዘጋጃል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በባለፈው ዓመት ረመዳን ፆም ከተማሪዎች መስገድ ጋር የተነሱ ቅሬታዎችን መፍታት ችሏል ያሉት ኃላፊው፤ በዘንድሮ ዓመት የረመዳን ፆም ተመሳሳይ ችግር እንዳያጋጥም ተማሪዎች በምሳ ሰዓታቸው ሰግደው መመለስ የሚችሉበት አሠራርን መምህራንና የትምህርት ቢሮ ጽሕፈት ቤቶች እንዲዘረጉና ተማሪዎቹን እንዲደግፉ አሳስበዋል።

በዘንድሮ ዓመት የአገሪቷን የትምህርት ስብራት ለመጠገን አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት ዶክተር ዘላለም፤ ጠንክሮና ታትሮ የሚሠራ አካልም ሆነ ትምህርት ቤት ዕውቅናና ሽልማት ሊሰጠው ይገባል። ለዚህም በ2015 የትምህርት ዘመን በመጀመሪያ ስድስት ወራት በሥራ አፈፃፀም ምዘና የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ዕውቅናና ሽልማት ሰጥተናል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ በበኩላቸው፤ ምዘናው የቢ ኤስ ሲ እቅድ አፈጻጸምን መሠረት አድርጎ መካሄዱን ጠቁመው፤ ምዘናውም በዋናነት በተቋማቱ መካከል የውድድር መንፈስ በመፍጠር ተቀራራቢ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ታስቦ የሚካሄድ ነው ብለዋል።

በምዘናው ከ470 በላይ ተቋማት መገምገማቸውንና ለምዘናው ከ500 በላይ ባለሙያዎች መሳተፋቸውን የጠቀሱት ኃላፊው፤ ይህም በትምህርት ቤቶች መካከል ውድድር እንዲኖር ከማድረግ ባለፈ የተሻለ የትምህርት ጥራት እንዲኖር እና በምዘና ሥርዓት ትምህርት ቢሮ ልምድ እንዲኖረው ያደርገዋል ብለዋል።

የ2015 ዓመተ ምህረት የስድስት ወር የቢ ኤስ ሲ አፈጻጸም ምዘና ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን የምዘና መስፈርት ከማዘጋጀት ጀምሮ ለመዛኞች ኦረንቴሽን ተሰጥቶ ወደ ምዘና መግባቱን የገለጹት ደግሞ የትምህርት ቢሮ የእቅድና በጀት ክትትል ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጌታሁን ለማ ናቸው።

ከቢሮ እስከ ትምህርት ቤት በተካሄደው ምዘና 469 ተቋማት በ590 መዛኞች ተመዝነው ለዕለቱ የዕውቅና መርሀ ግብር መብቃታቸውን አስታውቀዋል።

በምዘናው ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አጼ ቴዎድሮስ ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ረጺ ከኮልፌ ክፍለ ከተማ እንዲሁም ልቤፋና ትምህርት ቤት ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ በተከታታይ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ በመሆን ዕውቅና እና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሥራ አፈፃፀም እና በ12ኛ ክፍል ውጤት ደግሞ አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት 1ኛ፤ በሻሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 2ኛ እንዲሁም ቦሌ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3ኛ በመውጣት ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል። በላቀ የሥራ አፈፃፀም ደግሞ 1ኛ በላይ ዘለቀ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ 2ኛ በሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም 3ኛ ቤተልሔም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሆን ተሸልመዋል።

# ባለሥልጣኑ ከተለያዩ አገራት የተመለሱ ቅርሶችን ማስጎብኘት ጀመረ

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን በሕገወጥ መንገድ ከአገር የወጡና በተለያዩ ጊዜያት የተመለሱ ቅርሶችን ማስጎብኘት ጀመረ።

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የብሔራዊ ሙዚየም ዳይሬክተር አቶ ደምረው ዳኜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለፁት፤ በአውደ ርዕዩ የሚጎበኙት ከ150 ዓመታት በፊት ከመቅደላ ተዘርፈው የተመለሱ ታሪካዊ ቅርሶችን ጨምሮ ከእንግሊዝ፣ ከዴንማርክ፣ ከአሜሪካ እና ከኔዘርላንድ የተመለሱ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ በባለሥልጣኑ ጊዜያዊ አውደ ርዕይ 20 ያህሉ ለዕይታ ይቀርባሉ።

ከኮቪድ ወረርሽኝ ወዲህ የካቲት አጋማሽ 2015 ጀምሮ በሐረር ከተማ ተንቀሳቃሽ አውደ ርዕይ መካሄዱን አስታውሰው፤ በቀጣይም በተለያዩ ክልሎች ተንቀሳቃሽ አውደ ርዕይ የሚካሄድ መሆኑን አመላክተዋል። በቀጣይም በፈረንሳይ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ለማስመለስ በሂደት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የቅርስ ምዝገባና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደሳለኝ አበባው በበኩላቸው፣ ሕገወጥ የቅርስ ዝውውር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአደንዛዥ እፅ እና ከጦር መሣሪያ ቀጥሎ ዓለምን እየፈተነ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በቅርስ ላይ የሚደረጉ መሰል ተግባራት በዩኔስኮ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ እንደተፈጸሙ ወንጀሎች የሚወሰዱ ናቸው ብለዋል።

በአገራችን ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች የእምነት ተቋማትን የመዝረፍ፣ የማውደም ወዘተ ድርጊቶች መፈጸማቸውን አስታውሰው፤ ቅርሶች በጦርነት ወቅት መጠበቅ እንዳለባቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች የሚደነግጉ መሆኑን አንስተዋል። ሆኖም ሕገወጥ የቅርስ ዝውውሮች በጦርነት ወቅት በስፋት ይስተዋላሉ ብለዋል።

ኢትዮጵያ በተለይ በአፄ ቴዎድሮስ ወቅት ከእንግሊዝ ጋር በነበረው የመቅደላ ጦርነት በርካታ ቅርሶች በሕገወጥ መንገድ ከአገር ወጥተዋል ያሉት አቶ ደሳለኝ፤ በተመሳሳይ በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ትልቁ የአክሱም ሐውልትን ጨምሮ በርካታ ቅርሶች ተወስደው እንደነበር ጠቁመዋል። እንዲሁም በዲፕሎማቶች፣ በአሳሾች እና በተለያዩ ግለሰቦች በተለያየ መንገድ ታሪካዊ ቅርሶች ከአገር የወጡ መሆኑን አስታውሰዋል።

አቶ ደሳለኝ እንደገለጹት፤ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሕገወጥ የቅርስ ዝወውር እንዳይፈፀም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዋናነት ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር እየሠራ ነው። ከፖሊስ አካላት፣ ከኢንተርፖልና ብሔራዊ መረጃና ደህንነት ከመሳሰሉት ሕግ አስከባሪ ተቋማት ጋር ሕገወጥ የቅርስ ቁጥጥር እና መከላከል ላይ ግንዛቤዎች ከመስጠት ጀምሮ የመግባቢያ ስምምነቶች የተፈራረመ መሆኑንም ገልጸዋል።

ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ጋር የየብስ ኬላዎች፣ በብሔራዊ አየር መንገዶች በሕገወጥ መንገድ በሚወጡ ቅርሶች ላይ ግንዛቤ መሰጠቱንና እየተቆጣጠሩ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ቅርስ ከማስመለስ ጋር በተያያዘ ከሦስት ዓመት በፊት የተቋቋመው ብሔራዊ ቅርስ አስመላሽ ኮሚቴ፣ በመንግሥት ደረጃ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ጭምር በመረባረብ በሕገወጥ መንገድ የወጡ ቅርሶች ወደ አገር እየተመለሱ ይገኛሉም ብለዋል።

ከአንድ ዓመት በፊት ከእንግሊዝ አገር 19 ቅርሶች በአንድ ጊዜ የተመለሱ መሆኑን አስታውሰው፤ በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያን በሚወዱ የውጭ ማህበረሰብ ቅርሶቹ ጨረታ ላይ ሲቀርቡ እየገዙ እና በማግባባት ጭምር እየተመለሱ ነው ብለዋል።

የተዘረፉ ቅርሶችን በየቤቱ ያስቀመጠ ሊኖር ስለሚችል ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ሙዚየሙ እንዲመለሱ የማድረግ ሥራ ይሠራል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በቅርቡም በደሴ የወደሙ ቅርሶችን የመመለስ እና መልሶ የማቋቋም ሥራዎች መጀመራቸውን ጠቁመዋል።

በጊዜያዊ ዓውደ ርዕዩ የቀረቡት ቅርሶች ከመጋቢት 15 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ 10 ቀናት ለጉብኝት ክፍት ይሆናሉ።

# «በዓባይ ጉዳይ ጊዜ ያስፈበትን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ የመጓዝ አካሄድ በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ አይደለም»

*- ኢንጂነር ፈቂአሕመድ ነጋሽ*
*የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያ*

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በዓባይ ጉዳይ የተረሳውን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ የመጓዝ አካሄድ በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ ካለመሆኑም በላይ ግብጽ በተፋሰሱ ውስጥ የምትከተለው ፖሊሲ የተፋሰሱ አገራትን በተለይም ውሃ አመንጪዎችን ያገለለ አቅጣጫ ነው ሲሉ የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያ አቶ ፈቂአሕመድ ነጋሽ አስታወቁ።

አቶ ፈቂአሕመድ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ ግብጽ በተፋሰሱ የምትከተለው ፖሊሲ ራሷን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግና ሌሎችንም የተፋሰሱ አገራት በተለይ ውሃ አመንጪዎችን ያገለለ ነው።

ከእነዚህ አግላይ ከሆኑ አቅጣጫዎች ውስጥ የመጀመሪያው ሌሎቹን ያላካተተ ስምምነት ማካሄድ ነው። እኤአ በ1929 እና በ1959 የተፈረሙት ስምምነቶች የቅኝ ግዛትና የድህረ ቅኝ ግዛት ስምምነቶች ናቸው። ዛሬም የቅኝ ግዛት በጠፋበት ዘመን ግብጾች በዚህ ስምምነት ላይ ለመንጠልጠል ይሞክራሉ። ራሳቸው መንጠልጠል ብቻ ሳይሆን ስምምነቱን በሌሎችም ላይ ለመጫን ሙከራ ያደርጋሉ፤ ይህ ደግሞ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተረሳውን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ የመጓዝ አካሄድ ግን በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ አይደለም ብለዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ግብጾች የሚፈልጉት የላይኛው ተፋሰስ አገራት በተለይም ኢትዮጵያ በጣም ድሃ፣ ደካማ እና ተጋላጭ ሆና እንድትቀጥል ነው። ለዚህም በርካታ የራሳቸው ስልቶች አሏቸው። እንዲያም ቢሆን በተለይ ዓለም እንደ አንድ መንደር በሆነበት ብሎም በሳይንስና በቴክኖሎጂ በረቀቀበት ዘመን እንዲህ ዓይነት ኋላቀር አስተሳሰብ ይዞ አንድን አገር ለመጉዳትና ለማፍረስ የሚደረጉ ጥረቶች በምንም መልኩ ተቀባይነት የላቸውም።

በተፋሰሱ ውስጥ ያለ የውሃ ሀብት የተፋሰሱ አገራት የጋራ ሀብት ነው ያሉት አቶ ፈቂአሕመድ፤ ሁሉም አገር ባለው ሀብት ላይ ሉዓላዊ መብት አለው፤ ውሃን በተመለከተ ግን ይህ ሉዓላዊ መብት ውስን እንደሚሆን ተናግረዋል። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የላይኛው ተፋሰስ አገር ናት። ውሃው የሚነሳው በአብዛኛው ከኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ውሃ አጠቃቀም ላይ ሉዓላዊ መብት አላት። ይህ ሉዓላዊ መብት ግን ውስንነት አለው ብለዋል።

አቶ ፈቂአሕመድ፣ ለዚህ በምክንያትነት ያስቀመጡት ውሃውን ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ልጠቀም ካለች ለበርካታ ሚሊዮን ዓመታት ወደታችኛው ተፋሰስ አገራት እየሄደ ስለሆነ በዚያ ውሃ ላይ ሕይወት ተመስርቷልና የራሱ የሆነ ችግር አለው። ሲሄድ በነበረው ውሃ እድገቱም ሥልጣኔውም ስለተመሠረተ ኢትዮጵያ ያንን ሳታጠፋ የምትጠቀምበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት አስረድተዋል። ግብጾቹም ቢሆኑ ማሰብ ያለባቸው በዚያ መልኩ መሆን አለበት ብለዋል።

አቶ ፈቂአሕመድ እንደተናገሩት፤ ውሃው የሚሄደው ከኢትዮጵያ ነው፤ እዚህም ሕይወት አለ፤ ልማትና እድገትም አለ። ተስፋና ፍላጎትም እንዲሁ አለ። በዚህ መልኩ መተሳሰብ ካለ አብሮ መጠቀም ይቻላል። እኛ ብቻ እንጠቀም የሚባል ከሆነ ግን ተጎጂ የሚሆኑት እነርሱ ናቸው። ምክንያቱም ውሃው የሚሄደው ከዚህ ነው። የላይኛው ተፋሰስ አገራት ለታችኛዎቹ ተፋሰስ አገራት ያስባሉ፤ ይጨነቃሉም። ሁሌም የታችኛዎቹ ተፋሰስ አገራት የላይኛዎቹ ተፋሰስ አገራት ትንሽ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የሚያዩት በፍራቻና በጥርጣሬ እንዲሁም በተቃርኖ ነው። ስለዚህ ይህ ዓይነቱ አተያይ የሚቀረፍበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት ብለዋል።

በ21ኛ ክፍለ ዘመን ይህ አስተሳሰብ ኋላቀር በመሆኑ ሊቀር የሚገባው ነው ያሉት አቶ ፈቂአሕመድ፤ ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በፍጹም የማያዋጣ መንገድ ስለሆነ በተቻለ መጠን ያንን በመተው ወደትብብር የሚመጣበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቃል ሲሉም ገልጸዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በናይል ውስጥ በትብብርም ሆነ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ በመፍጠሩ ላይ ከላይኛው ተፋሰስ አገራት ጋር ሆና በጣም በርካታ ሥራ ሠርታለች። እስካሁንም እየሠራች ነው። በተለይ የትብብር ሥራውም ሆነ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፉ ዓለምአቀፍ ሕግ ሆኖ በሕግና በሥርዓት እንዲመራ የተለያየ ተግባር ተፈጽሟል። እንክብካቤውም፣ ልማቱም፣ ጥበቃውም ሁሉም ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ እንዲመራ የሚያደርጉ ስለሆኑ ብዙ ሥራዎች በተፋሰሱ አገራት ተሠርተዋል። ብዙዎቹም ይህንን ስምምነት ተቀብለውታል። ከ11ዱ ውስጥ ወደስድስት አገራትም ፈርመውታል። አራቱ ደግሞ አጽድቀውታል። ሦስት አገራት ደግሞ የማጽደቅ ሒደት ላይ ይገኛሉ። ምንም እንኳ የዘገየ ቢመስልም ጥሩ አቅጣጫ ላይ ይገኛል ብለዋል።

# «በትግራይ ጊዜያዊ የሽግግር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አገልግሎቶችን ለመስጠት አቅም ከመሆን አኳያ ትልቅ ፋይዳ አለው» ብለዋል።

«መከላከያ የአገር ድንበርን፣ ፖሊስም ጸጥታን ሊያስከብር ይችላል፤ ይሁንና ክልሉንም ሆነ ሕዝቡ ወደ ቀድሞ ሰላማዊ ሁኔታ የመመለሱ ሂደት መንግሥታዊ ሥራን የሚጠይቅ ነው» ያሉት አምባሳደር ተሾመ፤ በተለይም በጦርነት የተጎዳውን አካባቢ ዳግም ለመገንባት ለሚደረገው ብሔራዊ ጥረት የሽግግር መንግሥቱ መመስረት ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖረው አስገንዝበዋል።

በጦርነቱ የተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም፤ አርሶአደሩን ወደ እርሻ ሥራው ለመመለስና መሠረታዊ የጤና እና ሌሎችንም አገልግሎቶችን ለመስጠት የፌዴራል ተቋማት ብቻቸውን ውጤታማ መሆን እንደማይችሉ አምባሳደር ተሾመ ተናግረው፤ በመሆኑም ጊዜያዊ አስተዳደር መቋቋሙን ተከትሎ የክልል ቢሮዎች ከፌዴራል ተቋማት ጋር ተቀናጅተው እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን አመልክተዋል።

እንደአምባሳደር ተሾመ ማብራሪያ፤ የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተከትሎ ከዚህ ቀደም የቀድሞ ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታት ሂደት የተከናወነ ቢሆንም ሥራው በብሔራዊ ደረጃ መከናወን እንዳለበትና ይህንን የሚመራ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ታምኖበት ኮሚሽኑ እንዲቋቋም ተወስኖ ወደ ሥራ ተገብቷል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላም ሦስተኛው ትጥቅ የማስፈታት ሂደት የተከናወነ ሲሆን ትግራይ ድረስ በመሄድ የቀድሞ ታጣቂዎችንም ሆነ ኅብረተሰቡን በቅርበት በማወያየት አበረታች ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል።

ታዋጊዎቹን ትጥቅ ከማስፈታት ባሻገር የክልሉም ሆነ የአገሪቱ የሰላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲ አካል እንዲሆኑ መልሶ የማደራጀትና የመደገፍ ሥራ በስፋት ማከናወን ይጠይቃል ያሉት አምባሳደር ተሾመ፤ ለዚህ ደግሞ የጊዜያዊ አስተዳደሩ መቋቋም ኮሚሽኑ በቀጣይ ለያዘው ግቦች መሳካት ሁነኛ አጋዥ ኃይል እንደሚሆን ይታመናል ሲሉ ጠቅሰዋል።

የሰላም ስምምነቱ በአግባቡ እንዲተገበር ከማድረግ አኳያም በተለይ የፖለቲካ ችግርና የተፈለገው ገንዘብ ያለማግኘት ችግር ሊያጋጥም ይችላል የሚሉ ስጋቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ኮሚሽነሩ ጠቅሰው፤ «አሁን ባለው ሁኔታ ከዚህ ውጪ ግን በክልሉ ተንቀሳቅሰን ለመሥራት የሚያዳግተን ነገር የለም ብለዋል።

በተለይ የሰላሙ በተጨባጭ መምጣት ኅብረተሰቡ፣ የቀድሞ ተዋጊዎች፣ ጊዜያዊ አስተዳደሩም ሆነ የፌዴራል መንግሥቱ የሚፈልገው ጉዳይ በመሆኑ ትግራይን መልሶ ለመገንባትና ከፀጥታ ስጋት ለማውጣት አዳጋች ይሆናል ብለው እንደማያምኑ ተናግረዋል። ለመልሶ ግንባታ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በማፈላለጉ ሂደትም የመፍትሔ አማራጮች ታሳቢ መደረጋቸውን አምባሳደር ተሾመ ጠቁመዋል።

# በሶማሌ ክልል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሚሊዮን ዜጎች ለተረጂነት ተጋልጠዋል። ከእነዚህም ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በዓለም አቀፍ ምግብ ፕሮግራም የምግብ ድጋፍ እየተደረገላቸው ሲሆን አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በመኖና በመጠጥ ውሃ እጥረትም እስካሁን ሁለት ሚሊዮን እንስሳት ሞተዋል፣ በሕይወት የተረፉም በአካላቸው የተጎዱና ምርትና ምርታማነታቸው የተዳከሙ ናቸው።

ክልሉ ችግሩን ለመቅረፍ የአጭር እና ረጅም ጊዜ እቅድ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የክልሉ መንግሥት፣ አጋር አካላት፣ ከፌዴራል መንግሥት እና ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በገንዘብና በዓይነት በአጠቃላይ 300 ሚሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ ለኅብረተሰቡ መደረጉን ገልጸዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው። ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ በስፋት ለአርሶ አደሩ በማቅረብ በመስኖ ሥራ ላይ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ሲሉም ኃላፊው ገልጸዋል።

ድርቁ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በክልሉ ትልቁ ችግር የውሃ ነው ያሉት ኃላፊው፣ ችግሩን ለመፍታት 200 የውሃ ማመላለሻ ቦቴዎች አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል ብለዋል። የበልግ ዝናብን ተከትሎ 11 ዞኖች ዝናብ ማግኘታቸውን ገልጸው ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ውሃን መቋጠር የሚችሉ ትላልቅ የውሃ ጉድጓዶች እና አነስተኛ ግድቦች እየተሠሩ ነው። ለመስኖ እርሻ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠርም ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

በቴክኖሎጂ በመታገዝ ሰፊ እንስሳት እርባታ ሥራዎችን በማስፋፋት ለአርሶ አደሩ የገበያ ትስስር በመፍጠር ትላልቅ ኢንቨስትመንቶችን ተግባራዊ ማድረግ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ድርቅን በዘላቂነት ለመከላከል የአየር ንብረት ለውጥ ላይ መሥራት ዋነኛው መፍትሄ ነው ያሉት አቶ አህመድ፣ አሁን የተከሰተውን ችግር ለመፍታት ሁሉም አካላት በተለመደው መሠረት ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# አገራቱ በቱሪዝም...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የቱሪዝም ተቋም በቱሪዝም ዘርፍ በጋራ መሥራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ መጋቢት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ስምምነት አድርገዋል።

በስምምነቱ ወቅት የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ እንደገለጹት፤ በቱሪዝም ዘርፉ የተደረገው ስምምነት ቱሪዝምን ከማሳደግ ጎን ለጎን ግንኙነቱን በኢኮኖሚው እንዲጠናከር ያግዛል።

ስምምነቱ በተለይ የገበያ ዕድልን ከመፍጠርና የሁለቱ አገራት የቱሪስት መዳረሻዎችን በማስተዋወቅ እንዲሁም በጋራ ክህሎት በማሳደግ የአገልግሎት አሰጣጡን በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

አምባሳደሯ አክለውም፣ ደቡብ አፍሪካ በቱሪዝም ዘርፉ የብዙ ጊዜ ልምድ ያላት አገር በመሆኗ በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት በዘርፉ የተለያዩ ችሎታዎችን ከማሳደግ አንጻር በጋራ መሥራታችን ተጠቃሚ ያደርገናል።

የተደረሰውን ስምምነት አፈጻጸም የሚከታተል ቴክኒካል ቡድን ተቋቁሟል ያሉት ሚኒስትሯ፤ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በዘርፉ ዝርዝር የሆኑ ተግባራትን በመለየት ወደ ሥራ እንገባለን ብለዋል።

የደቡብ አፍሪካው ቱሪዝም ተቋም ኃላፊ ሚስተር ቪክቶር ታሬጅ በበኩላቸው በጋራ ለመሥራት የተደረሰው ስምምነት ለአገራቱ የቱሪዝም ዕድገት ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል።


ስምምነቱ የባህልና የልምድ ልውውጥ ለማሳደግ እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ እንዲዳብር የሚያግዝ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ስምምነቱ ለሁለቱ አገራት በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ የሆነ የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያግዛል ብለዋል።

እንደ ሚስተር ቪክቶር ገለጻ፤ ስምምነቱ የጋራ ክህሎት ለማሳደግ፣ በጋራ በመሥራት ባህላዊ ቅርሶችን እንዲጠበቁ ከማድረግም በላይ የገበያ ዕድልን ለመፍጠርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘርፉን እውቅና ከፍ ለማድረግ ይረዳል።

ኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች ጠብቆ ከማቆየት አኳያ ብዙ ልምድ ያካበተች አገር በመሆኗ ብዙ ልምድ እንድናገኝ እንዲሁም የቱሪዝም ሥራዎች ላይ የጋራ ልምድ እንዲኖረን የሚረዳ ስምምነት በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ስምምነቱም ከትምህርትና ስልጠና፣ ከቱሪዝም ኢንቨስትመንት፣ ቱሪዝምን ከማስተዋወቅ አኳያ፣ የቱሪዝም ገበያን ከመፍጠር፣ ክህሎትን ከማሳደግና ስልጠናዎችን ከመስጠት አኳያ እንዲሁም በቱሪዝም ዘርፉ የመረጃና ልምድ ልውውጥ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይዟል።


ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

ኢትዮጵያና ደቡብ አፍሪካ የተፈራረሙት የቱሪዝም ስምምነት ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የሚቆይ መሆኑ ታውቋል።

በዕለቱ ከፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ጎን ለጎን የስምምነቱን አፈጻጸም የሚከታተል በሁለቱም በኩል ሦስት ሦስት አባላት ያሉት ቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሟል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

ዓይነ ስውርነትን እንዴት እንከላከል

ገጽ 8



ለተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላኑ ዝግጅት ውጤታማነት

ገጽ 14



‹‹በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተረሳውን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ መጓዝ በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ አይደለም››

- አቶ ፈቂአሕመድ ነጋሽ
የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያ

ገጽ 6




ከገጠር እስከ ከተማ በኑሮ የተፈተነች ሕይወት

ገጽ 16

## በውስጥ ገጾች

የአስተሳሰብ ግዞት ገጽ 9

ደን + መና= ደመና ገጽ 12



# የዘመን እንግዳ

# ‹‹በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተረሳውን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ መንዝ በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ አይደለም››

- አቶ ፈቂአሕመድ ነጋሽ
የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያ

አስቴር ኤልያስ

**ለበርካታ ዓመታት በውሃና መስኖ ላይ ሰርተዋል። ታላቁ የአባይ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ ለስኬታማነቱ በሙያቸው ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል። በመጀመሪያ ስራ የተቀጠሩት የኢትዮጵያ ሸለቆዎች ልማት ጥናት ባለስልጣን በሚባል ተቋም ውስጥ ነው። ይህ መስሪያ ቤትና የውሃ ሀብት ባለስልጣን በመባል የሚታወቀው መስሪያ ቤት ወደ ውሃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሲያድግ ደግሞ በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ በባለሙያነት፣ በቡድን መሪነት፣ በፕሮጀክት አስተባባሪነት እንዲሁም በመምሪያ ኃላፊነት አገልግለዋል። ሁለት የተለያዩ ዳይሬክተሮችን በተለያየ ጊዜ በምክትል ዳይሬክተርነት መርተዋል። በናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ ስር ካሉ ሶስት ተቋማት አንዱ የሆነውን የምስራቅ ናይል የቴክኒክ ቀጣናዊ ጽህፈት ቤቱን በስራ አስኪያጅነት ለሰባት ዓመት አገልግለዋል። በአባይ ግድቡ ላይ በተደራዳሪነት ለተወሰነ ዓመት የሰሩ ሲሆን፣ በብዙ የትብብር መድረኮች ደግሞ ኢትዮጵያን ወክለው በቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴነት የሚጠበቅባቸውን ተውጥተዋል - የዛሬው የዘመን እንግዳችን የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለሙያው አቶ ፈቂ አሕመድ ነጋሽ።**

**አቶ ፈቂአሕመድ፣ ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ዙሪያ ሰበታ አካባቢ ዳለቲ ተብላ በምትጠራ ቀበሌ ውስጥ ነው። አካባቢዋ ከመሃል አዲስ አበባ 22 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በዚያው በዳለቲ ቀበሌ ነው። ሁለተኛ ደረጃን የተማሩት ደግሞ ሰበታ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በአለማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በእንግሊዝ አገር በክራንፊልድ ዩኒቨርሲቲ በውሃ ሀብት አስተዳደር ላይ ነው። በአሁኑ ሰዓት እየሰሩ ያሉት በግል በውሃ ሀብት አስተዳዳር ላይ የማማከር ስራ ነው። ከዚሁ ከውሃ ሀብት አስተዳደር ላይ ከካበተ ልምዳቸው ልንጋራ እንግዳ አድርገን አቅርበናቸዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀም ዙሪያ ያለው ዓለም አቀፍ ህግና መርህ ምን ይመስላል?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** በዓለማችን በጣም በርካታ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች አሉ። ቁጥራቸው ምንም እንኳን ተለዋዋጭ ቢሆንም ከ280 በላይ ይሆናሉ። የወንዞቹ ቁጥር ተለዋዋጭ የሚሆንበት ምክንያትም አዳዲስ አገሮች ሲፈጠሩ ቁጥሩ ከፍ ይላል፤ አገራቱ ሲቀነሱ ደግሞ ቁጥሩ ዝቅ ስለሚል ነው። የዓለማችን 60 በመቶ የመሬት ስፋት፣ የዓለማችን 50 በመቶ የውሃ ሀብትና 40 በመቶ ያህሉ የዓለማችን ሕዝብ የሚኖረው በእነዚህ በወሰን ተሻጋሪ ወንዝ ነው።

እነዚህን ውሃዎች ለማስተዳደር ዓለምአቀፍ የውሃ ሕግ ተብሎ ዓለም በሙሉ የተማመነበት ሕግ የለም፤ ይሁን እንጂ የተባበሩት መንግስታት እኤአ በ1997 ያወጣው የዓለም አቀፍ የውሃ ድንጋጌ አለ። ይህ የውሃ ድንጋጌ በአሁኑ ጊዜ የዓለም አቀፍ የዘልማድ የውሃ ሕግ ተብሎ የሚወሰደው ነው።

እዛ ላይ ድንበር ተሻጋሪ ውሃን ለመጠቀም ዋና ተብለው የተነሱትና መሟላት ያለባቸው ነጥቦች ሶስት ናቸው። አንደኛው መሰረታዊ የተባለው ነጥብ ትብብር ነው። በተፋሰሶቹ ውስጥ የሚገኙ አገራት ቀናነት በተሞላበት መልኩ ውሃውን አጠቃቀም ላይ መተባበር አለባቸው የሚለው ነው። ሁለተኛው በወሰን ተሻጋሪው ወንዝ ውስጥ የሚገኙ አገራት በሙሉ ውሃውን ፍትሀዊና ምክንያታዊ በሆኑ መልኩ መጠቀም ይችላሉ የሚል ነው። ሶስተኛው መሰረታዊ ጉዳይ በአጠቃላይ በአጠቃቀም ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚል ነው። እነዚህን መርሆዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁሉም አገራት የሚጠቀምባቸው መሰረታዊ መርሆዎች ተብለው የሚታወቁ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ህግና መርህ አኳያ ኢትዮጵያ በአባይ ውሀ አጠቃቀም ዙሪያ የያዘችው አቋም በመርህ ደረጃ እንዴት ይታያል?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** የአባይ ውሃ ብለን በምንወስድበት ጊዜ የባሮ አኮቦን፣ የተከዜን እና የመረብን ተፋሰሶች ውሃ ያጠቃልላል፤ አባይ ሲባል ናይል ወይም ጥቁር አባይን ብዙውን ጊዜ ስለምንቀላቀል ነው። ኢትዮጵያ ይህን ውሃ ለመጠቀም በመጀመሪያ ደረጃ እንደ ማዕቀፍ የምትጠቀመው ፖሊሲ አላት። ይኸውም የውሃ አስተዳደር ፖሊሲ በሚል የሚታወቅ ነው። ይህ ፖሊሲ በአሁኑ ወቅት እየተከለሰ ነው። ነገር ግን እኤአ በ1999 የወጣ የኢትዮጵያ የውሃ አስተዳደር ፖሊሲ አለ። ይህ ፖሊሲ የድንበር ተሻጋሪ ውሃን በተመለከተ የራሱ የሆነ ማዕቀፍ አለው። በዛ ማዕቀፍ ውስጥ ዋና ዋና አንኳር የተባሉት ከዓለም አቀፍ ሕግ ጋር የተያያዙ ናቸው። ለምሳሌ ከተጋሪ አገራት ጋር መተባበር፣ ወንዞቹን ምክንያታዊና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መጠቀም፣ ዓለም አቀፍ የውሃ ሕጎችን በተመለከተ ኢትዮጵያ የገባችበት ዓለም አቀፍ ሕጎችን ማክበርን የመሳሰሉ በጣም አንኳር የሆኑ ሕጎች ስላሉ ኢትዮጵያ በፖሊሲ ደረጃ የምትከተለው አካሄድ ወይም አቅጣጫ ከዓለም አቀፍ ውሃ ሕግ ጋር የተያያዘ ነው።

በተግባር ደረጃ በምናይበት ወቅት በሁሉም ተፋሰሶች ውስጥ አሊያም ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ውስጥ ኢትዮጵያ ከተጋሪ አገራት ጋር በተለያየ መልኩ ትብብር እያደረገች ነው። ለምሳሌ የናይልን ብንወስድ የናይል የትብብር መድረክ አለ። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በትብብሩ ላይ ቁልፍ ሚና እየተጫወተች ነው። ስለዚህ ትብብሩ ውስጥ አለችበት። በሌላ በኩል ደግሞ ሕጋዊ ማዕቀፉ ላይ በተደረገው እንቅስቃሴ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ ትልቅ ሚና ተጫውታለች፤ ተደራድራለች፤ ፈርማለች፤ ብሎም አጽድቃለች። ከዚህ በላይም ፋናወጊ ነበረች። ሌላ ደግሞ የውሃ ሀብት አጠቃቀሟን በተመለከተ በተቻለ መጠን ከአገራቱ ጋር ተነጋግራ ጥቅም ላይ የምታውልበት ሁኔታ አለ። ይሁንና ከአንዳንድ አገራት ጋር ጉዳዩን ማከናወን አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ግን ኢትዮጵያ ባመነችበት ይህ አጠቃቀሜ ፍትሃዊና ምክንያታዊ ነው፤ በሌሎች ላይ ጉዳት አያደርስም ብላ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጋ ነው እየተንቀሳቀሰች ያለችው። በዛ መልኩ ብዙም ከዓለም አቀፍ ሕግ ውጭ የሆነ ነገር እያደረግን አይደለም የሚል እምነት አለኝ።



ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

**በተቻለ መጠን ውሃችንን አከማችተን ልንቆጣጠረው በምንችለው የግብርና ዘዴ ላይ ማተኮር አለብን**

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን እውነታ በአባይ ተፋሰስ አገራት ተግባራዊ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች ምን ይመስላሉ? እያጋጠማቸው ያለው ተግዳሮትስ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** የአባይ ውሃ አጠቃቀምን በተመለከተ ከአሁን በፊት በጣም በርካታ የትብብር ተግባራት ተደርገው ነበር። በተለይ እኤአ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስከ 1990ዎቹ መጨረሻ ድረስ ሶስት የትብብር ስራዎች ተሰርተዋል። እነዚህ የትብብር ስራዎች ግን በግብጽ እና ሱዳን የተመሩ እንዲሁም በአጋሮቻቸው የታገዙ ናቸው። በተለይም በአብዛኛው በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያላተኮሩ፤ የተፋሰሱን አገራት አቅጣጫ ለማንሳት ወይም ለማደናገር የተዘጋጁ ትብብሮች ስለነበሩ ኢትዮጵያ በዛ ላይ የተሳታፈችው በታዛቢነት ብቻ ነው። ታዛቢ መሆን ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም መረጃ ይገኛል። የራስንም አቋም የማሳያ መድረክ ስለሚሆን ጠቃሚ ነው። ይሁንና ኢትዮጵያ የተሳተፈችው በታዛቢነት ብቻ ነው።

እኤአ 1990ዎቹ መጨረሻዎቹ ላይ ግን ኢትዮጵያ እዛው ታዛቢ ሆና ከተወሰኑ የላይኛው ተፋሰስ አገራትና በተለይ ከዓለምአቀፍ የልማት ድርጅት ማለትም ከተባበሩት መንግስታት አንዱ ተቋም ጋር በመሆን ባደረገችው ጥረት የናይል ትብብር መድረክ እንዲቋቋም አድርጋለች። መድረኩ እስካሁን በስራ ላይ ነው። መድረኩ ከመቋቋሙ በፊት ግን በተለይ 1997 የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ድርድር እንዲጀመር ያደረገችው ኢትዮጵያ ወትውታ ነው። ስለዚህ በናይል ውስጥ በትብብርም ሆነ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ በመፍጠሩ ደረጃ ከላይኛው ተፋሰስ አገራት ጋር ሆና ኢትዮጵያ በጣም በርካታ ስራ ሰርታለች። እስካሁንም እየመራች ነው ያለችው።

እነዚህ ሁለቱ በተለይ የትብብር ስራውም ሆነ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፉ በተለይ ዓለማአቀፍ ሕግ ተፋሰስ ውስጥ በማስፈን የውሃ አጠቃቀሙ በሕግና በስርዓት እንዲመራ እንክብካቤውም፣ ልማቱም፣ ጥበቃውም ሁሉም ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ እንዲመራ የሚያደርጉ ስለሆኑ ብዙ ስራዎች በተፋሰሱ አገራት ተሰርተዋል። ብዙዎቹም ይህንን ስምምነት ተቀብለውታል። ከ11ዱ ውስጥ ወደስድስት አገራትም ፈርመውታል። አራቱ ደግሞ አጽድቀውታል። ሶስት አገራት ደግሞ የማጽደቅ ሒደት ላይ ይገኛሉ። ምንም እንኳ የዘገየ ቢመስልም ጥሩ አቅጣጫ ላይ ይገኛል ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይ በግብጽ በኩል በአባይ ወንዝ ውሃ ፍትሀዊ አጠቃቀም እንዳይኖር የሚደረገው ያልተገባ አካሄድ በዚህ ዘመን ምን ያህል አዋጭ ነው?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** ግብጽ በተፋሰሱ ውስጥ የምትከተለው የራሷ የሆነ ፖሊሲ አላት። አብዛኛው ፖሊሲዋ ራሷን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግና ሌሎችንም የተፋሰሱ አገራት በተለይ ውሃ አመንጪዎችን አግላይ የሆነ አቅጣጫ ነው እየተከተለች ያለችው። ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሌሎቹን ያላከተተ ስምምነት ማካሄድ

### ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



ነው። እኤአ በ1929 እና በ1959 የተፈረሙት ስምምነቶች የቅኝ ግዛትና የድሮ ቅኝ ግዛት ስምምነቶች ናቸው። ዛሬም የቅኝ ግዛት በጠፋበት ዘመን ግብጾች በዚህ ስምምነት ላይ ለመንጠልጠል ይሞክራሉ። ራሳቸው መንጠልጠል ብቻ ሳይሆን ስምምነቱን በሌሎችም ላይ ለመጫን ሙከራ ያደርጋሉ። ይህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተረሳውን የቅኝ ግዛት ስምምነት ይዞ መጓዝ በየትኛውም መመዘኛ የሚያዋጣ አይደለም።

ሌላው እነሱ የሚፈልጉት የላይኛው ተፋሰስ አገራት በተለይም ኢትዮጵያ በጣም ድሃ፣ ደካማ እና ተጋላጭ ሆና እንድትቀጥል ነው። ለዚህም በርካታ የራሳቸው ስልቶች አሏቸው። እንዲያም ቢሆን በተለይ ዓለም እንደ አንድ መንደር በሆነበት ብሎም በሳይንስና በቴክኖሎጂ በረቀቀበት ዘመን እንዲህ አይነት ኋላቀር አስተሳሰብ ይዞ አንድን አገር ለመጉዳትና ለማፍረስ የሚደረጉ ጥረቶች በምንም መልኩ ተቀባይነት የላቸውም።

በተፋሰሱ ውስጥ ያለ የውሃ ሀብት የተፋሰሱ አገራት የጋራ ሀብት ነው። ይህ በግልጽ መታወቅ መቻል አለበት። ሁሉም አገር ባለው ሀብት ላይ ሉዓላዊ መብት አለው። ውሃን በተመለከተ ግን ይህ ሉዓላዊ መብት ውስንነት አለው። ለምሳሌ እኛ የላይኛው ተፋሰስ አገር ነን። ውሃው የሚነሳው በአብዛኛው ከእኛ አገር ነው። እኛ በዚህ ውሃ አጠቃቀም ላይ ሉዓላዊ መብት አለን። ይህ ሉዓላዊ መብታችን ግን ውስንነት አለው። ምክንያቱም ውሃውን ሙሉ በሙሉ እንጠቀም ካልን ውሃው ለብዙ ሚሊዮን ዓመታት ወደታችኛው ተፋሰስ አገራት እየሄደ በዛ ውሃ ላይ ሕይወት መመስረት ተችሏል። በዚሁ እድገቱም ስልጣኔውም ስለተመሰረተ ያንን ማጥፋት እንዳይሆን ያንን ሳያጠፋ እኛ የምንጠቀምበት ሁኔታ ነው መፈጠር ያለበት። ግብጾቹም ቢሆኑ ማሰብ ያለባቸው በዛ መልኩ ነው። ውሃ የሚሄደው ከዚህ ከኢትዮጵያ ነው፤ እዚህም ሕይወት አለ፤ ልማትና እድገትም አለ። ተስፋና ፍላጎትም እንዲሁ አለ። በዚህ መልኩ መተሳሰብ ካለ አብሮ መጠቀም ይቻላል። ካልሆነ ግን እኛ ብቻ እንጠቀም የሚባል ከሆነ ተጎጂ የሚሆኑት እነርሱ ናቸው። ምክንያቱም ውሃ የሚሄደው ከዚህ ነው። የላይኛው ተፋሰስ አገራት ትክክል ናቸው፤ የላይኛው ተፋሰስ አገራት ለታችኛዎቹ ተፋሰስ አገራት ያስባሉ፤ ይጨነቃሉም። ይህ ሁኔታ ግን ከላይኛዎቹ ተፋሰስ አገራት እየተጠበቀ አይደለም። ሁሌም የታችኛዎቹ ተፋሰስ አገራት የላይኛዎቹ ተፋሰስ አገራት ትንሽ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የሚያዩት በፍራቻና በጥርጣሬ እንዲሁም በተቃርኖ ነው። ይህ አይነቱ አተያይ የሚቀረፍበት ሁኔታ ነው መመቻቸት ያለበት። ይህ ካልሆነ ግን በአሁኑ ያውም በ21ኛ ክፍለ ዘመን ይሄ አስተሳሰብ ኋላቀር በመሆኑ መተው አለበት ። መጣላትም ያለበትና በፍጹም የማያዋጣ መንገድ ስለሆነ በተቻለ መጠን ያንን በመተው ወደ ትብብር የሚመጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በተለይም ከድርቅ ጋር በተያያዘ ፈታኝ የሆነ አገራዊ ችግር እየታየ ነው፤ ይህን በዘለቄታ ለመፍታት የውሃ ሀብታችንን በአግባቡ መጠቀም ወሳኝ እንደሆነ ይጠቀሳል፤ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** በጣም አሳዛኝ ክስተት ነው፤ ለዘመናት ዜጎቻችን ሲያልቁ፣ ሲጎዱና ሕይወት ሲጠፋ እንዲሁም በኑሮ ሲጎሳቆሉና ሲፈናቀሉ እናያለን። ይሄ ሁኔታ ሲከሰት መደገም የለበትም በሚል በጣም ብዙ ጥናቶች ወዲያው ተከናውነው ዝግጅቶችም ተደርጓል፤ ነገር ግን ወደተግባር ልንቀይራቸው አልቻልንም።

አሁንም ምናልባት ከ1966 ዓ.ም ልናፍርበት ከተገባው የረሃብ ክስተት በኋላ ይህ ሲከሰት እንዲሁ እያስተዋልን ነውና በዓለም አቀፍ ፊት ቆሞ እህልም ሆነ እርዳታ መለመን እንደ አገር በእውነቱ በጣም ሞራል የሚነካ ጉዳይ ነው። ሁሌም ይህን ነገር እንቀርፋለን፤ እናቆመዋለን ብለን ከመፎከር በዘለለ ጉዳዩ ልክ ሲያልቅ እንረሳና የምንሄደው ወደሌሎች ተግባራት ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ጉዳይ ማንሳት እፈልጋለሁ። የዛሬ አስር ዓመት ገደማ የተፋሰሱ አገራት ባለሙያዎችን ግቤ አንድ፣ ሁለት እና ሶስትን ለማስጎብኘት ይዣቸው እሄድ ነበር። ወሩ ነሐሴ ነበር። ወደስፍራው የሄድነው በመኪና ነው። አቅጣጫችንም ወደጅማ መስመር ነበርና ሶኮሩ አካባቢ ግቤ አንድ የሚባለው ቦታ እስከንደርስ ድረስ ዝናብ ይዘንባል። ውሃ በከፍተኛ ሁኔታ የሚተኛበት አካባቢ አለ። ሜዳው በሙሉ በውሃ ተጥለቅልቋል። ልክ እዛ ስንደርስ አብረን ስንጓዝ የነበሩት ከመኪና ወረዱና እኔንም ጠርተውኝ ‹‹ለምን ግን?›› የሚል ጥያቄ ነው የሰነዘሩት። ሌላ ምንም አላሉም። ‹‹ለምን ግን?›› የሚለውን ጥያቄ የሰነዘሩልኝ ምክንያት ምን እንደሆነ ገባኝ። እሱ ማለት ይህ ሁሉ ውሃ እና መሬት እያለ ለምንድ ነው የምትራቡት ማለታቸው ነው። በቃ የእኛ ስህተት ነው፤ የፖሊሲ አውጪዎች ስህተት ነው። ሕዝባችንን ለዚህ ያጋለጥነው እኛ ነን ነው ያልኩት። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተለይ እያንዳንዱ የመማር እድል ያገኘ ኢትዮጵያዊ ይህን ነገር የማስጠበቅ ግዴታ አለበት። በሕዝቡ ግብር ነው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እየተማረ ያለው፤ የዘነጋውም እሱን ነው።

የተራቡ ሰዎች በረሃብ እንዳያልቁ እያንዳንዱ ተጠያቂነቱን ማወቅ መቻል አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ ማወቅ ያለበት እሱን ነው። ሁለተኛ ደረጃ ረጅም ጊዜ እቅድ ማውጣት ብሎም ያንን እቅድ መተግበር ነው። እያንዳንዱ ተፋሰስ ላይ የረጅም ዓመት እቅድ አለ። ያ እቅድ ተቀምጦ አቧራ እየጠጣ ነው። ለምሳሌ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በየተፋሰሱ እቅድ አለው። እነዚህ ድርቅ የገባባቸው ቦታዎች በሙሉ ማስተር ፕላን ተዘጋጅቶ ተቀምጧል። ያንን የመተግበር ጉዳይ ነው። ስለዚህ የፖሊሲ ችግር የለብንም። የስትራቴጂም ሆነ የእቅድም ችግር የለብንም። ችግሩ ያለው ግን አመለካከት ላይና አስተሳሰብ ላይ ነው። በዛ በኩል አንድ ቀን ገብቶን ዜጎቻችንን እናድናለን የሚል አመለካከት ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የውሃ ሀብታችንን ስመጠቀም በምናደርገው ጥረት በግብጽ በኩል ተግዳሮቶች እያጋጠሙን ከመሆናችን በተጨማሪ ተግዳሮቶቹ ዓለም አቀፍ ይዘት እንዲኖራቸው ቀን ከሌሊት እየሰራችም ነው፤ ይህ በአገራቱ መካከል በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ፍትሀዊ አሰራር እንዳይሰፍን እያደረገ አይደለም ይላሉ?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** ወደኋላ መለስ ልበልና ለብዙ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የምንጠቀመው ግብርና ዝናብ ላይ የተመሰረተ ነው። በአሁኑ ጊዜ የዝናብ ሁኔታ አስተማማኝ አይደለም። ከከባቢ የአየር ለውጥ ጋር በተያያዘ መጠኑ በጣም ቀንሷል። ስርጭቱም በጊዜም ሆነ በቦታ በጣም ተዛብቷል። ስለዚህ በዝናብ ላይ የተመሰረተ እርሻ በአብዛኛው አስተማማኝ አይደለም፤ አዋጭም አይደለም። በተቻለ መጠን ውሃችንን አከማችተን ልንቆጣጠረው በምንችለው የግብርና ዘዴ ላይ ማተኮር አለብን። እሱም የመስኖ ልማት ነው። በጣም ትልልቅና ሰፋፊ መስኖዎች መገንባት አለባቸው። እነዚህ መስኖዎች በዓመት ሁለቴ ወይም ሶስቴ ማምረት የሚያስችሉ ናቸው። የሚመረተው በዝናብ ከሆነ በዓመት አንዴ ነው። እሱም ደግሞ ዝናብ ሊዘንብም ላይዘንብም የሚችልበት አጋጣሚ አለና አስተማማኝ አይደለም። በዝናብ በሔክታር የምናገኘውን ምርት መስኖ ብናለማ እስከ ሶስትና አራት እጥፍ ማሳደግ ይቻላል። ከዚህ ጎን ለጎን የሚያድገው የምርት ጥራትም ነው። የሚፈለገውንም አይነት ምርት ማምረት እንችላለን። ይሄ አንድ አቅጣጫ ነው መሆን ያለበት።

ከትልልቅ መስኖ ባለፈ ደግሞ ውሃ በተለይ አርሶ አደሩ በማሳው ላይ እያከማቸ የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ መፍጠር መቻል አለብን። ይህ ሲደረግ በዘመቻ መሆን የለበትም። ከአሁን በፊት በዘመቻ ተጀምሮ ጉዳይ ውድቅ ሲሆን ታይቷል። እዚህ አገር ላይ ዘመቻ በየጊዜው ይካሄዳል። የሚሰሩ የዘመቻ ስራዎች ግን ውድቅ ሲሆኑ ተስተውሏል።

ከዚህ ቀደም የውሃ ማቆር ተብሎ ዘመቻ ተካሄደ፤ ያ ፕሮግራም ግን ወድቋል። ስለዚህ በተጠና ሁኔታ ለእያንዳንዱ አካባቢ የተዘጋጀ ቴክኖሎጂ ተሰርቶና ተግባራዊ ተደርጎ አርሶ አደሩ ቤቱና ማሳው አካባቢ ውሃ አጠራቅሞ የሚያመርትበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። በተለይ ደግሞ እነዚህ ድርቅ የሚያጠቃቸው አካባቢዎች በቂ ዝናብ ስለማይኖራቸው የከርሰ ምድር ውሃ የሚጠቀሙበት ሁኔታ ካልሆነም ደግሞ ውሃ ካለበት ወደሌለበት ከተፋሰስ ወደተፋሰስ የማሻገር ስርዓት ማካሄድ ነው። ያንን ተግባራዊ እያደረጉ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል።

እንግዲህ ግብጾች በጣም በርካታ ስልት አላቸው። በተለይ ኢትዮጵያ ላይ ጫና እንዲፈጠር ውሃ አጠቃቀሚ ዓለማአቀፋዊ ይዘት እንዲኖርም የሚያደርጉት ጥረት አለ። ውሃው የተፋሰሱ አገራት የጋራ ሀብት ነው። የሚመከረውም የተፋሰሱ አገራት ተቀምጠው በግልጽነትና ቀናነት በተሞላበት ሁኔታ ውሃውን በጋራ መጠቀም ነው። አንደኛው የሌላኛውን ስጋት፣ ፍርሃት ብሎም ፍላጎት ከተረዳ አብሮ መጠቀም ይቻላል። ውሃው ደግሞ በጣም በቂ ነው። ስለዚህ በጋራ ከተጠቀምን የጋራ ተጠቃሚ እንሆናለን። በጋራ ካልተጠቀምን ግን ሁላችንም እናጣለን።

ሶስተኛ አካል ማስገባት አግባብ አይደለም። ሶስተኛው አካል የእኛን ፍላጎት አይጋራም፤ የእኛን ፍርሃትም አይጋራም። ሶስተኛ አገራትን እዚህ ውስጥ መክተት የማይደገፍ ተግባር ነው። ግብጾች እያደረጉት ያለው ሩጫ በፍጹም የማይደገፍ ነው። ጫና ሊያመጣ ይችል ይሆናል፤ ግን ውጤት አያመጣም።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ግብጽ የአባይ ግድብን ጉዳይ በአረብ ሊግ ቋሚ አጀንዳ እንዲሆን ጥሪ አቅርባ አጸድቃለች፤ ይህ ከአህጉሪቱ አልፎ የሄደ በመሆኑ ያልተገባ ጣልቃ ገብነት አይሆንም?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** የአረብ ሊግ የተቋቋመበት የራሱ የሆነ ዓላማ ይዞ ነው። በአረብ አገራት ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ጫና እከላከላለሁ ነው የሚለው። ነገር ግን የአረብ አገራት በሌሎች ላይ የሚያደርሱት ጫና ካለ የእሱ ጉዳይ አይሆንም። ስለዚህ በጣም በጠባብነት ላይ የተመሰረተ ተቋም ነው። ለምሳሌ የአረብ የውሃ ምክር ቤት ተቋም የሚባል አለ። ይህ ምክር ቤት የአረብ ውሃ የሚላቸው ወንዞች አሉ። እነዚህ ወንዞች ለምሳሌ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ቱርክ ውስጥ የሚገኙ የአረብ ውሃ ናቸው ይላል። እስራኤል ያለችበት የዮሮዳኖስን ውሃ የአረብ ነው ይላል። ኢትዮጵያ ያለችበትን የመረብን፣ የአባይን፣ የተከዜን፣ የባሮ አኮቦን ውሃ የአረብ ነው ይላል። ለዚህ በምክንያትነት የሚያስቀምጠው ግብጽና ሱዳን የአረብ ሊግ አባል ስለሆኑ ነው በማለት ነው። ከዚያ ያልፍና ዋቤ ሸበሌን እና ገናሌ ዳዋን የአረብ ውሃ ነው ይላል። እንዴት ሲባል ደግሞ ሶማሊያ የአረብ ሊግ አባል ስለሆነች ነው የሚል አመክንዮ ይሰጣል። የአረብ ሊግ አገራት በቂ ውሃ ስለሌላቸው እነዚህን ውሃ የትኛውም አካል እንዳይነካው ይላል። ይህ አባባሉ ተቀባይነት የሌለው፣ ኋላቀር የሆነና ኢሰብዓዊም ጭምር ነው። እንዲህ አይነት አስተሳሰብ የሚያራምድ ተቋም ስለሆነ አግባብነት የሌለው ነው ባይ ነኝ። በዚህ ጉዳይ ላይ እጁን መክተቱ ምንም የሚያመጣው ጥቅም የለም፤ ይልቁንም የሚያመጣው ጉዳት ነው። የመጀመሪያው ነገር ጉዳዩ የኢትዮጵያ፣ የሱዳንና የግብጽ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ የአረብ ሊግ አባል አይደለችም። ስለዚህ ምንም የሚፈጥሩት ነገር አይኖርም።

በሌላ በኩል ግን የተቋሙ በዚህ ጉዳይ እጁን መክተት በሶስቱ አገራት ውስጥ ያለውን መተማመን፣ መተሳሰብና መተጋገዝ ያሻክራል እንጂ አንዳች የሚያመጣው ፋይዳ የለም። ከዚህ ውጭ ተቋሙ እርባና አለው ብዬ አላምንም።

**አዲስ ዘመን፡- የአባይ ግድብ ዘንድሮ 12ኛው ዓመቱን መያዙ ይታወቃል፤ አንዳንዶች ረጅም ጊዜ ወሰደ ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ በጥሩ ሁኔታ እየተጠናቀቀ ነው ይላሉ፤ እርስዎ በዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** ይህን ጉዳይ በሁለት መልኩ መውሰድ ይቻላል፤ ግድቡ ሲጀመር በሰባት ዓመት ማለትም በ2003 ዓ.ም ተጀምሮ በ2010 ዓ.ም ያልቃል ነበር የተባለው። ከዛ ባለፈ ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ እንደ አባይ አይነቱ ውስብስብ ግድቦች ተጀምረው በወቅቱ የመጠናቀቅ እድላቸው አነስተኛ ነው። ምክንያቱም በባህሪያቸው ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው። እንኳን የሀብትና የቴክኖሎጂ ችግር እያለብን ቀርቶ እንደዚህ አይነት ግድብ ሲገነባ በዓለምአቀፍ ደረጃም የሚያሳየው ተሞክሮ ፈጥኖ አለማለቁ ነው። እንደእነዚህ አይነት ፕሮጀክቶች ከ40 እስከ 60 በመቶ ያህል በተያዘላቸው ጊዜ የሚጠናቀቁ አይደሉም። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ከ40 እስከ 60 በመቶ በገንዘብ ደረጃ ተጨማሪ ክፍያን የሚጠይቁ ናቸው ይባላል። ስለዚህ ይህ የአባይ ግድብ በ10 እና በ11 ዓመት ውስጥ ቢያልቅ በጣም ትክክል ነው ማለት ይቻላል። ከዛ አኳያ ሲታይ አንድ ዓመት ዘግይቷል። በአጠቃላይ በተወሰነ ደረጃ ዘግይቷል ብሎ መውሰዱ ጥሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአባይ ግድብ በእስካሁኑ ጉዞው በግብጽም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተጋፈጣቸው የመጣው ተግዳሮት ይታወቃል፤ ይህ ተግዳሮት የታለፈበትን አካሄድ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** ግድቡ የመሰረተ ድንጋይ ተቀምጦለት እንደሚገነባ ከተበሰረበት ጊዜ ጀምሮ ከግብጽና ከሱዳን በተለይ ከግብጽ ከፍተኛ ጫና ነበረው። ይህንን ጫና ለመቋቋም ደግሞ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ አካሄድ ነበራት። ያንን ጫና ለመቋቋም ኢትዮጵያ የጀመረችው ግልጽነት በማስፈኑ ላይ ነው። እነሱንም ባላቸው ባለሙያዎች ደረጃም ሆነ በሚኒስትርም ደረጃ ለማሳተፍ ሞክራለች። በመሪዎች ደረጃም በጣም በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። ፕሮጀክቱን ሄደውም እንዲጎበኙት ተደርጓል። ብዙም ተመክሯል፤ ተዘክሯልም። ነገር ግን አልተቻለም። ጊዜ በሔደ ቁጥር ግብጾች ሲሞክሩ የቆዩት በራሳቸው ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጫና ለመፍጠር ነው።

በመጀመሪያ የዓለም ባንክን ለማስገባት ሞከሩ። ኢትዮጵያ በዚህም በዚያም ብላ ለማስቀረት ሞከረች። በኋላ ላይ ደግሞ የዓለም ባንክንና የአሜሪካ መንግስትን ለማስገባት ጥረት አደረጉ። የዓለም ባንክና የአሜሪካ መንግስት እንዲገቡ በተደረገው ጥረት ላይ የእኛ ኢትዮጵያውያንም እጅ አለበት። በኋላ ላይ በማስወጣቱ በኩልም ያየነው ትልቅ አበሳ ነው። በቀላሉ እንዳስገባናቸው በቀላሉ ሊወጡ አልቻሉም። እንደምንም ግን የእነርሱ ጫና እንዲቀንስ ተደርጎ ጉዳዩ ወደአፍሪካ ሕብረት እንዲመለስ ተደረገ። ግብጾችም በአፍሪካ ህብረት ላይ እምነት የላቸውም። የአፍሪካ ሕብረትና የናይል ቤዚን የትብብር መድረክ የሚባለው በጥቁር አገሮች የሚመራ ህብረት ስለሆነ ለአረባዊቷ አገር ግብጽ ፍትሃዊ አይሆንም የሚል እምነት አላቸውና ሊያምኑት አልቻሉም፤ አሁንም መልሰው ወደተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ወስደው የነበረ ቢሆንም ወደ አፍሪካ ህብረት መልሷቸዋል። የአረብ ሊግ ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ ሁሌም መግለጫ ያወጣል።

ዋናው ነገር እኛ በዚህ ዙሪያ አገራዊ አንድነትን መፍጠር፣ ለሰላምና አንድነት መትጋት አለብን። እንደ ድርቅና ረሃብ ያሉ ነገሮች በአገራችን እንዳይከሰቱ የምንወድ ከሆነ ለአገራዊ አንድነት በመትጋት ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ላይ መስራት ይጠበቅብናል። ግብጾች በየጊዜው መግለጫ በማውጣት ሊያስፈራሩን የሚሞክሩት እኛ አንድነታችንን ያጣን በመሰላቸውና በተቸገርን ጊዜ ነው። በተለይ መረጋጋት ያጣን በመሰላቸው ጊዜ መጮህ ይጀምራሉና መሰራት ያለበት ሰላማችንም ላይ ነው ብዬ አምናለሁ። ያንን ማድረግ ከቻልን የእነርሱንም ጫና ሆነ የሌላውንም ጩኸት ጭምር ያለምንም ጥርጥር ማዳከም እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ፈቂአሕመድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ዓይነ ስውርነትን እንዴት እንከላከል

እፀገነት አክሊሉ



አይናችን ብርሃናችን ነው፤ ሰርቶ ለመብላት ወጥቶ ለመግባት አይናችን መሰረት ነው። አይን የሰውነታችንን እኩልነት (ባላንስ) መጠበቅም ሌላው ጥቅሙ ነው። እንዲህ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ያለው አይናችን ደግሞ በሚታወቁም በማይታወቁም በሚጠበቁም በማይጠበቁም ችግሮች ሊጎዳና እስከ ወዲያኛውም ልናጣው የምንችልበት ሁኔታ ደግሞ ሰፊ ነው።

በመሆኑም አይናችንን መንከባከብ ብሎም በየጊዜው ስለጤንነቱ ባለሙያን ማናገርና ማማከር የሁል ጊዜ ልምዳችን ሊሆን እንደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች አብዝተው ይመክራሉ።

እኛም ለዛሬ የአይናችንን ጤና እንዴት መጠበቅ አለብን? አይነ ስውርነትን ሊያመጡብን የሚችሉ ምክንያቶች ምንድናቸው? የሚለውን መረጃ ልናካፍላችሁ ወደናል።

## ለአይነ ስውርነት አጋላጭ መንስኤዎች

የሞራ ግርዶሽ፣ ግላኮማ፣ ትራኮማ፣ አነጣጥሮ የማየት ችግር (ሪ ፋክቲቭ ኢር)፣ የስኳር ሕመም (ዲያቤቲስ) እና ከመደበኛው የመወለጃ ጊዜ ቀድሞ መወለድ ዓይነ ስውርነትን ከሚያስከትሉ በርካታ መንስኤዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

### የሞራ ግርዶሽ

የሞራ ግርዶሽ በተፈጥሮ ከሚመጡ ለዓይነ ስውርነት አጋላጭ መንስኤዎች አንዱ ሲሆን በኢትዮጵያ ከፍተኛው የዓይነ ስውርነት ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል። ከ 15 ዓመታት በፊት የተካሄደ ጥናት እንዳመላከተው በኢትዮጵያ ከሚኖረው ሕዝብ ቁጥር 1 ነጥብ 6 በመቶው የዕይታ ችግር አለበት። አሁን ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል።

በጥናቱ ግኝት መሰረት ካለው የዓይነ ስውርነት ምጣኔ 50 በመቶ የዓይነ ስውርነት ምክንያቱ የሞራ ግርዶሽ ነው። ይህም በተፈጥሮ (አብሮ በመወለድ)፣ በአደጋ (ምት) እና በዕድሜ መግፋት ሊመጣ ይችላል። የሞራ ግርዶሽን ቀድሞ መከላከል ባይቻልም ከተከሰተ በኋላ ግን በቀዶ ሕክምና ይስተካከላል።

### ግላኮማ

ጤናማ የዓይን ግፊት ከ 10 እስከ 21 ሚሊ ሊትር ድረስ ሲሆን ከ 21 ሚሊ ሜትር በላይ ከሆነ ግፊቱ ከፍ ማለቱ ብቻ ሳይሆን በተጓዳኝ የዓይን ነርቭን (ኦፕቲካል ነርቭ) በመጉዳት ዕይታን ይቀንሳ። ቶሎ ሕክምና ካልተደረገለትም እስከ ዓይነ ስውርነት ያደርሳል። ግላኮማ በዘር ይተላለፋል፣ ምክንያታቸው በውል ባልታወቁ ሁኔታዎች ይከሰታል፣ አንዳንዴ የዓይን ውስጥ ሕመሞችም ይህን ሊያመጡት ይችላሉ።

ምንም ዓይነት የሕመም ምልክት ስለሌለው ዕይታ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ይሄድና ፊት ለፊት ብቻ እንጂ ወደ ጎን ማየት እስከማይቻልበት ደረጃ ያደርሳል።

ግፊቱ ከፍ በሚልበት ጊዜ ደግሞ የራስ ምታት ያስከትላል፣ በመብራት ዙሪያ እንደ ቀስተደመና የሚመስሉ ቀለማትን ያሳያል፣ ብዥታዎችንም ይፈጥራል። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ተመርምሮ ሕክምና መጀመር ይገባል፤ ሕክምናው ለዕድሜ ልክ የሚሰጥ ሲሆን መቋረጥ የለበትም። የተጎዳውን ነርቭ መመለስ ስለማይቻል ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ግፊቱን ለማውረድ መድኃኒቶች ይሰጣሉ። ዕይታ ባለበት እንዲቆይ (እንዳይጠፋ) ለማስቻል ይህን በማድረግ ዕይታን ማቆየት ይቻላል።

### ትራኮማ

በኢትዮጵያ ዓይነ ስውርነትን ከሚያስከትሉ መንስኤዎች ትራኮማ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝና በጀርም የሚመጣ ሕመም ነው። በአብዛኛው የውኃ እጥረት ባለባቸውና ሞቃታማ በሆኑ አካባቢዎች፣ ዝንቦች በብዛት በሚፈለፈሉበት፣ ሰዎች ትፍግፍግ ብለው በሚኖሩበትና በሚተኙበት፣ ፎጣና የትራስ ጨርቆችን በጋራ በመጠቀም ይከሰታል፤ ከሰው ወደሰውም ይተላለፋልም። ይህ ሕመም የዓይንን ቆብ ወደ ውስጥ ቆልምሞ ጸጉሩ የዓይን ብሌንን እየፈገፈገ አቁስሎ ጠባሳ በመፍጠር ብርሃን እንዳይተላለፍ በማድረግ ዓይነ ስውርነትን ያስከትላል። ስለሆነም የአካባቢ እና የግል ንጽህናን በመጠበቅ ቀድሞ መከላከል እና ሕመሙ ከተከሰተ በኋላም ሕክምና በማድረግ በትራኮማ ምክንያት የሚመጣን ዓይነ ስውርነት ማስቀረት ይቻላል።

### አነጣጥሮ የማየት ችግር (ሪ ፋክቲቭ ኢር)

ከአነጣጥሮ የማየት ችግር ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ችግሮች ደረጃቸው የተለያየ ሲሆን በመነጽር የመስተካከል ዕድል እንዳላቸው ይታመናል። በየትኛውም ሰው ላይ ሕመሙ ቢስተዋልም በይበልጥ ልጆች፣ ወጣቶች፣ ተማሪዎች አነጣጥሮ የማየት ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ እንደሚታይባቸው መረጃዎች ያመላክታሉ። ቢያንስ ወደ 7 ነጥብ 8 በመቶ የሚሆነው የዕይታ ችግር ከአነጣጥሮ የማየት ችግር ይመጣል።

እነዚህ ሰዎች ተመርምረው መነጽር ሊታዘዝላቸው እና ዕይታቸውን ማስተካከል የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚገባም ይመከራል።

### የስኳር ሕመም (ዲያቤቲስ)

ሌላኛው የዓይነ ስውርነት መንስኤ በአሁኑ ወቅት ከከተማ እስከ ገጠር እየተስፋፋ የሚገኘም ነው። በደም ውስጥ ያለው የስኳር መጠን ሳይስተካከል ሲቀርና ከፍ ብሎ በሚገኝበት ወቅት እንደሚከሰት የሚታመነው የስኳር ሕመም፥ በባህሪው የደም ስሮችን ልፍስፍስ የማድረግ እና በቀላሉ እንዲቀደዱና ደም እንዲረጩ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ሕክምና ካልተደረገ በዓይን ውስጥ (ረቲና ላይ) ያሉ ቀጫጭን የደም ስሮች በቀላሉ ደም ሊረጩ ይችላሉ፤ ይህን ተከትሎም ዕይታ ሊጎዳና ሊጠፋ የሚችልበት አጋጣሚ ይከሰታል። ስለዚህ የስኳር ታማሚዎች ሁልጊዜ የደም ስኳር መጠናቸው እንዲስተካከል ሕክምናቸውን መከታተል ይጠበቅባቸዋል፤ እንዲህ ሲሆን ዕይታቸው ሳይጎዳ ለረጅም ጊዜ ይቆያል።

### ከመደበኛው የመወለጃ ጊዜ ቀድሞ መወለድ

ከመደበኛው የመወለጃ ጊዜ (ዘጠኝ ወር) ቀድሞ መወለድ ለዓይነ ስውርነት ከሚጋልጡ ምክንያቶች አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል። ሕጻናት በማህጸን ውስጥ እያሉ ሙሉ ዕድገቱን ያልጨረሰው ብሌን (ረቲና) በሚወለዱበት ጊዜ፥ ደም መርጨት፣ የብሌን መላቀቅ ችግር ያስከትልና ለዓይነ ስውርነት ሊያደርስ ይችላል። በመሆኑም ያለ ጊዜያቸው የሚወለዱ ሕጻናትን ወደ ሕክምና በመውሰድ ዓይናቸው እንዲመረመርና ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል። ለዓይነ ስውርነት በማጋለጥ ሂደታቸው ቅደም ተከተል መሰረትም የሞራ ግርዶሽ፣ ትራኮማ፣ ግላኮማ፣ አነጣጥሮ የማየት ችግሮች፣ የስኳር ሕመምና የተለያዩ ምክንያቶች፣ የሕጻናት የዓይነ ስውርነት ችግሮች ይጠቀሳሉ።

በአብዛኛው የዓይን ሕመም ሕክምና በአገር ውስጥ ስለሚሰጥ፥ ህብረተሰቡ በዓይኑ ወይም በዕይታው ላይ ዕክል ሳያጋጥመው ቀድሞ ለመከላከሉ ትኩረት እንዲሰጥና ችግሩ ካጋጠመም ጊዜ ሳያባክኑ ወደ ዐይን ሕክምና ተቋም እንዲሔድ ይመከራል።

ህብረተሰቡ በልማድ ወደ ሕክምና ተቋም የሚሔደው የዕይታ ችግር ሲደርስበት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቢመረመር የዓይኑን በጤንነት የመቆየት ጊዜ ማራዘም ይቻላል። ምክንያቱም በዘር ሊተላለፉ የሚችሉ የዓይን ችግሮች ስላሉና ምንም ዓይነት የሕመም ምልክት ሳያሳዩ (ለምሳሌ ግላኮማ) ዓይነ ስውርነትን የሚያስከትሉም ስለሆኑ።

### በመነጽር የሚስተካከል የማየት ችግር (refractive error)#

በአይን የምናየውን ማንኛውንም ነገር በጥራት ለመመልከት (ምስል ለመፈጠር) ብርሃን ከምንመለከተው ነገር በመነሳት በአይናችን ብሌን እና አይናችን ውስጥ ባለ የተፈጥሮ ሌንስ በማለፍ ረቲና ከሚባለው የአይናችን ክፍል ላይ በትክክል ማረፍ አለበት። ምስል ከሚፈጠርበት የአይናችን የውስጠኛው ክፍል (ረቲና) ከተሰራ በኋላ ወደ አንጎል ይላክና የምናየውን ነገር በጥራት ለመለየት ያስችለናል። ይህ ችግር በአገራችንም በዓለምም ዕይታን ከሚቀንሱ እና ዓይነ ሥውርነት ከሚያመጡ ቀዳሚ ችግሮች ውስጥ ዋነኛው ነው። ታዲያ በመነጽር የሚስተካከል የእይታ ችግር (refractive error) እንዴት ይከሰታል? የሚለውን ብናይ ደግሞ የዓይናችን ብርሃን የመሥበር አቅም ሲያንስ ወይንም ሲበልጥ፤ የአይናችን ኳስ ርዝማኔ (ከውጨኛው የዓይን ብሌን እስከ ውስጠኛው ክፍል ረቲና ያለው ርዝማኔ) ከሚያስፈልገው መጠን ሲያንስ ወይንም ሲበልጥ፤ የዓይን ብሌን የፊት ለፊት ያለው ብርሃን አሳላፊ መስታወት (cornea) ቅርፅ እንደኳስ ትክክለኛ ክብ መሆን ሲገባው በተፈጥሮ እንደ እንቁላል ሞላላ ክብ ከሆነ የብርሃን ስብረትን ያዛባል ብዥታ (astigmatism) ይፈጥራል።

አጭር እይታ ወይም ሾርት ሳይት (myopia) የሚባለው ችግር ያለበት ሠው ቅርብ ማየት ይችላል ነገር ግን ከሩቅ ማየት አይችልም። ረጅም እይታ ወይም ሎንግ ሳይት (hyperopia) የሚባለው ችግር ያለበት ሠው ከሩቅ ማየት ይችላል ነገር ግን ከቅርብ ማየት አይችልም። ብዥታ (astigmatism) የሚባለው ችግር ያለበት ሠው ከቅርብም ከሩቅም ማየት አይችልም። ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ያለበት ሰው በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ የእይታ መቀነስ ወይም ብዥታ ያጋጥመዋል። ከእይታ ጋር የተያያዘ ራስ ህመም፣ የእይታ አትኩሮት የሚፈልግ ስራ ሲሰራ የአይን ድካም፣ ወደ ውስጥ የመሳብ ስሜት ይኖረዋል። ውዝዋዜ ወይም ውጋት የለውም፣ አይቀላም፣ አያስለቅስም፣ አይናር አይዝም። ይህ የእይታ ችግር በአብዛኛው ጊዜ በተፈጥሮ የሚከሠት እና በዘር የሚተላለፍ ነው። አንዳንዴ ከአይን ሞራ ግርዶሽ ቀዶ ጥገና በኋላ ይከሠታል። በመነጽር የሚስተካከል የእይታ ችግር በሁለቱም ፆታ እንዲሁም በሁሉም የእድሜ ክልል የሚከሠት ሲሆን በቤተሰብ (በዘር) ያለባቸው ከሌላው ይበልጥ ይኖርባቸዋል።

### በወቅቱ ያልታከመ ከሆነ፦

ችግሩ ያለበት ሰው የተሰማራበትን የሥራ ውጤታማነትን ይቀንሳል። ችግሩ ያለበት ህፃን ከሆነ እንደማንኛውም የሠውነታችን ክፍል ዓይናችንና እይታችን የሚያድገው በሂደት ነው። ይህ የእይታ እድገት ሂደት በአመዛኙ እስከ 7 ዓመት ድረስ የሚከወን ቢሆንም የመጀመሪያዎቹ 2 ዓመታት በጣም ወሳኝ ናቸው።

በመነጽር የሚስተካከል የማየት ችግር በጊዜው ካልተስተካከለ ይህን የእድገት ሂደት በማስተጓጎል የሕፃኑ ዓይን ሠንፎ እንዲቀር ያደርጋል። ይህም ማለት በኋላ በመነጽርም ቢሆን ለማከም ይከብዳል ማለት ነው። የቅርብ እይታ ሾርት ሳይት (myopia) የሚባለው በአብዛኛው ጊዜ አንዴ ከጀመረ በኋላ መጠኑ እየጨመረ ይሄዳል። ይህም በውስጠኛው የአይናችን ምስል መፍጠሪያ ክፍል (ረቲና) በመለጠጥ በመበጣጠስ እና ጠባሳ በመፍጠር ለአይነ ስውርነት ሊያደርስ ይችላል። ለዚህ መፍትሄው በጊዜው መታከም እና ክትትል ማድረግ ነው።

ባልተስተካከለ እይታ ምክንያት በሚሠሩበት እና በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የመውደቅ የመጋጨት በማሽን የመጎዳት ወ.ዘ.ተ አደጋ ሊገጥም ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግም ይመከራል።

ምርመራውና ህክምናው በዘርፉ በሠለጠኑ የዓይን ህክምና ባለሙያዎች (ኦፕቶሜትሪስት) ይሰጣል።

የቤተሰባችን የወላጆቻችንን የአይን ጤና ሁኔታ መጠየቅ በዘር የሚተላለፉ የአይን በሽታዎችና ችግሮች በዘር ሀረጋችን ውስጥ ካሉ ለከፋ ጉዳት ሳንዳረግ ቀድመን ለማወቅ ስለሚረዳን ቤተሰቦቻችንን መጠየቅ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዘር የሚተላለፍ ችግር እንዳለብን በህክምና ከታወቀ ለሌሎች ቤተሰቦቻችን የአይን ምርመራ እንዲያደርጉ መንገር አለብን። ለምሳሌ ግላውኮማ እና ከርቀት ያለማየት ችግር ከዘር የሚተላለፉ ሲሆን ከቤተሰብ በአንዱ ልጅ ላይ ግላውኮማ ካለ በሌሎች የቤተሰቡ አባላት ላይ የመከሰት እድሉ በ5 እጥፍ የበለጠ ነው። ስለ አይናችን መጠየቅ፤ ማወቅ እንዲሁም በዓመት አንድ ጊዜ ምርመራ ማድረግ ልምዳችን መሆን አለበት።

የአይን ግፊት በሽታ (ግላኮማ) እይታን የሚያውክ ከባድ በሽታ ነው። የአይን ግፊት ህመም (ግላኮማ) እንዳለቦት ወይም ለዚሁ ችግር ከሌሎች በበለጠ ተጋላጭ እንደሆኑ ተነግሮት ከሆነ አልያም ደግሞ በአይን ህመም የተጠቃ ሰው ያውቁ ከሆነ ምናልባትም ስለ ግላኮማ ሰምተውከሆነ በየዓመቱ የአይኖትን ጤና ማረጋገጥ እንዳለብዎ ባለሙያዎች ይመክራሉ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የአስተሳሰብ ግዞት

**የጽንሰ ሃሳብ ማፍታቻ፤**

"**ግዞት፡-** እስራት፣ ቅጣት፣ አንድን ሰው ከሚኖርበት አካባቢ፣ አገር፣ ባህል፣ ሥነ ልቦና፣ ማሕበራዊ መስተጋብር ወዘተ. በማውጣት ባዕድ ወደ ሆነ ማሕበረሰብ፣ ቦታ ወይንም አካባቢ በልዩ ጥበቃና ክትትል ውስጥ እንዲኖር አስገድዶ ማኖር ሲሆን ግዞተኛ ደግሞ በግዞት ላይ ያለ ሰውን ይመለከታል። " ከመዛግብተ ቃላት የተውጣጣ ብያኔ (Definition) ነው።

ግዞት ከባርነት ትርጉም ጋር ተቀራራቢ ይዘት ያለው ይምሰል እንጂ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ባህርያቸው ደመቅ ብሎ ይለያል። "ባርነት የሰው ልጅ እንደ መናኛ ሸቀጥ አልባሌ ዋጋ ተተምኖለት በፈንጋዮች ወይንም በአስገባሪዎች አማካይነት ለገበያ ቀርቦ የሚሸጥበት ወይንም በቁስ የሚለወጥበት ኢሰብአዊ (ሰይጣናዊ) ተግባርም የኑሮ ዘይቤም ነው። "

በአንፃሩ ግዞት በአሸናፊ ጦረኞች፣ ወራሪዎች፣ በሹመኞች ወይንም በማዕከላዊ የመንግሥት ገዥዎች ትእዛዝና እውቅና አሸናፊነትን ወይንም የሥልጣን አቅምን ለማሳወቅ ወይንም ለመያዣነት ግለሰቦችን ወይንም በርከት ያሉ ሰዎችን ወደ ተለየ ሥፍራ ወስዶ ማስፈር ነው።

አንዳንድ አገራዊ የግዞት ታሪኮችን እናስታውስ። እብሪተኛው የፋሽስት ሠራዊት ኢትዮጵያን ወሮ በቆየባቸው ዓመታት (ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም) በርካታ ዜጎቻችንን አዚናራ በሚባል የአገሩ አካባቢና በቀይ ባህር ላይ ወደሚገኝ ናኩራ ወደተባለ ደሴት በማጋዝ ከፍተኛ ፋሽስታዊ ድርጊት ፈጽሞባቸዋል።

ከዓመታት በፊት "ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ከተዋሃደችበት ታሪክ ጋር ተያይዞ" ስማቸው በተለያዩ መልኮች ደጋግሞ የሚነሳውን ክቡር ቢትወደድ አስፍሃ ወ/ሚካኤልን ይህ ጸሐፊ አዲስ አበባ ይገኝ በነበረ መኖሪያ ቤታቸው ተገኝቶ በፋሽስት ወረራ ዘመን ተግዘው በአዚናራ ደሴት በነበሩበት ወቅት ሕይወትና ተስፋ ምን ይመስል እንደነበር ጠይቋቸው የሰጡትን ዝርዝር መልስ በአንድ መጽሔት ላይ ታትሞ ተነቧል። የግዞት አስከፊነት ምን ያህል የመረረና የከበደ እንደሆነ ከእኚህ አባት ምስክርነት የማላውቃቸውን ብዙ እውቀቶች ቀስሜያለሁ።

ያንን የእርሳቸውን ከፋ ትዝታ በሚገባ እንዲወክልልኝ በክብር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል "የአዝናራ እስረኛ" ግጥም ውስጥ ከተካተተው ረዥም ተራኪ ሥራ ውስጥ ጥቂት ስንኞችን እንደሚከተለው እጠቅሳለሁ።

**"ቀና ቢሉ ሰማይ ጎንበስ ቢሉ ምድር፣**
**ቀኝ ቢያዩ ጋራ ግራ ቢያዩ ባሕር፤**
**ቦታው የጭካኔ የጭንቅ የመከራ፣**
**ጥንትም ኖሯል ለካ ቦታው ልማደኛ፤**
**ባለም ጦርነት ላይ ገብቶበት እስረኛ፣**
**መቃብር ሆኖታል ለጀርመን ምርኮኛ።**
**ባንድ ወገን ባሕር ነው፣ ባንድ ወገን ተራራ፣**
**እዚያ መካከል ነው የእስረኞች ስፍራ።**
**ባፈሳ ተይዘው እየተጎተቱ፣**
**ከኢትዮጵያ ወጥተው እየተንገላቱ፣**
**በዱር በበረሃ ታመው እየሞቱ። "**

ትረካው አልተቋጨም። ሙሉው ግጥም "የቅኔ አዝመራ" ከሚለው መጽሐፍ እንዲነበብ እያበረታታሁ ግዞትን ወደ ተመለከተ ሌላ የታሪክ ማስታወሻ ልለፍ።

እብሪተኛው የሱማሊያ ጦር በ1969 ዓ.ም ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅትም እንዲሁ በርካታ ዜጎቻችን ደናን (ደናኔ) ወደተባለ አካባቢ በቁጥር በርካታ ወገኖቻችንን በግዞት አፍልሶ ወስዷል። ከግዞተኞቹ መካከል ጥላሁን አትሬሶ "የእኛ ሰው በሶማሊያ እስር ቤቶች"፣ የከበደች ተክለአብን "የት ነው?" በሚል ርዕስ ያሳተመችውን ድንቅ የግጥም መድብል እና ሊሻን አጎናፍር "የምድረ በዳው እረኛ" በሚል አርእስት የተጻፉትን መጻሕፍት ማንበቡ የመራሩን የግዞት ሕይወት ምንነት በሚገባ መገንዘብ ይቻላል። ከግዞተኞቹ መካከል አንዱ የነበሩት ዶ/ር ጥበቡ ኃይለ ሥላሴ የደናንን የግዞት ሥፍራ የገለጹት እንዲህ በማለት ነበር።

"የደናን እስር ቤት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ጣሊያን ደቡብ ሱማሊያን ወርራ በነበረበት ወቅት የተቋቋመ ወህኒ ቤት ነው። ከውጭ ለሚያየው የማይደፈር ጥንታዊ ምሽግ ይመስላል። ከምድር ወደ ላይ ከፍታ እና በረዥሙ የታጠረው የድንጋይ ግንብ የወህኒውም የውስጥ ግድግዳ ስለሆነ ትንንሽ መስኮቶች በግንቡ ዙሪያ ይታያሉ። ...ወታደሮች በየቀኑ እስረኞቹን ከክፍላቸው እያወጡ በግፍ እየደበደቡና እያዳፉ ወደ ተለያየ የጉልበት ሥራ የሚያሰማሩበት ትልቅና ሰፊ ክፍት ሜዳ ግቢው መሃል ይገኛል (ገጽ 170)።

ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የአንድ አገር ሕጋዊ መንግሥት ሥልጣኔን ተቀናቅኖኛል፣ አድሞብኛል፣ ወይንም የመንግሥቴን ክብር አቃሏል ወዘተ. ተብሎ የተጠረጠረን የራሱን ዜጋ ወይንም የመንግሥትን ሹመኛ በቅጣት መልክ ራቅ ወዳለ ዳር አገር በመላክ በጥብቅ ክትትልና ጥበቃ ሥር ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀጣ ማድረግም የተለመደ "መንግሥታዊ ተግባር" ነበር። ግዞተኛው የተወሰነበትን የቅጣት ጊዜ ሲያጠናቅቅ ወይንም በወሰነው አካል ምህረትና ይቅርታ ሲደረግለት ከግዞቱ ቦታ ወደ ቀድሞ ሕይወቱ ተመልሶ የተለመደውን ኑሮውን ሊኖር ይችላል።

ለኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ሥርዓተ መንግሥታት ግዞትና ግዞተኝነት የባህል ያህል ለፖለቲካ አካሄዱ ቤትኛ እንደነበር በተለያዩ ታሪኮቻችን ውስጥ ተጽፎ እናነባለን። ለምሳሌ፡- "አቤቶ እያሱ አጤ ምኒልክ ታመው አልጋ ላይ በዋሉበት ጊዜ ሥልጣነ መንግሥቱን ይቀናቀናሉ ተብለው የጠረጠሯቸውን እቴጌ ጣይቱንና ወይዘሮ ዘውዲቱን (በኋላ ንግሥተ ዘውዲቱ) በግዞት መልክ ጣይቱን እንጦጦ ይገኝ በነበረው ቤተ መንግሥት፣ ዘውዲቱን ደግሞ ሙሎ ወረዳ ፋሌ በሚባለው አካባቢ ርስታቸው ላይ ከሥልጣን ወንበሩ ፊት ገለል በማድረግ ለተወሰነ ጊዜ አርቀዋቸዋል። ልጅ እያሱም እንዲሁ ዕድል ፊቷን አዙራባቸው ቀን ከጣላቸው በኋላ ኩረማሽ፣ ፍቼ እና ሀረርጌ (ጋራ ሙለታ) ባለጊዜ አሸናፊዎቹ ከቦታ ቦታ እያዟዟሩ የግዞትን ዋንጫ እንዲጎነጩ አድርገዋቸዋል።

እጅግ በርካታ መጻሕፍትንና የቴያትር ሥራዎቹን ያወረሰን ታዋቂው የሥነ ጽሑፍ ሰው አቤ ጉበኛ በድርሰት መጻሕፍቱ አማካይነት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሥርዓተ መንግሥት ክፉኛ ይተች ስለነበር በቀድሞው የኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ጎሬና ሞቻ ውስጥ ተፈርዶበት የግዞት ኑሮ እንዲገፋ ተደርጓል። በግዞት ላይ እያለም በሚከተሉት አጫጭር ሰም ለበስ ስንኞች ቁጭቱን ይገልጽ ነበር።

**"አውሬ መስያቸው ፈሩኝ ዘመዶቼ፣**
**ድንገት ቢያዩኝ ጊዜ ከጎሬ ወጥቼ።**

ሰሙ፡- ከተሸሸግሁበት ጉድጓድ (ከጎሬ) ውስጥ ወጣሁ የሚል ሲሆን፤ በወርቅ የሚመሰለው ፍቺ ደግሞ "ጎሬ ተግዣለሁ" ማለት ነው።

**የምትፈልጉኝ ወዳጅ ዘመዶቼ ስሙልኝ ርሮ፣**
**ተስፋ እንዳታደርጉ ሞቻለሁ ዘንድሮ። "**

ስለ ሞቻ የተጠቀሰው ግጥም በትክክል ስለመታወሱ እርግጠኛ ባልሆንም የመልእክቱን ሃሳብ ግን በሚገባ ይገልጻል። ሰሙ ለሞት ተዳርጌያለሁ (ሞቻለሁ) ሲሆን ወርቁ ደግሞ "ሞቻ ውስጥ በግዞት ተጥያለሁ" ማለት ነው።

በግዞትና በግዞተኝነት ጉዳይ ላይ ይህንን ያህል በሰፊ ትንተና ከተንደረደርኩ ዘንድ ወቅታዊና ዐውዳዊ አገራዊ እውነታችንን በተመለከተ በአስተሳሰብ ግዞተኝነት ጉዳይ ላይ ጥቂት ሃሳቦችን ልፈነጣጥቅ።

**"ግዞተኛ አስተሳሰብ በድፍን ቅል ይመሰላል"**

የአስተሳሰብ ግዞተኝነት ከአካላዊ ግዞት እጅግ የከፋና የሚያስከትለው ውጤትም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። አካላዊ ግዞት ጠባሳ አኑሮ የሚያልፈው በአንድ ግለሰብ ወይንም በቅርብ ዘምዶችና ወዳጆች ላይ ብቻ ሊሆን ይችላል። የአስተሳሰብ ግዞተኛ ሆኖ አእምሮን በተለያዩ ቁልፎች ቆልፎ ማሕበረሰብን ለመምራትና ለማገልገል መሞከር ግን ውሎ አድሮ የከፋ ውጤት ማስከተሉ አይቀርም።

የአስተሳሰብ ግዞተኝነት በልማድ፣ በወግና በቋንቋ፣ በብሔርና በጎጥ፣ በትምህርት፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ ሥርዓቶችና በማሕበራዊ ተራክቦ ውስጥ ተጠናክሮ ሲንሰራፋ አገር እያነሰና የዕድገት ምኞትና ተስፋ ቁልቁል እንደ ካሮት ሥር እየሰደደ ሄዶ አደጋ ላይ መውደቅ አይቀሬ ነው። የመጀመሪያው የጋና ጠቅላይ ሚኒስትርና ፕሬዚዳንት የነበሩት ዶ/ር ፍራንሲስ ክዋሚ ንክሩማ ከቅኝ ገዢዎች የተላቀቀችውን አገራቸውን በነፃነት ዋዜማ የገለጹት እንዲህ በማለት ነበር። "Ghana got a flag and anthem in 1957. But, it didn't get real independence."

ጋናን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካውያንን የአስተሳሰብ ግዞተኝነት በተመለከተ ከልጀቿ ቁጭት ውጭ እጅግ የጠነከሩ የምጸት፣ የትችትና የማዋረድ አገላለጾች በምእራቡ ዓለም ጸሐፍት፣ ምሁራንና ተንታኞች እንደ ጉድ ሲዘንቡ እንደኖሩ በሚገባ ይታወቃል። "አፍሪካ ራሷን ከመለወጥ ይልቅ በታሪክ ኩራት ተለክፋ የኖረች አህጉር ነች - Africa is a continent to be history's permanent victim" የሚለው ገለጻ በብዙ የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል።

መሰል ገለጻዎችን በመደርደር አፍሪካን ማሰስም ሆነ ሩቅ ተጉዞ ማሳበብ ሳያስፈልግ የአገራችንን ጉዳይ ብቻ መፈተሹ በቂና ከበቂ በላይ ማስተማሪያ ሊሆን ይችላል። በተለይም ዛሬ የተዘፈቅንባቸውን አገራዊ ሁኔታዎችና ግራ አጋቢ ጉዳዮቻችንን ጫንና ጠንከር ብለን እንድንፈትሽ ግድ የሆነበት ወቅት ላይ የደረስን ይመስላል።

ፖለቲከኞቻችን በአዲስ አስተሳሰብና አመለካከት ተቃኝተው ራሳቸውን ከግዞተኝነት በማላቀቅ ነፃ እንዳይወጡ ዛሬም ተራራ የመውጣት ያህል ወኔያቸውና ጉልበታቸው ከድቷቸው ሲንፏቀቁ እያስተዋልን ነው። እንደ እኛ እንደ ኢትዮጵያውያን በግል አስተሳሰብ ለለውጥ ግትር በመሆን እኔነትን የሙጥኝ ብሎ የሚኖር ሌላ አገር ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ያዳግታል። አለ ከተባልንም ዝርዝሩ ይገለጽልንና ራሳችንን እየፈተሽን እንማርበታለን።

**ለምሳሌ፡-** የሶሻሊዝም ሥርዓት ሞቶና ተገንዞ መቃብር መውረዱ ተረጋግጦ እያለ እንኳን አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን መቃብሩን ቆፍረው በድኑን በማውጣት የአበባ ጉንጉን አንገቱ ላይ ሊያጠልቁ ሲያላዝኑ ስንመለከት "ይብላኝላችሁ!" ማለታችን አልቀረም። የሚያሳዝነው ነገር ይህ የአስተሳሰብ ግዞተኝነት የሚስተዋለው "ተቃዋሚ" በሚል ፍረጃ በተለዩት የፖለቲካው ቤተሰቦች ዘንድ ብቻም ሳይሆን አገር እመራለሁ የሚለው የገዢው ፓርቲ በርካታ ካድሬዎችም ዛሬም ድረስ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዐይነ ጥላ ሊገፈፍላቸው ስላልቻለ ሞቶ ለተቀበረው ውል አልባ ፍልስፍና ሙሾ አውራጆች ሆነው ሲያረግዱ መመልከት በእጅጉ ለትዝብት ይዳርጋል።

በሰፌድ ላይ እንደሚበጠር ጥሬ አገራችንን እያንቀረቀበ አሳሯን በማብላት ላይ የሚገኘውና ጥቂቶችን ብቻ ተጠቃሚ ያደረገውን የፅንፈኝነት ፖለቲካ "እንዳትነኩብን" በሚሉ የአስተሳሰብ ግዞተኞች አማካይነት አገሬ አሳሯን እየገፈገፈች ትገኛለች። ዓለም ባከበረው ታሪክ መስማማት ተስኖን፣ በየራሳችን ጎራ ፀጋችን በሆኑት ቋንቋዎችና ባህሎች ተከባብረን፣ ተደናንቀንና ተቀባብለን አብረን ከማደግ ይልቅ "የእኔ ካንተ ይሻላል፣ ከቅርቡ የጋራ ቅርሳችን ይልቅ የሩቁ ይበልጥብናል" እየተባባልን እንደ መመከቻ ጋሻና በጉራጌዎች አገላለጽ እንደ የወፎች ማስፈራሪያ "አውከሬ" በነተበ አስተሳሰብ ግዞተኝነትን መርጠን "ይዋጣልን!" እያልን መፋለም ጀግንነት ሳይሆን ድኩምነት ነው። የንጹሐን ደምን በማፍሰስ ጀግንነትን ለማሳየት መሞከርም ሽንፈት ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ቅጣት የሚያስከትል የእሳት ፍም በራስ ላይ ከመሸከም የሚተናነስ አይደለም።

በአስተሳሰብ ግዞት አእምሯቸውን ባጠሩ ጥቂት ቡድኖች ወይንም ጆብደኛ የዕለት ተዕለት ተግባር ግለሰብ ዜጎች በነፃነት ከቦታ ወደ ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ ማገድና መገደብ ስያሜ የሌለው የግፍ ድርጊት ነው። የአገራችን የአስተሳሰብ ግዞተኝነት ተኮትኩቶ የበቀለው በውጭ አካል ተጽእኖ ሳይሆን እኛው ራሳችን ዘርተን በማሳደጋችን መሆኑ ለክርክር አይጋብዝም።

የአስተሳሰብ ግዞተኝነት ከሌሎች ሰዎች እውቀትንና ጥበብን፣ በጎ ተሞክሮዎችንና ልምምዶችን ከመቅሰም ይልቅ በራስ አስተሳሰብ ታጥሮ መኖርን የሚያበረታታ አመለካከት ነው። የሌሎች መልካምና በጎ ሃሳብ ለግዞተኛ ሰው አይጥመውም። እርሱ ካለው ውጭ አንዳች ነቁጥ ተግባራዊ ከሚሆን ይልቅ "ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይመርጣል።

"እንደ ሰፈር በጠበበችው ዓላማችን እውቀት እንደ ንፋስ በተዘራበት ዘመን የአስተሳሰብ ግዞተኞች "ጎሬያቸው ውስጥ መሽገው" አናይም፣ አንሰማም፣ አናስተውልም ብለው መወሰናቸው መብታቸው ቢሆንም፤ የቆለፉበት አእምሯቸውና አስተሳሰባቸው ተፈትቶ ነፃ እስካልወጡ ድረስ ተገንዘው ሲቀበሩ የሚደረደርላቸው የሙሾ ግጥም "ተኖረና ተሞተ" እየተባለ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

እንደነዚህ ዓይነት የራስ አስተሳሰብ ግዞተኞችን አሊክ ሻሃዳድ የተባለ በመወለድ ጀርመናዊ፣ እድገቱ በካሪቢያን፣ ኑሮውን በአሜሪካና በእንግሊዝ ያደረገ የፓን አፍሪካ አቀንቃኝ ሙዚቀኛና የፊልም ባለሙያ ስለ አስተሳሰብ ግዞተኞች እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር።

"ጥማቸውን እንዲያረኩ ንጹሕ ውሃ በብርጭቆ ብትሰጧቸው እየዋኘን ካልሰመጥንበት ብለው ለያዥ ለገራዥ ያስቸግራሉ። እንደ ተራራ የገዘፈውን የራሳቸውን ችግር በአሸናፊነት እንዲወጡ የመወጣጫ "ገመድ" ብታቀብሏቸው ካልተሰቀልንበት ብለው ይወራጫሉ። " ለሰብእና ክብር ደንታ በሌላቸው ጉልበተኞችና "ዘመን ባገነናቸው ምን ግዴዎች" ተጽእኖ ሥር ወድቀው የአስተሳሰብ ግዞተኛ ሆኖ ከመኖር ይልቅ፤ አንድ ቀን ነፃ መውጣቴ አይቀርም እየተባለ ተስፋ በሚደረግበት አካላዊ ግዞት መቀጣት በብዙ ይሻላል። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

# ተናጋሪው ዶሴ

# ክፉ አባት የልጁ ገዳይ?

አስመረት ብስራት

ወላጆችን ወላጅ የሚያስብላቸው በመውለዳቸው ብቻ አይደለም። መውለድ አንዱ ጉዳይ ቢሆንም ወላጅ ለልጁ ሊያደርግ የሚገባውን አድርጎ ማሳደግ ደግሞ ግዴታ ጭምር ነው። ይህን የማያደርግ ወላጅ ግን እስከነተረቱ "የከብት እዳሪም .... ይወልዳል " ይባላል። ይሄ የሚባለው ወላጅ ወላጅ የሚሆነው ስለወለደ ብቻ ሳይሆን የወላጅነቱን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ሳይችል ሲቀር፣ ልጆቹን ለቁም ነገር ሳያበቃ ሲቀር፣ ሲያስርብ ሲያስጠማ፣... ነው። ለልጅ የሚያስፈልገውን ካላደረገ "ወላጅ" የሚለው በጥያቄ ውስጥ ይወድቃል። ወላጅ ወላጅ የሚሆነ ታዲያ ያፈሯቸውን ልጆች በወላጅ የኃላፊነት ስሜት፣ በስነምግባር ኮትኩቶ ማሳደግ ሲችል ነው። ለልጅ የሚያስፈልገውን በአቅሙ አሟልቶ ሲያሳድግ ነው። ልጅን በፍቅር ማሳደግ ሲቻል ነው። አባትን አባት የሚያደርገው ለሚወስደው ማንኛውም እርምጃ ኃላፊነትን የሚወስድ ሲሆን ነው። ለእናትም በተመሳሳይ።

አባትን አባት የሚያደርገው ራስ ወዳድ አለመሆኑ ነው። አባትነት መስጠት ማካፈል ነው። ለመስጠትና ለማካፈል አባት የፍቅር ሰው መሆን አለበት። ልጆቹን በትህትና ማገልገሉ ነው። አባትነት ዝም ብሎ የተሰጠ ስያሜም ተግባርም ሳይሆን የወላጅነት እድል ነው። አባት ልጆቹን በማገልገል መምራት ይገባዋል። ልጆቹን በትጋትና በታማኝነት መምራት አለበት። መንከባከብ፣ ማብላት ማጠጣት፣ ማልበስ ማስተማር ሁሉ የአባት ተግባር ወይም የውዴታ ግዳታም ነው። ልጅን በስነምግባር ማሳደግ፣ ለራሱም ለሀገርም ለወላጅም ልጅ እንዲሆን አድርጎ በእውቀት፣ በስነምግባር መቅረጽም ይጠበቅበታል። በድህነት ውስጥ ያለ ሰው ቢሆን እንኳን ለልጁ ፍቅር ሰጥቶ ከድህነት ለመውጣት የሚችልበትን መንገድ ማሳየት ይኖርበታል። በአንዳንድ አጋጣሚ የሚታየው ግን ልጅን ወላጅ መጠቀሚያ ሲያደርገው ነው። መለመኛ፣ በልጅ ጉልበት መነገድ ( ገንዘብ ማግኛ) ሲደረግ ነው። ይሄ እንደ ሰው አስተሳሰብም ሆነ በህግ የሚያስጠይቅ ነው።

አባትነት የ24 ሰዓት የ7 ቀን ኃላፊነት ነው። አባትነት መናገር ማስተማር ብቻ ሳይሆን መኖርን ይጠይቃል። አባት እንዲያውቁትና እንዲከተሉት ለልጆቹ ጊዜን መስጠት ይገባዋል። ልጆች ከንግግር በላይ ኑሮን ይኮርጃሉ። በአስተሳሰብ በአነጋገርና በድርጊት ለልጆች መልካም ምሳሌ መሆን ነው። አባትን አባት የሚያደርገው በትጋት ማሳደጉ ነው። እንዲሁም ማሳደግ ማስተማሩ፤ ማብላት ማጠጣቱ ብቻ ሳይሆን ጥፋቶችንም በሆደ ሰፊነት ማየትና ማረም መቻሉ ነው። ይቅርታና ምህረት ማድረጉ ነው። ሌላም ሌላም ማለት ይቻላል።

አባት ልጆቹን ለክፉት አሳልፎ የማይሰጥ፤ በተግዳሮት ለመከላከል ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሊሆን ይገባዋል። ችግር ወደ ልጆች ላይ ከሚመጣ አባት ራሱ ዋጥ የሚያደርገውና ቤተሰቡን የሚጠብቅ መሆንም አለበት። የነገሮችን አካሄድ በትጋት የሚከታተል አደጋን ከሩቅ የሚያይ ትጉህ ጠባቂ፣ ዋስ ጠበቃ ሊሆን ይገባዋል። ከጥቂቶች በስተቀርም አባት ያልነውን ሆኖ ነው የምናየው። አንዳንድ ጊዜ ግን እጅግ የማይጠበቅ አስደንጋጭና አስገራሚ ዜናዎችን እንሰማለን። አባት ልጁን ደፈረ አባት ልጁን ገደለ ... የሚሉ።

ሰሞኑን ከወደ ምዕራብ ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ ያገኘነው መረጃ ግን አባት ይህን ያደርጋል እንድንል አስገድዶናል። ከምዕራብ ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ ያገኘነው መረጃ እንደሚገልጸው፤ አባት ልጁን ምግብ ሳትሰሪ ጠበቅሽኝ ብሎ ደብድቦ መግደሉን ነው። ነገሩ እንዲህ ነው.....



### አባት.....ወይስ?

አባት አቶ አለፊ አዲሱ ገብሬ ይባላል። ከሰው ጋር ነገር አለሙ የማይገጥምለት ከዚህም ከዛም መናጨት የሚወድ አይነት ሰው ነው። ከልጅነቱ ጀምሮ ነጭናጫ ስለነበር “ አይፅዳሽ.....” በሚል ቅፅል ስም ነበር የሚጠራው። ምንም ነገር አስደስቶት አያውቅም። ከማንም ጋር መግባባት ስራ የሚሆንበት የአንድም ሰው ሀሳብ ከእሱ ሀሳብ ጋር የማይጣጣም ባህሪ ያለው ሰው ነበር። ለአቅመ አዳም እንደደረሰ እንደምንም ቤተሰቦቹ ሰው ፈለገው ሽማግሌ ልከው ቢድሩትም ትዳሩ በጭቅጭቅና በንትርክ የተሞላ ነበር።

አንዳንዴ እራሱም በማያውቀው ምክንያት ሚስቱ ላይ ሲጮህ ይገርመው ነበር። ለመግባባት የሚያደርጋቸው ሙከራዎች በሙሉ ይበልጥ የሚያጣሉት፤ የሚናገረው ነገር በሙሉ ለአድማጩ ጆሮ የማይመች፤ የትዳር አጋሩም “ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል እድሜ ልኩን ያለቅሳል” ነገር ሆኖ በመቻልና ባለመቻል መካከል ተውተርትራለች። በትዳር ሂደት ውስጥ መውለድ መክበድ የተለመደ ነውና አተካራው የማያጣው ቤት በሴት ልጅ ተባረከ። ልጅት የተወለደች ሰሞን ቤቱ ውስጥ የተፈጠረው ንትርክ እንደመቀዛቀዝ ብሎም ነበር። “ወዳጅ ዘመዱም ልጅ ሲወልደ ልብ ገዛ....” በማለት ደስታውን ገለፀ።

ያዳቆነው ሴይጣን ሳያቀስስ አይተውም እንዲሉ ከአምስት አመታት በኋላ ክፉ አመሉ አገረሸበት። ዳግም ንዝንዝና ጭቅጭቅ ተጀመረ። ከጭቅጭቁም ዘሎ ዱላ ተከተለ። ያኔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የወሰነችው ሚስት የአምስት አመት ልጇንና ባሏን አስተኝታ በጠፍ ጨረቃ ቤቱን ጥላ ዳግም ላትመለስ ተሰደደች።

ያኔ ነው እንግዲህ አባትና ልጅ በግላጭ የተዋወቁት። አቶ አለፊ አመሉ ስለከፋ ወዳጅ ዘመድ አይቀርበውም ነበር። የአምስት አመት ህፃን ሴት ልጁና እሱ ብቻቸውን መቅረታቸውን ተከትሎ ልጁን የሚበላ ለማቅመስ ከማጀት መግባት ግድ ሆኖበታል።

ግብርና ሲሄድ እንደ ወትሮው ምሳ አስሮ ለሚጠጣው ጉሽ ጠላን ሰንቆ የሚሄድለት ይቅርና አስከተሏት ግብርና ለሚሄደውን ህፃን ልጁን ኩርማን የሚመግብለት አጣ። ከልጅነት እስከ እውቀት እንኳን ማጀት ገብቶ ሊያበሰል የቀረበለትንም አቃቂር ሲያወጣ ነው የኖረው። እንደምንም እየታገለ ያለፋቸው አመታት ከባድ ፈተና ሆነበት አሳለፈ። በሕይወት ትግል ውስጥ አመት አመትን እየጨመረ ልጅቷም ከፍ ከፍ እያለች ሄደች።

ልጅት እንደጠነከረች የእማወራነትን ቦታ ተክታ ታገለገል ጀመር። በተቻላት አቅም ምግብ ሰርታ ለአባቷ ማቅመስ ጀመረች። ከአባቷ እየተደበቀችም ሄዳ የምትጠይቃቸው ዘመዶቿ የሚቆጣጥሩላትን ይዛ እየመጣች በወግ እህል መመገብ ጀመሩ። ማደግ አይቀርምና ልጅት እያደገች ስትሄድ ጉርምስና መጣ። ካልታዘዝኩኝ አልሰራም አይነት ነገርም ታሳይ ጀመረ። ከአባቷ ጋር የምታሳልፈው ሕይወት ምንም ደስታን የማይሰጥ እየሆነባት ከሱ የምትገላገልበትን ቀን መናፈቅ ጀመረች።

### ያልታሰበው የአባትና ልጅ ፀብ

የአባት የከረመ አመል የልጅ የጉርምስና ባህሪ አንድ ላይ ተደማምሮ አባትና ልጅ ምንም መግባባት አቅቷቸዋል። ልጅ አልታዘዝም ባይነት አመል አምጥታለች። አባትም እንዴት ብትደፍረኝ ነው በሚል ነጋ ጠባ ይነታረካሉ። በዚህ መካከል አንድ ቀን ፀባቸው ከረረ። አባት እርሻ ውሎ ሲመጣ ልጅቷ ከጓደኞቿ ጋር ፀጉራቸውን ሲሰራሩ ውለው ገና ቤት መድረሷ ነበር።

አባት በተቆጣ ድምፅ “ራቴን ወዲህ በይ” አላት።

ልጅም “ መች ሰርቼ..” አለች ፍርሃትና ደፍረት በተቀላቀሉበት ድምፅ።

አባት “ ለምነ ነው ያልሰራሽ ?” አላት ቁጣውን መቆጣጠር አቀቶት።

ልጅ “ መች አዘዝከኝና...” አለችው።

ያን ጊዜ ነው እንግዲህ ቁጣው ከቁጥጥር ውጭ የሆነበት አባት ለምን እራቴን /ምግብ አልሰራሽም በማለት ልጁን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ደብድቦ ዛሬ ለፀፀት የዳረገውን ጉዳት ያደረሰባት።

### የመጨረሻዋ ቀን

አቶ አለፊ አዲሱ ገብሬ የተባለ ተከሳሽ ነዋሪነቱ ቋራ ወረዳ ወርቂና ቀበሌ ሲሆን ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 3:00 አካባቢ ቋራ ወረዳ ወርቂና ቀበሌ ወንበልጌ ተብሎ ከሚጠራው ልዩ ቦታ ከመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ከ15 ዓመት ልጁ ጋር ከባድ ፀብ ውስጥ ይገባሉ። ከልጅቱ ጋር አንድ አንድ እየተባባለ የተካረረው ፀብ ባልታሰበ ሁኔታ ወደ ኃይል ጥቃት ይቀየራል።

አባትየው አንድያ ሴት ልጁን "ሳልጠይቅሽ ለምን እራቴን አዘጋጅተሽ አልጠበቅሽኝም?" በሚል ምክንያት እጇን እና እግሯን በሰንሰለት በማሰር በዱላ እና በሲባጎ በተደጋጋሚ ይደበደባታል። ድብደባውን መቋቋም ያቃታት ወጣትም ሕይወቷ ባልታሰበ ሁኔታ አባቷ እጅ ላይ ጠፋ።

የልጅቷን የድረሱልኝ ድምፅ ከርቀት የሰሙ ጎረቤቶችም ሰውየው አመለኛ ስለሆነ ሊገላግሉ ለመግባት ባይደፍሩም በአካባቢው ያገኙትን የፀጥታ ኃይል ጠርተው ቤቱን ያስከፍታሉ። ሰዓቱ ምሽት ቦታው ገጠራማ ስፍራ በመሆኑ ልጅት ጉዳት ሳይደርስባት መድረስ ሳይችሉ ይቀራሉ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ የማህበረሰቡን ጥቆማ ተከትሎ ሲደርስ አባት ልጁን የገደላት መሆኑን ይመለከታል። ገዳይን በቁጥጥር ስር አውሎ በሰውና በሰነድ ማስረጃ በማረጋገጥ የቋራ ወረዳ ፖሊስ ፅህፈት ቤት ምርመራ አጣርቶ ለምዕራብ ጎንደር ዞን ዐቃቤ ህግ መምሪያ መዝገቡን ልኳል።

የዞን ዐቃቤ ህግም የምርመራ መዝገቡ እንደደረሰው መዝገቡን በመመርመር ተከሳሹ የገዛ ልጁን ለምን ምግብ አላዘጋጀሽም በሚል ምክንያት በአሰቃቂ ሁኔታ ደብድቦ የገደላት በመሆኑ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 539 (1-ሀ) በመጥቀስ በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ክሰ መስርቶ ተከራክሯል።

ተከሳሹም ወንጀሉን አልፈፀምኩም በማለት ክዶ የተከራከረ ቢሆንም ዐቃቤ ህግ ምስክሮችን አስቀርቦ ያሰማ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ዐቃቤ ህግ እንደክሱ አመሰራረት ያስረዳ በመሆኑ ተከሳሹ የዐቃቤ ህግን ክስ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል።

### ውሳኔ

ተከሳሹም የመከላከያ ምስክር የለኝም በማለቱ የምዕራብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የጥፋተኝነት ፍርድ የሰጠ ሲሆን የዐቃቤ ህግንና የተከሳሹን የቅጣት አስተያየት ካዳመጠ በኋላ ዛሬ በቀን 12/07/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሹንና መሰል የወንጀል ድርጊት የሚፈፅሙ ግለሰቦችን ያርማል፣ ያስተምራል ያለውን የ18 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ወስኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# ስብሰባ(ሥልጠና) እና ስልክ

**ዋለልኝ አየለ**

የስብሰባ ዋና ዓላማ ምንድነው? ተብሎ ቢጠየቅ ያን ያህል ውስብስብና ሰፊ ማብራሪያ የሚጠይቅ አይመስለኝም። የስብሰባ ዋና ዓላማ በአንድ ጉዳይ ላይ በጋራ ለመወያየት የሚደረግ እና ለችግሮች መፍትሔ ለማስቀመጥ ነው። ሥልጠና ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ወይም የነበረ ሙያን ለማዳበር በባለሙያ የሚሰጥ ተጨማሪ ክህሎት ነው።

በዚህ ስብሰባ(ሥልጠና) ውስጥ ደግሞ መደማመጥና ሀሳብ መለዋወጥ የግድ ነው። ተሰብሳቢው ደንበኞች የሚስተናገድበትን ሥራ ዘግቶ ነው የመጣው። ምክንያቱም በስብሰባው ላይ ተወያይተው ለሆነ ጉዳይ መፍትሔ መምጣት ስላለበት ማለት ነው፤ ወይም በሥልጠናው ላይ ለሥራው የሚያግዝ ዘመኑንና ወቅቱን ያማከለ ተጨማሪ ክህሎት መያዝ ስላለበት ነው።

ታዲያ የስብሰባዎችን(ሥልጠናዎችን) ነገር ካየን በጣም ብዙ ነገር መታዘብ እንችላለን። ውድ የሆነው ሰዓትና የሰው ኃይል ይባክናል። በተሰብሳቢዎች ሰዓት ማርፈድ የሚባክነው ጊዜ እና ገባ ወጣ በማለት ሌሎችን መረበሽ የተለመዱ ናቸው።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ። በትልልቅ የስብሰባ አዳራሾች ውስጥ ‹‹ዋይ ፋይ›› ተገጥሟል። ይሄ ማለት እኮ ‹‹ስብሰባውን ተውትና ፌስቡክ ተጠቀሙ›› ማለት ነው። ይሄ የሚሆነው በትልልቅ የስብሰባ ቦታዎች ላይ ነው፤ ዓለም አቀፍ ጉዳይ በሚወራባቸው ስብሰባዎች ላይ ጭምር ነው። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ግን(ለምሳሌ ስካይላይት ሆቴል) ስብሰባው እስከሚያልቅ ነው ተብሎ ዋይ ፋይ እንዳይሰራ ተደርጎ አይቻለሁ።

በብዙ ቦታዎች ግን ገና ወደ አዳራሹ እንደገባችሁ የቤቱ የዋይፋይ የምስጢር ቁጥር ከፊት ለፊት ይለጠፋል። ይሄኔ እንግዲህ ሌላ ቦታ ‹‹ኮኔክሽን›› ሲያስቸግረው የነበረ ሁሉ ጥሙን የሚወጣው እዚያ ነው። ከኢንተርኔት ማውረድ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያወርደው የዚያን ዕለት ነው። በዚያ ላይ ነጻ ስለሆነ ሳንቲም አለመቁረጡም ሌላው ቀልብ ሳቢ ነገር ነው። እዚህ ስብሰባ ውስጥ ያለ ሰው ጆሮውን ቢቆርጡት አይሰማም፤ ሌላ ዓለም ውስጥ ነው ያለው።

ስብሰባ ውስጥ ‹‹ዋይ ፋይ›› የሚያስፈልግበት አጋጣሚ እንዳለ አምናለሁ፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የግዴታ የሚሆንበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ ሥልጠናው ‹‹ሳይበር›› ነክ ነገር ከሆነ ሁሉም ኢንተርኔት እየተጠቀሙ ነው ልምምዱ የሚደረገው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በሌሎች ሥልጠናዎችና ስብሰባዎች ውስጥም ዘመኑ የፈቀደው ነውና ነገሮችን ለማረጋገጥ ወደ ኢንተርኔት ጎራ ማለት የግድ ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ስብሰባዎች በተባለላቸው ሰዓት ተካሂደው አያውቁም፤ ቀድሞ የደረሰ ሰው የሚደርስበትን መጉላላት አስቡት! ስለዚህ ይሄ ሰው በነጻ ኢንተርኔት መካስ አለበት። የባከነውን ሰዓቱን ቢያንስ በማንበብ ሊጠቀምበት ይገባል።

ትዝብቴ ዋይ ፋይ ስብሰባ ቦታ ውስጥ ሙሉ በሙሉ አያስፈልግም ሳይሆን አጠቃቀሙ ግን አልታወቀበትም፤ ወይም የሆነ ሌላ ዘዴ ሊፈጠርለት ይገባል ነው። ለምሳሌ፤ ስብሰባው ሲጀመር የዋይ ፋይ አገልግሎት መቋረጥ አለበት፤ ወይም ሌላ የክልከላ ዘዴ መኖር አለበት። ይህ ካልሆነ ስብሰባው እየተካሄደ ያለው ለመርሃ ግብርና ለሪፖርት ብቻ ነው ማለት ነው። መድረክ መሪውም ማንም እንደማይሰማው እያወቀ ከሆነ የሚያወራ እሱም የይውጣልኝ ነው እየሰራ ያለው። እዚያ ላይ እኮ አገራዊ ጉዳይ ነው እየተወራ ያለው። መድረክ ላይ ምን እንደቀረበ ያልሰማ ተሳታፊ ምን ብሎ አስተያየት ሊሰጥ ይችላል?

ያለመደማመጥ ነገር ቀላል ችግር አይደለም። ሳይሰሙ የሚናገሩ ይኖራሉ። መድረክ መሪው ‹‹እባካችሁ የተነሳ ሀሳብ አትድገሙ›› እያለ ደጋግሞ ይናገራል፤ እሱን ራሱ ማን ሰምቶት። መድረክ መሪው ባስ ሲልበት ተናጋሪውን በማቋረጥ ‹‹እሱ ሀሳብ ተነስቷል›› ሲለው ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ‹‹ቆይ ልጨርስ›› እያለ ሌላ ሰው የተናገረውን ሁሉ ደግሞ ይናገራል። እንግዲህ አስቡት በጥሞና ያላዳመጠ ሁሉ ሲናገር ሀሳቦች እጥፍ እጥፍ ሊደገሙ ነው ማለት ነው።

በአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ የታዘብኩትን ልጥቀስ። ስብሰባው ዓለም አቀፍ ስብሰባ ነው። በየጠረጴዛው ላይ ላፕቶፕ ተቀምጧል። መጀመሪያ ሳየው ለስብሰባው የግድ አስፈላጊ የሆነ ነገር ነበር የመሰለኝ። በኋላ ውይይቱ ሲጀመር ሳይ ግን የሚጠቀሙት ነገር ከስብሰባው ጋር ምንም የሚገናኝ አይደለም። አንዳንዱ ፌስቡክ ይጠቀማል፤ አንዳንዱ ቪዲዮ ያየል፣ አንዳንዱ ሌላ ጽሑፍ ያነባል፤ መድረክ ላይ የሚባለውን ነገር የሚሰማው ከፊቱ ላፕቶፕ የሌለ ሰው ብቻ ነበር። ላፕቶፕ ከሌላቸው ሰዎች ውስጥም በራሱ ስልክ የሚጠቀመው ቀላል አይደለም።

ሌላው የዋይፋይ ትዝብቴ ደግሞ ጋዜጠኞች ላይ የማየው ነው። አንድ ጋዜጠኛ ሊዘግብ የሄደበትን ጉዳይ በጥሞና ነው መከታተል ያለበት። ምናልባት እሱ የፈለገው የራሱ አንግል ይኖረው ይሆናል። ምንም ይሁን ምን ግን ስብሰባው ላይ የተባለውን ነገር ሳይሰማ የራሱን ጥያቄ እንኳን መጠየቅ አይችልም። ያ የሚያናግረው ሰው እንኳን ‹‹ውይይቱ ላይ እንደሰማኸው…›› እያለ ነው የሚያወራ። ይሄኔ ጋዜጠኛው የተባለውን አልሰማም። ለዚህ እኮ ነው ጋዜጠኞች ጥያቄ ሲጠይቁ ‹‹የዛሬው ስብሰባ ስለምንድን ነበር›› ብለው የሚጀምሩት።

የዋይፋይ ነገር ቦታ ሊመረጥለት ይገባል። አንድ ስብሰባ የጋራ መደማመጥ ከሌለበት ለምንድነው ጊዜ የሚባክነው? ምን ጊዜ ብቻ ያ ሰብሰባ እኮ ብዙ ብር ወጪ የተደረገበት ነው። ስለዚህ ለውይይት የሚጠራው ሰው የማይከታተለው ከሆነ ብክነት ብቻ ነው የሚሆነው።

አከራካሪው ነገር ‹‹እንዴት ትልልቅ የስብሰባ ቦታ ላይ ዋይ ፋይ ይጥፋ! ይባላል›› የሚል ነው። እርግጥ ነው ዋይ ፋዩ በራሱ እኮ ችግር የለበትም። እሱ የተሰራበትን አገልግሎት እየሰጠ ነው። እኛ ግን አጠቃቀሙን ካልቻልንበት ያለው አማራጭ አለመኖሩ ሊሆን ነው። አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ያገልግል እንጂ ለመረባበሽማ መሆን የለበትም።

አንዳንድ ጊዜ አስቂኝ ነገር ሁሉ ይፈጠራል። የሆነ የድምጽ ብልጫ የሚያስፈልገው ነገር ካለ እጅ እንዲያወጡ ይቀሰቀሳሉ። የምርጫ ሀሳቡ ሲሰጥ ለየትኛው ሀሳብ ያውጡ? ከደጋፊውና ከተቃዋሚው ይልቅ ድምጸ ተዓቅቦ የሚባለው ይበልጣል ማለት ነው። ይሄ የሆነው እንግዲህ ምን እንደሆነ ስላልገባው ነው። በዘፈቀደ ካወጣም የሚፈጠረውን መጭበርበር አስቡት። እናም ወይ አጠቃቀማችን ይስተካከል ካልሆነ በስብሰባ ቦታ ውስጥ ዋይ ፋይ ገደብ ይኑረው!

በጣም እየከፋ የመጣው ችግር ደግሞ ስልክ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የእጅ ስልክ መጠቀም ከተጀመረ ከ20 ዓመት በላይ ሆኖታል። በዚህ ዘመን ‹‹የተማረ›› የሚባለው ሰው በትንሹ ከ10 ዓመት በላይ የእጅ ስልክ የያዘ ነው። ሰው እንዴት ይህን ያልህ ዓመታት አሁንም ብርቅ ይሆንበታል? ስልክ አጥፉ ወይም ደምጹን ፀጥታ(ሳይለንት) ላይ አድርጉ እየተባለ የሚሰማ የለም።

በነገራችን ላይ አንዳንድ የሥራና የሙያ አይነቶች ጭራሹንም ስልክ የማይያዝባቸው አሉ፤ እኛ ግን ለሰዓታት እንኳን መለየት እየቸገረን ነው። ጥሩ ማብራሪያ እየተሰጠ እያለ ድንገት የአንዱ ስልክ ያንባርቃል። ሊያናግር ወደ ውጭ ይወጣል። በር ይዘጋል ይከፍታል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ታዳሚው እየተረበሸ ነው።

ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ አሁንም ስለእጅ ስልክ አጠቃቀም መተዛዘብ ሌላ ትዝብት ነው!

## ዓለም አቀፍ



# አሜሪካ እና ካናዳ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ሳስመቀበል ተስማሙ

አሜሪካ እና ካናዳ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ደንበሮቻቸውን አቋርጠው የሚገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ላለመቀበል ከስምምነት መድረሳቸውን መሪዎቻቸው ገለጹ። ስምምነቱን የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን እና የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ፣ ባይደን ጉብኝት በሚያደርጉባት የካናዳዋ ኦታዋ ከተማ ዛሬ ይፋ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል።

ይህ ስምምነት በሁለቱም አራት በኩል ያሉ ባለሥልጣናት ወደ አሜሪካ ወይም ወደ ካናዳ ለመግባት ድንበር የሚያቋርጡ ሰዎችን ወደመጡበት እንዲመልሱ የማድረግ ሥልጣን የሚሰጥ ነው። አሜሪካ በካናዳ በኩል የሚያዋስናትን ድንበር አቋርጠው ወደ አገሯ የሚገቡ ፍልሰተኞች ቁጥር አሻቅቧል። ይህ ስምምነት እየጨመረ የመጣው እና ሮክሳም በተባለው መንገድ ከካናዳዋ ኪውቤክ ግዛት ወደ ኒውዮርክ ግዛት የሚፈልሱ ስደተኞችን ቁጥር ለመገደብ እየተደረገ ያለው ጥረት አካል ነው።


በስምምነቱ መሠረት ካናዳ ከደቡብ እና ከማዕከላዊ አሜሪካ ግጭት እና ጥቃትን የሚሸሹ 15 ሺህ ስደተኞችን የምትቀበልበት አዲስ መርሃ ግብር እንደሚዘረጋ አንድ በስም ያልተጠቀሱ ባለሥልጣን በአሜሪካ የቢቢሲ አጋር ለሆነው ሲቢኤስ ኒውስ ተናግረዋል። ባይደን በካናዳ ኦታዋ በኢኮኖሚ፣ በንግድ እና በስደት ጉዳይ ከትሩዶ ጋር ለመምከር ለ24 ሰዓት የሚቆይ ጉብኝት እያደረጉ ሲሆን፣ የፍልሰተኞች ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥነው ስምምነት ፕሬዝዳንቱ ወደ አገራቸው ከመመለሳቸው በፊት ይፋ ይሆናል።

ሁለቱ አገራት የደረሱበት ይህ አዲስ ስምምነት እንደ አውሮፓውያኑ በ2004 የነበራቸውን ስምምነት ያሻሻለ ነው። ይህ ስምምነት ስደተኞች አሜሪካ ወይም ካናዳ ከመግባታቸው ቀድመው በሌላ "ደኅንነቱ በተጠበቀ" ሦስተኛ አገር ጥገኝነት እንዲጠይቁ የሚመራ ነው። አዲሱ ስምምነት ከቀድሞው በተለየ ካናዳ ይፋዊ ባልሆነ ድንበር የሚያቋርጡ ስደተኞችን እንድትመለስ የሚያስችል ነው።

የቀደመው ስምምነት ፍልሰተኞች ወደ ካናዳ እንዲገቡ የሚያደርግ ነው። አገራቱ እዚህ ስምምነት ላይ ለመድረስ ወራትን የፈጀ ድርድር ማድረጋቸውንም ሪፖርቶች አመልክተዋል። የፕሬዝዳንት ባይደን አስተዳደር በአሜሪካ ደቡባዊ ድንበር ከሜክሲኮ አቋርጠው የሚገቡ ሰዎች ጥገኝነት ለመጠየቅ የሚሄዱበትን መንገድ አስቸጋሪ የሚያደርግ አዲስ ዕቅድ አዘጋጅቷል። ይህ ዕቅድ ከሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ነቀፌታ ገጥሞታል።

ይህ በአሜሪካ እና በካናዳ መካከል የተደረሰው ስምምነት በአሜሪካ ኮንግረስ በኩል አልፎ መጽደቅ ሳያስፈልገው በፍጥነት የሚተገበር መሆኑን ቢቢሲ ዘገባ አመልክቷል።

# የናይጄሪያ የምክር ቤት አባል የሰው ኩላሊት ስልጃቸው በመግዛት ወንጀል ጥፋተኛ ተባሉ



ሴናተር ኢኬ ኢኬዌረማዱ

አንድ የናይጄሪያ ባለሀብት እና የምክር ቤት አባል የሆኑ ግለሰብ እንዲሁም ባለቤታቸው የሰውን አካል በመግዛት ወንጀል ጥፋተኛ ተባሉ። ሴናተር ኢኬ ኢኬዌረማዱ እና ባለቤታቸው ቢያትሪስ ይህን ወንጀል ሲፈጽሙ የነበረው ኦቢና ኦቤታ ከተባለ አንድ የሕክምና ዶክተር ጋር በመመሳጠር ነበር።

ሦስቱ የወንጀል ጥምረት የፈጠሩት ግለሰቦች አንድን የ21 ዓመት ወጣት ከሌጎስ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም (ዩኬ) በማሻገር አዲስ ሕይወት ትጀምራለህ በሚል ተስፋ ኩላሊቱን በንቅለ ተከላ ለልጃቸው ለማስተላለፍ መመሳጠራቸው ተደርሶበታል። የገዛ ኩላሊቱ ሊሸጥበት የነበረው ወጣት የጎዳና ንግድ ላይ የተሰማራ ናይጄሪያዊ ሲሆን፣ ወደ ዩኬ የተወሰደው 80ሺህ ፓውንድ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች እንደሚሰጡት ቃል ተገብቶለት ነው።

ይሁንና ኩላሊት ሊወሰድበት እንደሆነ አልተብራራለትም ተብሏል። ኩላሊት ሊሰጣት የነበረችው ሴት የ25 ዓመቷ ሶንያ ስትሆን፣ የእኚህ የምክር ቤት አባል እና ባለሀብት ሴት ልጅ ናት። የምትኖረውም በዳያለሲስ ነው። የኩላሊት ንቅለ ተከላው ሊደረግ የነበረው በለንደን የሮያል ፍሪ ሆስፒታል ውስጥ ነበር።

በሌጎስ የጎዳና ላይ ንግድ ላይ የነበረው ወጣት ስለ ኩላሊቱ ንቅለ ተከላ ምንም ዓይነት መረጃ ሳይሰጠው በመቅረቱ ሆስፒታል ውስጥ ሲደነጋገር ነበር ተብሏል። ወደ ለንደን ተወስደህ አዲስ ሕይወት ትጀምራለህ የተባለው ወጣት ለጊዜው ቃል የተገባለት 7ሺህ ፓውንድ ተሰጥቶት ነበር። ወጣቱ የገዛ ኩላሊቱ ሊወሰድበት እንደሆነ ያወቀው ግን ሆስፒታል ከሐኪም ጋር ሲገናኝ ነበር።

እኚህ የምክር ቤት አባል ግን ግለሰቡ የልጃቸው የሶኒያ የአክስት ልጅ እንደሆነ ሐኪሞቹን ለማሳመን ጥረት አድርገዋል ተብሏል። ምን እንደተደገሰለት ያለወቀውን ወጣት ለማሳመን በእርሱ እና በሐኪሞቹ መካከል የቆሙ አስተርጓሚዎች ከፍተኛ ገንዘብ ተከፍሏቸውም ነበር ተብሏል። ይሁንና ሐኪሞች የወጣቱ ሁኔታ ጥርጣሬን ፈጥሮባቸዋል።

በዩኬ ምንም እንኳ ኩላሊትን በፈቃደኝነት መለገስ ሕጋዊ አሠራር ቢሆንም በገንዘብ የሰውን አካል መግዛትና መሸጥ ግን ከባድ ወንጀል ነው። በዕለቱ የሮያል ፍሪ ሆስፒታል ሐኪም ዶ/ር ፒተር ደፖንት ግለሰቡ ለንቅለ ተከላው ዝግጁ እንዳልሆነ በመረዳታቸው ቀዶ ጥገናው እንዲዘገይ ወስነዋል።

ወጣቱ ከዚህ በኋላ ከሆስፒታል ሮጦ አምልጦ ለሦስት ቀናት በለንደን ጎዳና ላይ እያደረ ቆይቶ በመጨረሻ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ደርሶ እያለቀሰ ሁኔታውን በመንገሩ ነው ወንጀሉ ሊደረስበት የቻለው። ይህንን የወንጀል ድርጊት በዩኬ ውስጥ የተመለከተው ችሎት በዘመናዊ ባርነት ሕግ (modern slavery act) ሦስቱን ግለሰቦች ጥፋተኛ ብሏቸዋል።

ኩላሊት ሊሰጣት የነበረችው ሶኒያ ኡኬሩዎማዱ ከወንጀል ነጻ በተባለችበት ቅጽበት፣ ወንጀለኛ የተባሉትን አባቷን አቅፋ አምርራ ስታለቅስ ታይታለች። ይህን ወንጀል ያቀነባበረው ዶ/ር ኦቢና ኦቤታም ጥፋተኛ ተብሏል። ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ሥር የዋሉት ለተመሳሳይ ንቅለ ተከላ ቱርክ ተጉዘው ሲመለሱ ነው።

ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት በዐቃቤ ሕግ የቀረቡለትን ተጠርጣሪዎቹ በዋትስአፕ ሲለዋወጧቸው የነበሩ የአጭር የጽሑፍ መልዕክቶችን መርምሯል። ጥፋተኛ የተባሉት ሦስቱ ግለሰቦች የእስር ብይን በግንቦት ወር ይጠበቃል።

በዚህ የሰው ሰውነት ንግድ የተሳተፉ ሰዎች በዚህ በዩኬ ታሪክ የመጀመሪያ ነው በተባለው የዘመናዊ ባርነት ወንጀል ሲዳኙ የመጀመሪያዎቹ ሲሆኑ፣ ፍርድ ቤት እስከ ዕድሜ ልክ ሊፈረድባቸው ይችላል መባሉን ቢቢሲ ዘግቧል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ደን + መና= ደመና

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ያለነው የካቲት በወጣበት፣ በልግ በባተበት እና መጋቢት በተጋመሰበት ወቅት ነው። የካቲት መከተት መሰብሰብ ማለት ነው። ገበሬው አዝመራውን ወቅቶ ጎተራ ውስጥ የሚከትበት፣ ገለባውን ሰብስቦ የሚከምርበት ወር ነው። ሞፈርና ቀንበሩን ወልውሎ ማረሻውን ስሎ፤ ለበልግ አዝመራ መሰናዶም የሚጀምርበት። ለዚህ ነው የካቲት የመከር (በጋ) መካተቻ የበልግ መባቻ የሚባለው። በየካቲት ዜጋው ሁሉ ልዩነቱን ትቶ ለሀገሩ ከቶ፣ ዘምቶ በዓድዋ ድል አድርጎ ታሪካዊ ገድል የፈጸመበትም ነው። ጣልያን ሀገሪቱን ስትወር ‹‹ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት›› ሲባል ሁሉም ለሀገሩ፣ ለድንበሩ፣ ለክብሩ በአንድነት ተዋደቀ፤ በቅኝ ለሚገዙ ሀገሮች ምሳሌ ሆነ።

ወደ መጋቢት ስንመጣ ገበሬው የመግቦት ወር ይላታል። በሬውና ገበሬው ከእርሻው የተወሰነ እረፍት ወስደው የሚመገቡባት ጊዜ ስለሆነች ነው የመግቦት ወር የሚሉት። የበልግ ወይም የጸደይ ወቅት የመጀመሪያ ወር ናት። ቀንና ሌሊቱ እኩል ሰዓት የሚሆንበትም ጊዜ ነው። መጋቢት የበልግ መግቢያ የበጋ ማብቂያ ናት። እናም በበጋ ፀሐይ ደርቃ የነበረች መሬት በጸደይ ዝናብ የምትረሰርስበት፣ የመስኖ እርሻ አትክልቶች በብዛት የሚታዩበት፣ የከብትና ጭድ መዋደድ የሚፀናበት፣ በጸደይ ዝናብ የሚበቅሉ እህሎች የሚዘሩበት ነው። ለበልግ አብቃይ አካባቢዎች የፍሬ የልምላሜ ወቅት ነው። በቆሎ ተዘርቶ ለምርት የሚደርስበትም ነው። በዕውቀቱ ስዩም በሚያዝያ በብዛት በመዲናዋ የሚታየውን በቆሎ ሲገልጸው፤ በየመንገዱ በብዛት በከሰል በቆሎ ስለሚጠበስ መዲናዋ በአንዴ ከመዲናነት ወደ ማድቤትነት ትቀየራለች ብሎ ነበር። ይህም የበቆሎ ጋጋታ የመጋቢት ውጤት መሆኑ ነው።

የከሳቴ ብርሃን የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደን፡ - ብዙ ደንን፣ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ዛፍ የበዛበት ዱር በሚል ይፈታዋል። ደን ለአካባቢ ጥበቃ ሁነኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው። ሞቃታማ ቦታዎች ደን ሲተከልባቸው መልከዓ ምድሮች ለሰው ልጆች ምቹ ይሆናሉ። ዛፎች በበዙበት ንጹህ አየር ይገኛሉ። ንጹህ ውሃም ይመነጫል። በተለይ ዕድሜ ጠገብ ዛፎች ከሥራቸው ውሃ በመሳብ ምንጭ ያመነጫሉ፡ የዱር እንስሶችና ወፎች መጠለያና ምግብ ያገኛሉ፤ የአፈር መሸርሸርን መከላከል የሚቻለው ዛፎችን በመትከል ነው፤ በአጠቃላይ ስነ ምህዳሩ ተስማሚ የሚሆነው ደን ሲኖር ነው።

መና የሚለውን ቃል ደግሞ እሥራኤል አርባ ዓመት ከሰማይ እየወረደ የተመገቡት ምግብ ነው። በዕብራይስጥ መና፣ በግዕዝ መኑ፣ በአማርኛ ምን እንደሚለው ማለት ነው ይለዋል። በተጨማሪም መና፡- ኅብስተ መና ሲባል በጣም የነጣ የጥሩ ስንዴ ዳቦ ማለት ነው። በምሳሌያዊ ብሂልም ‹‹አንተ ቀውላላ መኖህ ባቄላ›› ሲባል ቀውላላ የሚለውን ትተነው መኖህ ባቄላ ሲል ምግብህ ባቄላ መሆኑ ይታወቃል። በአንፃሩ ‹መና ሆነ› ሲባል ደግሞ ባክኖ፣ መክኖ ከንቱ ሆኖ ቀረ ማለት መሆኑን መዝገበ ቃላቱ ይፈታዋል።

የከብቶች መኖ የሚለውንም ቃል እዚህ ውስጥ ብንከተው የከብቶች ምግብ መሆኑ እሙን ነው። ልዩነቱ ከብቶች ቅጠላ ቅጠል፣ ሣርና ገለባ ሲበሉ፤ የሰው ልጅ ጥራጥሬና፣ ፍራፍሬ ይበላል። ከብቶች ከሰው ልጅ የተረፈውን አልያም ሰው የማይበላውን ሣርና ገለባ ይበላሉ ለዚያ ነው ምግባቸው መኖ የተባለው። ወደ አፋን ኦሮሞ ስንሄድ መኖሪያ ቤት መና ይባላል። መና (ቤት) የምንበላት፣ የምንጠለልበት፤ የእኛንም የእንስሶችንም መኖ የምናከማችበት ነው። በፈረንጆቹም መኒ ብር ማለት ነው። ገንዘብ ደግሞ መኖ (ምግብ) ይገዛል።

ደመና የሚለውን ቃል እንደ ማግ ንድፍ አይነት ኹኖ በሕዋ ተረግርጎ እንደ ጋራም ከፍ በማለት ተስፋፍቶ የሚታይ ክምር ነው ሲል መዝገበ ቃላቱ ያስረዳል። ደመና በጣም ጠቁሮ፣ አደምድሞ ከብዶ ሲመጣ ከባድ ዝናብ ሊሆን



ይችላል። በርግጥም ደመና ሲሆን ሰማዩ ሲጠቁር ዝናም ሊመጣ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ።

በርዕሳችን ደን ሲደመር መና፣ ደመና ነው ያልነው፤ ደን ሲተከል ለሰዎች፣ ለቤትና ለዱር እንስሳት፣ ለአዕዋፋት ለነፍሳት፤ ምግብ መጠለያ ይሆናል። በቀጥታ መና ከሰማይ ባይወርድም ከምድር የተነነው አየር ወደ ሰማይ ወጥቶ በደመና ዝናብ ሆኖ ይወርዳል። ዝናቡ ደግሞ ዕጽዋት አዝዕርት እንዲበቅሉ ሚና አለው። የበቀለው አዝዕርት አትክልትና ዕጽዋት የተወሰኑ ፍጥረታት ይመገቡታል፣ ይጠለሉበታል፣ የሚጠጣ ውሃ ያገኙበታል። ደመናው በተዘዋዋሪ መና ሆኖ ወረደ ማለት ነው። ከደመናው በወረደ ዝናብ ደግሞ ገበሬው በሬውን ጠምዶ፣ መሬቱን አርሶ ዘሩን ይዘራበታል። ስለዚህ መና ወይም ምግብ ያገኝበታል። ‹‹በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ ›› የሚመግበውን አምላክ ያመሰግንበታል።

በበልግና በክረምት ደመና የተስፋ ምልክት ነው። ገበሬዎች ደመናውን ከሰማይ ሲያዩ ዝናብ መጣልን ብለው በተስፋ ይሞላሉ። ድርቅ የነበረባቸው እንደ ቦረና የመሳሰሉ አካባቢዎች በያዝነው በዚህ በበልግ ወቅት የዘነበው ዝናብ ለቀጣዩ ጊዜ በድርቅ ለተጎዱት ወገኖችና ለዜጎች ሁሉ ብሩኅ ተስፋን ያቀዳጀ ነው። በመጠጥ ውሃና በሚጋጥ ሣር ተጎድተው ለነበሩ ከብቶች ሕይወታቸው እንዲያገግም ይረዳል። ከብቶቻቸው ውሃውን እየተጎነጩ ሣሩን እየነጩ እንዲፈነጩ ብሎም እንዲያገግሙና እንዲደልቡ የሚረዳ ተስፋ የሚያጭር ነው። ዝናብ ዘነበ ማለት መጪው ጊዜ ብሩኅ ነው እንደ ማለት ነው፡

በዱር የሚኖሩ እንስሳትና አራዊት የሚበሉትን የሚጠጡትን እንደልብ የሚያገኙት ደመና ዝናብ ሆኖ ሲወርድ ነው። በዝናብ የበቀለው ቅጠላ ቅጠልና፣ ሣር፣ እጽዋት፣ እየጋጡ የወንዝ ውሃ እየጠጡ በየዱሩና በየሜዳው ይቦርቃሉ። ሥጋ በል አራዊቶች ደግሞ እንስሳቱን አድነው ስጋቸውን ይበላሉ። እናም ደመና ለሁሉ መና ሆነ ማለት ነው።

እዚህ ላይ ለጽሁፋችን ጋር የሚጣጣም ግጥም ከደራሲ ከበደ ሚካኤል ቀንጭበን ወሰድን። ርዕሱ ጽጌረዳና-ደመና ይሰኛል።

የፀሐዩ ንዳድ ያጠቃት በብዙ
ጠውልጎ የሚታይ የቅጠልዋ ወዙ።
አንዲት ጽጌረዳ ቃልዋን አስተዛዝና፣
እንዲህ ተናገረች ለሰማይ ደመና።
ድርቀት በጣም ጎድቶኝ እየኝ ስንገላታ ...
እባክህ ጣልልኝ የዝናብ ጠብታ፣
ቶሎ ከላረስከኝ ጉልበቴ እንዲጥናና
ምንም ተስፋ የለኝ መሞቴ ነውና። . . .

**ስለደመና ስናወራ በደመና ዝናብ የማዝነብ ቴክኖሎጂ በተለያዩ ሀገሮች ይተገበራል። ባለፈው ዓመትም በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ደመና ማዝነብን ቴክኖሎጂ ተጠቅማ ነበር። ነገሩ ተስፋ ሰጪ ይመስላል። በአረንጓዴው አሻራ የተጀመረውን የደን ሽፋን ማሳደግም ተፈጥሯዊውን ደመና የማበልጸግ አቅማችንን ያጠናክርልናል። በዚህ ደግሞ የበለጠ ደመና በደመና ሆነን ጠግበን ለማደር እንችላለን**

መጽሐፍ ቅዱስም ደመናትም ጠልን ያንጠበጥባሉ ይላል። . . . የንጉሥ ፊት ሲፈካ ሕይወት አለ፤ በጎነቱም ዝናብ እንዳዘለ የበልግ ደመና ነው። ኤፍሬም ሶሪያዊም በውዳሴ ማርያም ‹‹አንቲ ዘበአማን ደመና እንተ አስተርአየኪ ለነ ማየ ዝናም፤ የዝናብ ውኃን ያስገነሸልን እውነተኛ ደመና አንቺ ነሽ›› ይላል። የጠቀስናቸው መጽሐፎች ከሳይንሱም በፊት ደመና ከምድር ወደ ሰማይ ተኖ ዝናብን ተሸክሞ ወደ ምድር እንደሚወርድ ያስረዳሉ። በፈሊጣዊ አነጋገርም ደመናው ገፈፈ ሲባል ደመናው ጠፋ፣ ደመናው ተሾመ ሲባል ደመናው በአየሩ ላይ ተንሳፏል፤ ሊዘንብ ሳይሆን አይቀርም። ደመናው ተጠንስሷል ሲባልም ሊዘንብ ነው ማለት ነው።

ስለደመና ስናወራ በደመና ዝናብ የማዝነብ ቴክኖሎጂ በተለያዩ ሀገሮች ይተገበራል። ባለፈው ዓመትም በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ደመና ማዝነብን ቴክኖሎጂ ተጠቅማ ነበር። ነገሩ ተስፋ ሰጪ ይመስላል። በአረንጓዴው አሻራ የተጀመረውን የደን ሽፋን ማሳደግም ተፈጥሯዊውን ደመና የማበልጻግ አቅማችንን ያጠናክርልናል። በዚህ ደግሞ የበለጠ ደመና በደመና ሆነን ጠግበን ለማደር እንችላለን።

የግሪካዊውን ፈላስፋ ታሊስ እሳቤ ላክልበት። የፍጥረት ሁሉ መሠረት ውሃ ነው ይልና ሲያብራራ (በነገራችን ላይ በአሮሞ ዋቄፈናም የፍጥረት ሁሉ መሠረት ውሃ ነው ይባላል) ውሃ ሲፈላ እየተነነ ወደ ላይ ሄዶ ዳመና ይሆናል። ወደ ውሃ ተለውጦም ይዘንባል፤ ውሃ ሲጠጥር በረዶ ይሆናል፤ በረዶ የበለጠ ሲጠጥር አፈር ይሆናል፤ አፈር የበለጠ ሲጠጥር ድንጋይ ይሆናል፤ የሁሉ መሠረቱ ግን ውሃ ነው ይለናል።

በገጠራማ አካባቢዎች መሬት የደረሰ ደመና ማየት የተለመደ ነው። መሬት የረገጠ ደመና ጭጋግ ይባላል። ጭጋግ የሳሳ ሲሆን የተወሰነ ርቀት ማየት ያስችላል። ጭጋጉ ጥቅጥቅ ብሎ ሲገኝ አጠገቡ ያለውን ሰው በቅጡ የማያሳይበት ጊዜም ይኖራል። በዚህ ጊዜ አውሬዎችም ከጫካቸው የሚወጡበት አጋጣሚ እንዳለ ሰዎች ይናገራሉ። ስለዚህ ሰው መንገዱን ተጠንቅቆ መራመድ አለበት፤ ጭጋጉ ለጨለማ የሚቀርብ በመሆኑ ለመንገዱ ባትሪ መያዝም ሊያሻው ይችላል።

ደመና ሰማዩ ጥቁር ሆኖ ሲሸፍን ዝናቡን ከልሎ ወደ ምድር ሊወርድ እንደሆነ ሰዎች በልምድ ደመናውን አይተው ያውቃሉ። ከላይ እንደጠቀስነው አንዳንድ ጊዜ ጥቅጥቅ ያለ ጉም መሬቱን ሸፍኖ ሰዎች መንገድ ይቸገራሉ። በከተሞች ተሽከርካሪዎችም እንደልብ ለመብረር በቅርብ ርቀት ያለውን ሰው እና ቁስ እንደልብ ለማየት ይቸገራሉ።

ነጭ ደመና ጉም ይባላል። ጉም ለበሰ ሲባል ጥቅጥቅ ያለ ደመና፣ ጭጋግ ጉም አፍኖ ዋለ እንደማለት ነው። ደመናው ከሰማያት አልፎ መሬት በመድረስ ከአቅራቢያችሁ በቅርብ ርቀት ያሉ ረጃጅም ህንፃዎችን ድልድዮችን ጋራዎችን በአቅራቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ጭምር የሌሉ እስኪመስል ሲጋርድ ታያላችሁ። በአዲስ አበባ ባለፈው ክረምት ምክንያት በደመና ከእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች እንዲሁም ፖሊስ ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሽከርካሪዎችም ፍጥነታቸውን ቀንሰው እንዲነዱ እግረኞችም በመኪና መንገዶች አካባቢ እንዲጠነቀቁ ሲያሳስቡ ሰምቻለሁ። የኢትዮጵያ አየር መንገድም በደመና ምክንያት የውጭ በረራ የተስተጓጎለባቸው ቀናት ነበሩ።

መቼም ደመና ሲባል ደመና ሁሉ የልማት ደመና ነው፤ መና ሆኖ ምግብ ያወርዳል፤ መጋቢ ነው ማለት አይደለም። በደመና እህል እንደሚበቅለው ሁሉ ዝናብ በዝቶ ፍጥረታትን የሚበቀል ደመና ዝናብም አለ። ሰውን እና እጽዋቱን ያርዳል። እጽዋት ደግሞ ይታረዳል እንዴ? እንዳትሉ ለጽሁፍ እንዲመቸን ሰዋስውን ጥሰን ተጠቅመን ነው። እጽዋቱ ባይታረዱም ባይታጨዱም የጥፋት/ የስጋት ደመና ከመጣ ይወድማሉ። ቤት ንብረት ይወድማሉ፣ ሰዎች ይፈናቀላሉ፤ ምግብ ልብስ መጠለያ ያጣሉ። ሲብስም በጥፋት ደመና ሕይወታቸው የሚጠፉም አሉ። የጥፋት ደመና ሲሆን እጽዋቱ፣ አዝእርቱ፣ አታክልቱ፣ እንስሳቱ፣ አራዊቱ፣ ይጎዳሉ። መጠለያቸው የሚወድም በውሃ ጎርፍ ተወስደውም የሚሞቱ አራዊት ይገኛሉ። እንዲህ ዓይነቱን የጥፋት ደመና፣ ደመኛ ደመና ብንለው ማን ይቀየመናል? ዝናቡ በልክ ሲሆን ግን ለእጽዋቱ፣ ለእንስሳቱ፣ ለአራዊቱ፣ ለአዕዋፋቱ እና ለነፍሳቱ የተመቸ ይሆናል። እናም ደመና የበጎ ነገር ምሳሌ ስለሆነ፤ ደንና መናን፣ የጥፋት ደመናን አርቆ፤ የልማት ደመናን ያምጣልን። አሜን!

ኢኮኖሚ

ስኬት

# ስኬታማ የንግድ ሕይወት-ከአባት በተወረሰ ጠንካራ የስራ ባህል

ፍሬሕይወት አወቀ

ተወልዶ ያደገው የስንዴ ምርት በስፋት በሚመረትበት ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን አሳሳ ከተማ ነው። ቤተሰቡን ጨምሮ አብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ ግብርና የኑሮ መሰረታቸው ሲሆን፣ እሱም ይህን እየተመለከተ አድጓል። ግብርናውን ጨምሮ በንግድ ሥራም የተዋጣለት ለመሆን መብቃቱን ይናገራል። ወላጅ አባቱን ተከትሎ አሽከርካሪነትን፣ የእህል ንግድን፣ የትራንስፖርት አገልግሎትንና የኮምባይነር ሥራን በመሥራት ውጤታማ መሆን ችሏል። ይህ ሰው የዛሬው የስኬት እንግዳችን አቶ ፍቅሩ ጋረደው ይባላል።

ከትምህርት ይልቅ ለንግድ ሥራ በማድላት ትምህርቱን እስከ 12ኛ ክፍል ብቻ የተማረው አቶ ፍቅሩ የ“ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ” መስራችና ባለቤት ነው። እሱ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ወላጅ አባቱ መሰረቱ መሆናቸውን ይገልጻል። ከግብርና ሥራ የተነሱት ወላጅ አባቱ የእህል ወፍጮ ቤት አቋቁመው፣ እህል ነግደው የጭነት መኪና ገዝተዋል። በጭነት መኪናውም የወፍጮ ቤትና የእህል ንግድ ሥራቸውን ይበልጥ አጠናክረዋል።

የሥራ ባህልን ከቤተሰቡና ከአካባቢው ማህበረሰብ የተማረው የዛሬው ታታሪ ባለሀብት አባቱን ለሰባት አመት በአሽከርካሪነት አገልግሏል። ይህን ሁሉ የተረዱት አባትም ‹‹ሰርተህ ትከፍላለህ›› በሚል ለፍቅሩ የሥራ መኪና ገዙለት። እሱም ሌት ተቀን ሰርቶ መኪናው የተገዛበትን ገንዘብ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መለሰ።

ይህ ስኬቱ በሁለተኛው ዓመት ኮምባይነር መግዛት አስቻለው። ወዲያውም የአርሶ አደሩን አዝመራ መሰብሰብ ውስጥ ገባ። በኮምባይነር ስራውም ከአንድ ኮምባይነር ወደ ሁለት እያለ ውጤታማ ሆነ። የኮምባይነር ሥራ ጊዜያዊ መሆኑ ያሳሰበው አቶ ፍቅሩ፣ የትራንስፖርት ፈቃድ አውጥቶ የአፈር ማዳበሪያና እርዳታ የመሳሰሉትን በማጓጓዙ ስራ ደግሞ ተሰማራ። ይህ ውሳኔው ጊዜያዊ ችግርን ወደ እድል መቀየር የሚችል እሳቤ እንዲያዳብር አድርገው።

የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ለተለያዩ የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ስንዴ ያከፋፍል ነበር። አዲስ አበባን ጨምሮ ሀዋሳና አዳማ ላይ ለሚገኙ የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የስንዴ ምርትን ሲያከፋፍል በመሰል ስራ ላይ ቢሰማራ ውጤታማ እንደሚሆን ተገነዘበ። ስንዴን በግብአትነት የሚጠቀም ፋብሪካ ማቋቋም እንዳለበትም ወሰነ።

ፋብሪካ የመገንባት ውስጣዊ ፍላጎቱን አንግቦ ወደ አዳማ ያቀናው አቶ ፍቅሩ፤ በ2003 ዓ.ም አራት ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በአዳማ አካባቢ ጋራ ዱኮ ቀበሌ ላይ ፋብሪካውን በመገንባት ወደ ሥራ ገባ። ግንባታውን እንዳጠናቀቀም በአነስተኛ አቅም የስንዴ ዱቄት ማምረት ጀመረ። በወቅቱ በቀን 420 ኩንታል ዱቄት ብቻ ያመርት እንደነበር ያስታውሳል። በአሁኑ ወቅት ፋብሪካው አቅሙን በማሳደግ በቀን 1920 ኩንታል የስንዴ ዱቄት ያመርታል። ፋብሪካው ሙሉ አቅሙን ተጠቅሞ ማምረት እንዳይችል አልፎ አልፎ የመብራት መቆራረጥ ቢያጋጥመውም ችግሮችን ተቋቁሞ በማለፍ የፋብሪካውን አቅም እያሳደገ መጥቷል።

በአነስተኛ አቅም ዱቄት ብቻ በማምረት ወደ ሥራ የገባው ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ዱቄት የማምረት አቅሙን ከማሳደግ በተጨማሪ የተለያዩ ብስኩቶች ማምረት የሚያስችሉትን ሁለት አይነት ዘመናዊ የብስኩት ማሽኖችን በመትከል የተለያዩ አይነት ጣዕምና ይዘት ያላቸውን ብስኩቶች እያመረተ ይገኛል። ፋብሪካው ከዱቄትና ከተለያዩ የብስኩት ምርቶቹ በተጨማሪም ወደ ችፕስ ምርት መግባት መቻሉን የጠቀሰው አቶ ፍቅሩ፤ ምርቶቹን ማስፋት የቻለውም ፋብሪካውን በማስፋትና የተለያዩ ማሽኖችን በመትከል እንደሆነ ይናገራል።


ፎቶ፦ በአሸናፊ ጉደታ

አቶ ፍቅሩ ጋረደው

ስምንት ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል በመያዝ የፋብሪካ ሥራን ዱቄት በማምረት የተቀላቀለው አቶ ፍቅሩ፤ በመጀመሪያ አራት ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ ፋብሪካውን እንዳቋቋመ አጫውቶናል። ሥራውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳደገ በመሄድም የፋብሪካ ምርቶቹን ለማሳደግ ፋብሪካውን አስፋፍቷል። የፋብሪካ ይዞታውንም ወደ 14 ሺ 600 ካሬ ሜትር ስፋት በማሳደግ ምርቶቹን በከፍተኛ ጥራት እያመረተ ይገኛል።

ፋብሪካው ከሚገኝበት 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የድንች ምርት በስፋት እንደሚመረት ያጫወተን አቶ ፍቅሩ፤ በዚሁ መነሻ ነው ወደ ቺፕስ ማምረት የገባው። ዩኒክ በሚለው የንግድ ስሙ በአሁኑ ወቅት ድንች ላይ እሴት ጨምሮ ዩኒክ ችፕስን አምርቶና አሽጎ ለገበያ ያቀርባል።

ፋብሪካው በአካባቢው የሚመረተውን ድንች ፋብሪካው በቀጥታ መጠቀም እንዲያመቸው ድንች አምራች ከሆኑ አርሶ አደሮች ጋር የገበያ ትስስር ፈጥሯል። በተፈጠረው የገበያ ትስስርም አርሶ አደሩ ምርቱን በቀጥታ ለፋብሪካው እያስረከበ ይገኛል። ይህም ፋብሪካውን ተጠቃሚ ከማድረግ ባለፈ የገበያ ዕድል በመፍጠር ምርቱን በቀላሉ መሸጥ እንዲችል አግዞታል።

ከቺፕስ ማምረት ባሻገር በስንዴ ዱቄት የተለያዩ ምርቶችን ማምረት እንደሚችል የተረዳው አቶ ፍቅሩ፤ የሁሉም ነገር መነሻው በሆነው ዱቄት ላይ ከ2004 እስከ 2011 ዓ.ም ትኩረት አድርጎ ሠርቷል። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮም ጥናት በማድረግና በዕቅድ በመንቀሳቀስ ወደ ብስኩት ምርቶች መሸጋገር እንደቻለ ነው የገለጸው።

አቅሙን እያሳደገ በጥናትና በዕቅድ ወደ ብስኩት ማምረት የገባው ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፤ አንደኛውና መደበኛው ብስኩት በሚያመርተው ማሽን በሰዓት 1450 ኪሎ ግራም ብስኩት የማምረት አቅም አለው። ሁለተኛውና ዋፈር የተባለውን ለህጻናት ምግብ መሆን የሚችለውና ጣፋጭ ብስኩቶችን የሚያመርተው ዘመናዊ ማሽን ደግሞ 250 ኪሎ ግራም ዋፈር ብስኩት የማምረት አቅም አለው። ቺፕስን በተመለከተም በቀን 200 ኪሎ ግራም ቺፕስ እያመረተ ይገኛል።

በአብዛኛው ህጻናት የሚጠቀሙት ዋፈር የተባለው የብስኩት አይነት የተለያየ ጣዕም ያለውና ወተት፣ ቅቤና ሌሎች ግብዓቶችንም የሚፈልግ እንደሆነ የገለጸው አቶ ፍቅሩ፤ ከስንዴ በስተቀር

**በአነስተኛ አቅም ዱቄት ብቻ በማምረት ወደ ሥራ የገባው ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ዱቄት የማምረት አቅሙን ከማሳደግ በተጨማሪ የተለያዩ ብስኩቶች ማምረት የሚያስችሉትን ሁለት አይነት ዘመናዊ የብስኩት ማሽኖችን በመትከል የተለያዩ አይነት ጣዕምና ይዘት ያላቸውን ብስኩቶች እያመረተ ይገኛል**

ተጨማሪ የሆኑ አብዛኞቹ ግብዓቶች ከውጭ አገር የሚመጡ በመሆናቸው በዘርፉ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንደሚያጋጥመው ጠቁሟል። ይሁንና አሁን አሁን እንደ ቅቤ ያሉ ግብዓቶች በአገር ውስጥ እየተመረቱ መሆኑ አበረታች ነው ይላል። ነገር ግን የተለያዩ ጣዕም ያላቸውን ምርቶች የሚያመርት አምራች ኩባንያ በአገሪቱ ባለመኖሩ ግብዓቶቹን ከውጭ ማምጣት የግድ ነውና አብዛኞቹ ግብዓቶች ከውጭ የሚመጡ ናቸው ይላል።

ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ምርቶቹን በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ ናቸው። ወኪል ከሆኑ ነጋዴዎች ጋር ትስስር በመፍጠር በአገሪቱ በሚገኙ የተለያዩ የክልል ከተሞች ተደራሽ መሆን እንደቻለ ይናገራል።

በፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በዘይት ምርት ለመሰማራት የፋብሪካ ግንባታውን አስጀምሯል። በአገሪቱ ያለውን ከፍተኛ የሆነ የዘይት ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ምግብ አምራች ፋብሪካ እንደመሆኑ ዘርፉን የተቀላቀለው አቶ ፍቅሩ፤ በአዳማ ከተማ አካባቢ ቦኩ ሸነን ቀበሌ ከከተማ አስተዳደሩ በተረከበው 30 ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ የዘይት ፋብሪካውን እየገነባ ይገኛል። በአሁኑ ወቅትም ግንባታውን አጠናቅቆ ወደ ምርት ለመግባት የማሽን ጥናት እያደረገ ይገኛል።

የዘይት ፋብሪካው ሲጠናቀቅም 1100 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም ዱቄት፣ ብስኩትና ችፕስ በማምረት የሚታወቀው ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፣ አጠቃላይ 800 ለሚደርሱ ዜጎች በቋሚነትና በጊዜያዊነት የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። ከእነዚህ መካከልም 580 የሚደርሱት በቋሚነት ሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ናቸው።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም ፋብሪካው የተለያዩ አበርክቶዎችን ለማህበረሰቡና ለመንግሥት እያደረገ መሆኑን የጠቀሰው አቶ ፍቅሩ፤ በተለይም አገራዊ ለሆኑ ማንኛቸውም ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት ቀዳሚ መሆኑን ይናገራል። ለአብነትም በ2014 ዓ.ም ብቻ ከአዳማ ከተማ አስተዳደር ለተደረገለት ጥሪ ከሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል። በክፍለ ከተማ ደረጃም እንዲሁ ትምህርት ቤትና የስብሰባ አዳራሽ ገንብቶ አስረክቧል። አዳማ ከተማን ስማርት ሲቲ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ፋብሪካው ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር በተለይም ዱቄት በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንዲችሉ በአካባቢው የችርቻሮ መሸጫ ሱቅ ከፍቶ ምርቱ ነጋዴ ጋ ሳይደርስ የአካባቢውን ማህበረሰቡ ተጠቃሚ ያደርጋል። ፋብሪካውም ሆነ የአካባቢው ማህበረሰብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ማግኘት እንዲችል የውሃ ጉድጓድ በመቆፈር ፋብሪካ ከሚጠቀመው የውሃ መጠን ባለፈ በአካባቢው የውሃ እጥረት በሚገጥምበት ወቅት ማህበረሰቡ የጉድጓድ ውሃውን በፈለገ ጊዜ እንዲጠቀም እያደረገ ይገኛል። ለፋብሪካው ሠራተኞች ቁርስ በነጻ እንዲሁም ምሳም 50 በመቶ ወጪ በመጋራት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ሠራተኞችን እያገዘ እንደሆነም አቶ ፍቅሩ አጫውቶናል።

በአሁኑ ወቅት የስንዴ ምርት በአገሪቱ ባልተለመደ መልኩ በስፋት እየተመረተ መሆኑ በተለይም እንደ ፍቅር የምግብ ማቀነባበሪያ ላሉ ፋብሪካዎች የሚኖረው አበርክቶ የጎላ መሆኑን የሚናገረው አቶ ፍቅሩ፤ በአሁኑ ወቅት ግን ገበያው በተወሰነ መንገድ መረበሽ ታይቶበታል ይላል። ይህም ለጉዳዩ አዲስ ከመሆን ጋር ተያይዞ የመጣ ቢሆንም በሥራው ላይ ግን ከፍተኛ ጫና ፈጥሮ መቆየቱንና እንደነበር ጠቅሷል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በነበረው የግብይት አሰራር የስንዴ ምርቱ አዳማ ድረስ በስፋት ይቀርብ እንደነበር አስታውሶ፣ የፋብሪካውን የጥራት ደረጃ አሟልቶ ሲገኝ ፋብሪካው ወስዶ ያራግፍ እንደነበር ይገልጻል። አሁን ላይ ግን ከተለመደው የግዢ ስርዓት ውጭ ምርቱ ካለበት ቦታ ሄዶ መግዛት እንደሚያስፈልግ ይናገራል። የገበያ ስርዓቱ አዲስ እና ያልተለመደ በመሆኑ ለቁጥጥርም አስቸጋሪ ሆኖ መቆየቱን ጠቁሟል። አሁን ችግሩን ለማቃለል መንግሥት ኮታ መድቦ ፋብሪካዎች የስንዴ ምርት እንዲያገኙ እየተሠራ መሆኑንም አስረድቷል።

በቀጣይ የፋብሪካውን ምርቶች በከፍተኛ ጥራትና በሙሉ አቅሙ ለማምረት ዕቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑን የጠቀሰው አቶ ፍቅሩ፤ በተለይም ግንባታው የተጀመረውን የዘይት ፋብሪካ አጠናክሮ በማስቀጠል ወደ ሥራ ማስገባትና እንደ አገር ያለውን የዘይት ምርት እጥረት እንዲሁም የዋጋ ንረትን በማቅለል አማራጭ የመሆን እቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑ ይጠቁማል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ለተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላኑ ዝግጅት ውጤታማነት

**መሳኩ ሔሮሴ**



መሰረተ ልማት ለአገር ብሎም ለከተማ እድገት ምሶሶ ነው። የለውጥና የእድገት ካስማ የሆነውን የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በአግባቡ ያከናወኑ አገራት የዓለማችን የለውጥና የብልጽግና አብነት ተደርገው ይወሰዳሉ። በአንጻሩ ደግሞ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ወደ ኋላ የቀሩ አገራት የድህነት እና ኋላቀርነት አብነት ሆነው ይኖራሉ።

ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ረገድ አመርቂ ውጤት ማስመዝገቧ ይታወቃል። በመሰረተ ልማት ግንባታ ረገድ ብዙ ርቀት ብትጓዝም፣ ግንባታዎቹን በተቀናጀ መንገድ የመምራት ልምዷ ግን እምብዛም ነው።

መሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በየፊናቸው እያካሄዱ ያለበት ሁኔታ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይካሄድ እንቅፋት ሆኗል። ሀብት አላግባብ እንዲባክንም መንስኤ ሆኗል። የአገር ሀብት እንዳይባክን እና የመሰረተ ልማት ዝርጋታን ማፋጠን እንዲቻል የመሰረተ ልማት ዝርጋታን አቀናጅቶ መምራት ለአገርም ሆነ ለከተሞች እድገትም ተኪ የለውም።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ዝርጋታና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ዙሪያ በዋና ኦዲተር በቀረበለት የክዋኔ ኦዲት ላይ ከወር በፊት ባካሄደው ውይይት፤ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ረገድ ቅንጅታዊ አሰራርን በመተግበር ረገድ የሚመለከታቸው አካላት ብዙ መስራት ቢጠበቅባቸውም፣ የሚጠበቅባቸውን ያህል እንዳልሰሩ ጠቁሟል። በተለይም የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የመሰረተ ልማቶች ግንባታ በተቀናጀ መንገድ እንዲገነባ የሚጠበቅበትን አልሰራም ብሏል። በዚህም ምክንያት አገሪቱ ብዙ ዋጋ እየከፈለች መሆኗን አመልክቷል።

በእርግጥ በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የመሰረተ ልማት በሚያቀርቡ ተቋማት መካከል መናበብ ባለመኖሩ አንዱ የገነባውን ሌላው ሲያፈርስ መመልከት ተለምዷል። አንዳንድ ጊዜ አንዱ የገነባውን መሰረተ ልማት ወር እንኳን ሳያገለግል ሌላኛው አፍርሶ በቦታው የራሱን መሰረተ ልማት ሲዘረጋ ይታያል።

አንዳንድ ጊዜ ተቋማቱ በአንድ መንግሥት የሚመሩ መሆናቸውን እንድንጠራጠር የሚያደርጉ ተግባራት ሲከናወኑ ይስተዋላል። የመንገድ መሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋም መሰረተ ልማቱን ዘርግቶ ካጠናቀቀ ብዙም ሳይቆይ ኢትዮቴሌኮም የራሱን መሰረተ ልማት ዘርግቶ ሲጨርስ፣ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ግንባታ ለማካሄድ ይነሳል፤ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ዝርጋታ ተጠናቀቀ ተብሎ እፎይታ ሊገኝ ነው ሲባል ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ አዲስ ቁፋሮ ይጀምራል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኢትዮጵያ በዴቻ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፤ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በተቀናጀ መንገድ ማካሄድ አለመቻሉ አገሪቱን ብዙ ዋጋ እያስከፈላት ነው። የተቀናጀ አሰራር አለመኖር በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ላይ ትልቅ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል። መሰረተ ልማት የሚገነቡ ተቋማት በአግባቡ ተቀናጅተው ባለመስራታቸው ከፍተኛ የሕዝብ እና የመንግሥት ሀብት እየባከነ ቆይቷል። በቅንጅት እጦት ምክንያት በአገር አቀፍ ደረጃ የባከነውን ሀብት መጠን በእርግጠኝነት መገመት ባይቻልም ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ እንዳለ በተለያዩ አጋጣሚዎች በዘርፉ ባለሙያዎች እና በመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ይነሳል።

ባለፈው ዓመት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ያካሄደው ጥናት እንዳመላከተው በአገር ደረጃ ተቀናጅቶ ባለመስራቱ አገሪቱ ላልተገባ ወጪ እንድትዳረግ ምክንያት እየሆነ መሆኑን አመላክቷል።

በቅንጅት እጦት ምክንያት አገሪቱ እየከፈለች ያለችው ዋጋ ከዚህም የበለጠ ነው። ለአብነት መንገድ ሲሰራ የመንገድ ዝርጋታ እና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ በሚያካሂድ አካል መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ የኤሌክትሪክ ፖል መነሳት ባለበት ወቅት ሳይነሳ የሚቀርበት አጋጣሚ አለ። በዚህም ምክንያት የመንገድ ግንባታው ይጓተታል። ግንባታዎች በወቅቱ ሳይጠናቀቁ በሚቀሩበት ወቅት የሚፈጠር የግንባታ እና የግብዓት ዋጋ መናር ይከሰታል። ዘንድሮ መሰራት ያለበት ፕሮጀክት በተቋማት ቅንጅት እጦት ምክንያት ዘንድሮ ሳይጠናቀቅ ሲቀር ለዓመታት እየተጓተተ በሄደ ቁጥር የመሰረተ ልማቶቹ ግንባታ ጥራት እየቀነሰ፣ የግንባታ ግብዓት ዋጋ እየጨመረ ፣ለሰው ኃይል የሚከፈለው ክፍያ እየጨመረ፣ ለካሳ የሚከፈለው ክፍያም እየጨመረ ይሄዳል። ይህም የአገር ሀብት በአላስፈላጊ ሁኔታ እንዲባክን እያደረገ ይገኛል ይላሉ።

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ ይህ የቆየ ችግር ለመፍታት በተለያዩ ጊዜያት ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ችግሩን እንደሚፈታ ተስፋ የተጣለበት ተቋም ከስድስት ዓመት በፊት ተቋቁሟል። ተቋሙም የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ኤጀንሲ ይሰኛል። ይህ ተቋም እጅግ ትልቅ ተቋም ነው። በመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት መካከል የሚታየውን የቅንጅት ችግሮችን እንዲፈታ ነው የተቋቋመው። ወደ ስራም ገብቶ ነበር።

ሆኖም የተቋሙ መቋቋም ችግሩን አልፈታም። በመሆኑም የተቋሙ ሙሉ ስራው ወደ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መጥቶ ሚኒስቴሩ ክትትል እያደረገበት የመሰረተ ልማቶች ግንባታ እንዲቀናጅ ጥረት እየተደረገ ነው። የመሰረተ ልማት ዝርጋታ የሚያካሂዱ አገር አቀፍ ተቋማት፤ የቴሌኮም፣ የመንገድ፣ የመብራት፣ የውሃ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ እና አቪዬሽን ተቋማት በጋራ ተቀናጅተው መስራት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር በዋናነት እነዚህ ተቋማት የጋራ እቅድ እንዲያዘጋጁ የመግባቢያ ሰነድ የመፈራረም ስራ መሰራቱን ጠቁመዋል።

ተቋማቱ እያንዳንዱን ስራ በየፊናቸው ከሚሰሩ ይልቅ አንዱ ከአንዱ ጋር ተናቦ መስራት ቢችል የሚፈጠረውን የገንዘብ፣ የጊዜ እና የቁሳቁስ ብክነት ማዳን እንደሚቻል የጠቆሙት አቶ ኢትዮጵያ፤ ህብረተሰቡም የሚፈልገውን የመሰረተ ልማት ፍላጎት በሚፈልገው ጥራትና ጊዜ ማግኘት የሚችልበት እድል ይፈጠራል ይላሉ። ይህንን በማሰብ የጋራ እቅድ እንዲኖራቸው ለማድረግ የጋራ የስምምነት ሰነድ እንዲፈራረሙ ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል። ስምምነቱን መሰረት አድርጎ ለሚሰሩት ስራ የጋራ እቅድ እንዲኖራቸውም ጥረት መደረጉን አብራርተዋል።

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ገለጻ፤ በጋራ እቅዳቸው መሰረት ችግሮች እንዲፈቱና በየጊዜው እየተገናኙ ስራዎችን እንዲገመግሙ እየተደረገ ነው። ከማቀድ ባለፈ ስራዎችን ታች ድረስ ወርዶ ለመከታተልና ድጋፍ ለማድረግ እየተሰራ ነው። እነዚህ ስራዎቹ ምን ይመስላሉ፣ እንዴት እየተሰራ ነው የሚለው መመልከት ያስፈልጋል። የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ እና የቴሌኮም መሰረተ ልማት ሲሰራ እንዲሁም ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲገነቡ እና በየቦታው የአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ሲስፋፋ የሚሰሩት የቅንጅት ስራዎች በክትትል እና ድጋፍ አንድ የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው።

አገሪቱን ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለ የሚገኘው ያልተቀናጀ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መንስኤዎች በርካታ ቢሆኑም፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ማስተር ፕላን አለመኖር፣ ለችግሩ ዋነኛው መንስኤ ነው የሚሉት አቶ ኢትዮጵያ፤ የመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማትን ለማቀናጀት ከዚህ በፊት ያልነበረ አገራዊ የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላን አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት፤ የማስተርፕላን ዝግጅት ስራ እየተሰራ ነው ሲሉ ያብራራሉ። ይህንን ማስተር ፕላን ወደ ውጤት ለመቀየር እየተሰራ ነው።

በቅርቡም የማስተር ፕላን ዝግጅቱ ያለበትን ሁኔታ አስመልክቶ በአዳማ ውይይት ተደርጓል። የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ከሚያካሂዱ ዋና ዋና ተቋማት የፕላንና ልማት ሚኒስቴርን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተናበው መስራታቸው አስፈላጊ በመሆኑ የመጀመሪያው ምዕራፍ የማስተር ፕላን ዝግጅት ተጀምሯል።

የማስተር ፕላን ዝግጅት ለውይይት መነሻ የሚሆን በመድረኩ ላይ የመሰረተ ልማት አገራዊ ማስተር ፕላን እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት፣ የማስተር ፕላኑ አስፈላጊነት፣ የሌሎች አገራት ተሞክሮ ምን እንደሚመስል፣ የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላን ያላቸው አገራት ማስተር ፕላን በምን መልኩ አዘጋጁ፣ ማስተር ፕላን በማዘጋጀት ልምድ ያላቸው አገራት የትኞቹ ናቸው፣ እነዚህ አገሮች በማስተር ፕላኑ ምን ማትረፍ እንደቻሉ የሚያሳዩ ጽሁፎች ቀርበው ተቋማት ተናበው በመስራታቸው ምን ውጤት መጣ የሚለው ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጎባቸዋል። በቀጣይ ምን ምን መሰራት እንዳለበት የተመላከተበት ትልቅ መድረክ መካሄዱንም አብራርተዋል።

ማስተር ፕላኑን የማዘጋጀት ስራውን ከየተቋሙ የተወጣጡ ባለሙያዎች እየሰሩት ነው። እነዚህ ተቋማት በቀጣይ ማስተር ፕላኑን ወደ መሬት አውርደው፣ የሚያስፈልገውን በጀት፣ የሰው ኃይል እና የተለያዩ ግብዓቶች በማካተት፣ እነዚህን አሟልቶ በፍጥነት ማስተር ፕላኑ ተዘጋጅቶ በአገር አቀፍ ደረጃ ጸድቆ ወደ ስራ የሚገባበት ይሆናል። ማስተር ፕላኑ በቀጣይ አንድ ዓመት ውስጥ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ይገባል ተብሎ እንደሚጠበቅ አቶ ኢትዮጵያ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ ማስተር ፕላኑ የቅንጅት ችግር እያስከተለ ያለውን ጉዳት ለመከላከል በየደረጃው የሚገኙ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት የየራሳቸውን የአጭር እና የረጅም ጊዜ እቅድ ከአገራዊ ራዕይ ጋር በማጣጣም ማስተር ፕላኑን ማዘጋጀት ይቻል ዘንድ በቂ ግብዓት ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የውይይት መድረኩ ፋይዳው የላቀ መሆኑ ተጠቁሟል።

ማስተር ፕላኑ ተግባራዊ ሲሆን ከአሁን በፊት የተፈጠሩት እና ይፈጠራሉ ተብለው የሚሰጉት ችግሮች እየተቀረፉ የሚሄዱበት ሂደት ይኖራል ያሉት አቶ ኢትዮጵያ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ መሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት መሰረተ ልማቶችን በመዘርጋት ላይ ባሉ ተቋማት መካከል ቅንጅት ሲኖር የሀብት፣ የጊዜ እና የሰው ኃይል ብክነትን ማስቀረት ይቻላል ብለዋል።

በውይይት መድረኩ የፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር፣ ኢትዮ ስፔስ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል፣ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን፣ የአዲስ አበባ ፕላን ኮሚሽን እና የአዲስ አበባ ግንባታ ፈቃድ ተቋማት ለአገራዊ ማስተር ፕላኑ ዝግጅት ከየተቋማቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት አስፈላጊውን ግብዓት መስጠታቸውን ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

አገራዊ የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተር ፕላንን በቁርጠኝነት ተግባራዊ ለማድረግ በሚወጡ መመሪያዎች ዙሪያ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው በመስራት የአገርን ሀብት ከብክነት ማዳን ይገባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላሙ ጉዞ ዘላቂነት ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የድርሻውን ይወጣ!

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተካሄደው ጦርነት በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ዜጎች ለሞት፣ ለስደትና ለረሃብ ዳርጓል። ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ፈጥሯል። ጦርነቱን ለማቆም በኢትዮጵያ መንግስት እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ተፈርሟል።

አሁን ላይ ይህ የሰላም ስምምነት ከአራት ወራት በላይ አስቆጥሯል። በስምምነቱ መሰረት በሁለቱ አካላት መካከል መተማመን የሚፈጥሩ ተግባራት ተከናውነዋል። በቅርቡ ደግሞ ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ስያሜ የመሰረዝና በስምምነቱ አንቀፅ 10(1) መሰረት በትግራይ ለሚቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር እንዲሆኑ መንግስት አቶ ጌታቸው ረዳን ሾሟል። ጊዜያዊ አስተዳደሩ አሳታፊና አቃፊ እንደሚሆን ይጠበቃል። ይህ ሂደት በትግራይ ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና ዳግም ግንባታ ለማስጀመር ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

የሰላም ስምምነቱ ትግበራ ተከትሎ በትግራይ ክልል ያለው አጠቃላይ ሁኔታ አሁን ተቀይሯል። ሰብአዊ ርዳታ እየገባ ነው፣ መሰረታዊ አገልግሎቶች ወደነበሩበት እየተመለሱ ነው። ይህ ሰላም ለትግራይ ህዝብ ትልቅ እፎይታን የሰጠና ስለ ዳግም ግንባታ እንዲያስብ እድል የፈጠረ ነው። ሰላም ከማንም በላይ ለትግራይ ሕዝብ ጠቃሚ መሆኑን በተጨባጭ ያመላከተም ነው።

የትግራይ ሕዝብ ያለፉትን አስቸጋሪ ውጣ ውረዶች ግምት ውስጥ በማስገባት አሁን ያለውን የሰላም ምዕራፍ ለማስጠበቅና ዘላቂ ለማድረግ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል። እንደ አገርም ካለፈው ታሪካችንና ስህተታችን ተምረን ጦርነት ከጥፋት ውጪ አንዳች ጠቀሜታ እንደሌለው ተረድተን አሁን ያለውን ሰላም በመጠበቅ ለመልሶ ግንባታ ትኩረት ሰጥተን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ መንግስት በጦርነቱ የወደሙ መሰረታዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመጠገን ወደ ስራ እያስገባ ነው። በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ የደረሰውን ውድመት ተረባርቦ በመጠገን ሕዝቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጓል።

በተመሳሳይ መልኩ በቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ላይ የደረሰውን ጉዳት ጠግኖ አብዛኞቹ የትግራይ አካባቢዎች የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። መንገዶችን፣ ድልድዮችን፣ የትምህርትና እና የጤና ተቋማትንም ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ በማስተካከል ወደ አገልግሎት እንዲመለሱ አድርጓል፤ እያደረገም ነው።

አሁን ባለው እውነታ መልሶ ግንባታው በፌደራል መንግስት እና በጊዜያዊ አስተዳደሩ አቅም ብቻ ሊፈታ የሚችል አይደለም። ለግንባታው የትግራይ ተወላጅ ከሆኑ ዳያስፖራዎችና ምሁራን ብዙ ይጠበቃል። እነዚህ ወገኖች በሚሰሩባቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት መሬት ላይ ያለውን ሁኔታ በማስረዳት ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ እንዲገኝ በስፋት ሊንቀሳቀሱ ይገባል። ጠንካራ የገንዘብ አቅም ያላቸውም በክልሉ ኢንቨስት በማድረግ ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራና ለወጣቶች የስራ ዕድል ለመፍጠር መስራት ይኖርባቸዋል፡።በትግራይ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎችም የፖለቲካ ልዩነታቸውን ጠብቀው ደጋፊዎቻቸውን በማስተባበር ለትግራይ መልሶ ግንባታ እና ለግዜያዊ አስተዳደሩ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ነገ ምረጡኝ የሚሉት ሕዝብ ከችግር በማውጣት ስራ ላይ ተሳታፊ በመሆን ህዝባዊነታቸው ከወዲሁ በተጨባጭ ሊያሳዩ ይገባል።

የትግራይ ሕዝብ በተለይም የትግራይ ወጣቶችም ለክልሉ መልሶ ግንባታ ያላቸውን ትልቅ አቅም በመረዳት፤ የወደሙ ተቋማትን በመጠገንና በተፈጥሮ ሀብትና በተፋሰስ ጥበቃ ሥራ ላይ በመሰማራት ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ግዴታቸውን በመወጣት የትግራይን መልሶ ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤታማ ለማድረግ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

ዓለም አቀፍ ተቋማትም ቢሆኑ በትግራይ ክልል የሚካሄደው መልሶ ግንባታ ከፌደራል መንግስትና ከጊዜያዊ አስተዳደሩ በተጨማሪ በብዙ መልኩ የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ድጋፍ የሚሻ መሆኑን በአግባቡና በቅንነት በመረዳት የሞራልና የሰብአዊነት ግዴታዎቻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

በአጠቃላይ የተገኘው ሰላም ለትግራይ ህዝብ ሆነ በመላው አገሪቱ ከፈጠረው እፎይታ አኳያ፤ ሰላሙን በመልሶ ግንባታ በመደገፍ ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ መላው ሕዝባችን በተለይ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ፣ ልሂቃን፤ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ዳያስፖራው እና ሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች በጋራ ተቀናጅተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ‹‹ግባ›› አይሉት የዝናብ እንግዳ

መልካምሥራ አፈወርቅ

አበው ሲተርቱ ‹‹የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ ›› ይላሉ። ተረቱ ሁሉም በጊዜው መስመር ሊይዝ እርምጃህን በወግ አድርገው ለማለት ይመስላል›› ድንገቴው የሰሞኑ ዝናብ ግን እንደአባባሉ ቶሎ ያልፍ አይመስልም። ዘንቦ ባባራ ቁጥር ክፉ ዜናዎችን ያሰማን፣ ያሳየን ይዟል።

በአምና ካቻምና ተሞክሮ ዝናቡ ይህን ጊዜ እንደወጉ ደርሶ፣ እንደዓመሉ አድርሶ ይመለስ ነበር። ብዘዎች እንደሚሉትም በዚህ ወቅት የሚመጣ ዝናብ ለበልጉ እርሻ እጅግ ተፈላጊና ተስማሚ ነው። ዘንድሮ ግን የአመጣጡ ጉዳይ ከዓመል መለወጥ ጋር ሆኗል። በበጋው ጸሀይ መሀል እንግዳ ሆኖ የከረመው ከባድ ዝናብ በርካቶችን ዋጋ እያስከፈለ ነው።

ከሰሞኑ በከተማችን አዲስ አበባ አምርሮ የሚጥለው ከባድ ዝናብ ጎርፍ አስከትሎ ህይወትን ቀጥፏል። ንብረት አውድሞ መንገድ ድልድዮችን ሰብሯል። የድንገቴው ከባድ ዝናብ ጉዳይ ማባራትን ተከትሎ ወደጆሮ የሚደርሱ ክፉ ዜናዎች ደግሞ የጉዳዩን አሳሳቢነት ያመላክታሉ። በቅርቡ አገር አማን ብለው ከታክሲ ገብተው ጉዞ የጀመሩ መንገደኞች ያላሰቡት ገጥሟቸዋል። የመንገደኞቹ ጉዞ በምሽት ነበር። እዚሁ መዲናችን አዲስ አበባ።

ታክሲው ተሳፋሪዎቹን እንዳጨቀ መፍጠኑን ይዟል። ሰዓቱ እየገፋ፣ ጊዜው እየጨለመ ነው። በውስጡ ያሉት ተሳፋሪዎች የዝናቡን ማጉረምረም እያስተዋሉ ከቤታቸው ለመግባት ተጣድፈዋል። ለሾፌሩ መንገዱም ሆነ መንገደኞቹ አዲሶች አይደሉም። በየዕለት አጋጣሚው እነሱን መሰል ተሳፋሪዎች ይዞ መጓዙ የተለመደ ነው።

መንገዱ ቀጥሏል። በየወንበሩ ከልክ በላይ የጫነው ታክሲ የእግር ማሳረፊያ ይኩት የለውም። በታክሲው ተቀምጠዋል ከተባለ ከመሬት ኩርምት ያሉ መንገደኞች ጭምር ተካተዋል። ሾፌሩ አንድ ከተባለ በውስጡ ሀያ አንድ ሰዎች ተቆጥረው ታጭቀዋል።

ታክሲው ቀስ እያለ የማዝገሙን ጉዳይ ተሳፋሪው የወደደው አይመስልም። ሁሉም ‹‹መጣሁ›› ካለው ከባድ ዝናብ አምልጦ ቤቱ መግባትን ይፈልጋል። ጉዳዩ እንደታሰበው አልሆነም። ዝናቡ እየጨከነ፣ ክፉኛ እያመረረ ነው። ጉልበቱን በከባድ ወጨፎው ተገልጾ እያሳወቃቸው ነው።

በዚህ ብቻ አልበቃውም። ጥቂት ቆይቶ ወጨፎው በሀይለኛ ዝናብ ተተካ። ሆዱን ሞልቶ ጉዞ የጀመረው መኪና ጭንቅ ያዘው። ከውስጥ ያሉት ሰዎች እየሆነባቸው ያለውን ጉዳይ አምነው መቀበል አልቻሉም።

አሁን የታክሲው ግማሽ ወገብ በደለልና በጎርፍ ተውጧል። አንድም ሰው በቀላሉ ወርዶ ማምለጥ አይችልም። የታክሲው ውስጥ ሰዎች አይቀሬውን ገጠመኝ ሊጋፈጡት ግድ ሆነ። ራሳቸውን ከችግሩ የታደጉ የመሰላቸው ጥቂቶች መላ ያሉትን ዘየዱ። ፈጥነው ከታክሲው አናት ኮፈኑ ላይ ወጡ። መፍትሄ የለም። ዝናቡ ያለማቋረጥ ቀጥሏል። ጭንቀቱ ያለቅጥ በርትቷል።

ከላይ ዝናብ፣ ከስር ጎርፍና ደለል ባስጨነቀው ታክሲ ያሉ ሰዎች ‹‹ድረሱልን›› እያሉ ነው። ሰሚ የለም። ከነዚህ መሀል ዘጠኙ ሴቶች ናቸው። ማንም ከአፍታ በኋላ የሚሆነውን አያውቅም። ጊዜው በተስፋም ያለተስፋም እየሄደ ነው። የበረቱ ስልካቸውን ይደውላሉ፣ ወደ ወዳጅ ቤተሰብ፣ ጓደኛና ጎረቤት ዘንድ። ውሀው ወገባቸውን አልፎ ከትከሻቸው የደረሰ ተሳፋሪዎች አሁንም ተጨንቀዋል። ለእርዳታ ከሚደውሉ ስልኮች መሀል በድንገት አንደኛው መስመር ተነሳ። የአዲስ አበባ እሳትና ደንገተኛ አደጋዎች ክፍል ነበር።

መልዕክት ተቀባዩ ስልኩን እንደዘጋ ጊዜ አላባከነም። ጥቆማ በደረሰው ቦሌ አካባቢ አስፈላጊውን ቡድን አሟልቶ በፍጥነት ገሰገሰ። የአደጋ ጊዜ ተጠሪዎች በስፍራው ሲደርሱ ሀይለኛው ዝናብ እንደቀጠለ ነበር። እንዲህ መሆኑ እርዳታውን ፈጥኖ ለመከወን አዳጋች አደረገው።

ሀያ አንዱን ተሳፋሪዎች እስከ አንገታቸው ከዋጣቸው ጎርፍ አውጥቶ ታክሲውን ከገባበት የደለል ማጥ ለማንቀሳቀስ ሁኔታው ከባድ ሆኖ ቆየ። በመጨረሻም በአደጋ ጊዜ ባለሙያዎች ብርታትና በሌሎች ሰዎች እገዛ ሕይወት ሳይጠፋና የከፋ ጉዳት ሳይደርስ ችግሩን መታደግ መቻሉን ከሚመለከተው ክፍል መረጃው ተላለፈ።

በዚህ ቀን በደረሰው ተመሳሳይ ክስተት በዝናቡ ሰበብ መንገድ ጥሶ የገባ ድንገቴ ጎርፍ በመኖሪያ ቤቶችና በርካታ ንብረቶች ላይ ጉዳት አድርሷል። ይህ የበጋ ዝናብ ጉዳይ በእንዲህ አይነቱ ገጠመኝ ብቻ አልተቋጨም። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ልዩ ቦታው ‹‹ማንጎ ጨፌ›› ከሚባል ስፍራ ድንገቴው ዝናብ ከወንዝ አብሮ የአራት ሰዎችን ህይወት ቀጥፏል።

መረጃዎች እንደጠቀሙት ጎርፉ ከሌላ አካባቢ ተጠራርጎ አካባቢውን ያጥለቀለቀ ነው። በአካባቢው ቤቶችን እየጣሰ፣ ግድግዳ እየገመሰ ጉዳት አድርሷል። በድንገቴው ዝናብና አደጋውም አንዲት እናት ከሶስት ልጆቿ ጋር ህይወቷን አጥታለች።

የአጋጣሚው መከሰት አንድ ጉዳይ ሆኖ ለአደጋው መባባስ መንስኤ የሚሆኑ ሰበቦችን መገመት ይቻላል። በቅድሚያ በታክሲው የተከሰተው ድንገቴ ጉዳይ እንቃኝ ብንል ከመጠን በላይ ሀያአንድ ሰዎችን የማሳፈሩን ስህተት ነቅሶ ማየቱ ተገቢ ነው።

በእርግጥ ታክሲው በተፈቀደለት ቁጥር ልክ መጫኑ ብቻ ከአደጋ አያድነውም ሊባል ይችላል። በወቅቱ በልክ ማሳፈሩ ግን ሊደርስ የሚችለውን የአደጋ መጠን ሊቀንስለት እንደሚችል ልብ ይሏል። ምንአልባት የከፋ አደጋ አጋጥሞ ህይወት ቢያልፍና አካል ቢጎዳ ቁጥሩ በግማሽ መቀነሱ የጉዳት መጠኑን የተሻለ ያደርገዋል።

ሰሞኑን እየሆነ ያለውን ክስተት መነሻ በማድረግ በአንዳንድ አካባቢዎች ያለውን እውነታ እንፈትሽ። ተደጋግሞ እንደሚባለው ድንገቴው ዝናብ የሚያስከትለው የጎርፍ አደጋ መንስኤ በየስፍራው የሚደፈኑ የውሀ መፋሰሻ ቱቦዎች ያለልክ መደፈን ነው። ለዚህ ደግሞ የቆሻሻ አወጋገድ ልማዳችንን ተጠቃሽ ማድረጉ ብቻ በቂ ይሆናል።

አንዳንዴ ሰዎች በአንድም ይሁን በሌላ ጉዳይ በራሳችን ላይ ለሚከሰት ችግር ተጠያቂ የምንሆንበት አጋጣሚ ይኖራል። ሙዝ በልቶ ከጎዳና ላይ ጥሎ ያለፈ መንገደኛ ሲመለስ በጣለው ልጣጭ ተንሸራቶ ቢወድቅ ለስብራቱ ማንንም ተወቃሽ ሊያደርግ አይገባም። ‹‹እጄን በእጄ›› ይሉት ነውና ጉዳቱ መልሶ ራሱን የሚጎዳው ይሆናል።

አብዛኞቻችን በ‹‹አዩኝ አላዩኝ›› ስሜት ዛሬን ከቱቦ የምንወረውረው ቆሻሻ ውሎ አድሮ ዋጋ ያስከፍለናል። ለውሀ የተባለው መፋሰሻ በቁስ ጥርቅም በተዘጋ ጊዜ ውጤቱን ለማየት ቀን መቁጠር፣ አልያም ክረምቱን መጠበቅ አይኖርብንም። እንዲህ እንደሰሞኑ ክስተት በገዛ እጃችን አጥብቀን በምናስረው ገመድ ተጠልፈን ለመውደቅ የተመቸን እንሆናለን።

ችግሩ ከደረሰብን በኋላም በሌሎች ላይ ጣት ለመቀሰርና ኃላፊነቱን ላለመውሰድ ፈጣኖች ነን። ይህ እንዳይሆን ጥንቃቄ ከራስ ሊጀምር ግድ ይላል። ዛሬ በእኛ ሰበብ በሚፈጠረው ግዴለሽነት ነገን በስጋት ለሚያድሩ ወገኖች ሰበብ ልንሆን አይገባም።

ዛሬ የወንዝ ዳር ቤቶች ዕንቅልፍ የላቸውም። ዳምኖ ባካፋ ቁጥር የሚሆነውን አያውቁምና ስጋታቸው ያይላል። እንዲህ እንደ ሰሞኑ በጸሀይ ተዋዝቶ፣ በዳመና ተሸፍኖ ‹‹መጣሁ›› የሚለው የዝናብ እንግዳ በማን ላይ ምን እንዳሰበ መገመቱ ከባድ ነው። ትንሽ ነው የተባለ ካፊያ በአፍታ የበረዶ ክምር ሲሆን ያስደነግጣል። ምክንያቱም ያለንበት ምድር ኢትዮጵያ እንጂ አውሮፓና አሜሪካ አይደለም።

‹‹ግባ›› አይሉትን ድንገቴ ደራሽ ከበር ለመሸኘት አስቀድሞ መዘጊያን ማጠንከር፣ ተግባርንም ማጥራት ግድ ይላል። ዛሬ በእኛ ምክንያት ለሌሎች መጎዳት ሰበብ ልንሆን አይገባም። ሁሌም ለአደጋ መንስኤ በመሆን ከመተባበር እንጠበቅ፣ ‹‹ነግ በኔ›› ስንል ስለራሳችን እንጠንቀቅ።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ከገጠር እስከ ከተማ በኑሮ የተፈተነች ሕይወት

ጽጌረዳ ጫንያለው

ቤተሰብ ስም ሲያወጣላት በምክንያት ነው። ሰላም እንዳየሁ በማለት የሰላምን አስፈላጊነት ገልጦባታል። በዚህም ለቤቱ ተስፋና ሰላም ሆና ዓመታትን ከእነርሱ ጋር ዘልቃለች። ነገር ግን ሰላሟን የማይሰጥ አንድ ነገር ገጠማት። ያለዕድሜዋ መዳር። ከትምህርቷ አስተጓጉለው ቤተሰቦቿ ሊድሯት መሆኑን ከሰማችበት ጊዜ ጀምሮ አእምሮዋ ታውኳል። ይህም ቤተሰቦቿ የፈጠሩት ነው። ምንም ሳያጎሉባት በቤት ውስጥ ቢያቆዩዋትም መማርን ግን ሊፈቅዱላት አልቻሉም። አግብተሽ ወልደሽና ከብደሽ ከእኛ ጋር ነው የምትሆኚው የሚል አቋም ነበራቸው። እርሷ ደግሞ ይህንን መቀበል አቃታት። በተደጋጋሚ ልታሳምናቸውም ሞከረች። እነርሱ ግን ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ አሉ።

አሁን ነገሮች ሁሉ ተወሳስበዋል። የሚሰማትም አንድም ዘመድ አላገኘችም። ገና በልጅነቷ ቤተሰብ አስተዳዳሪ እንድትሆን ለአንዱ ልትዳር ነው። ስለዚህም ምን ማድረግ እንዳለባት ካወጣችና ካወረደች በኋላ በቀጥታ አንድ ድምዳሜ ላይ ደረሰች። ይህም ከቤተሰቧ ጠፍታ እግሯ ወዳመራት ቦታ መሄድ ነው። ልክ እንደ እርሷ በቤተሰብ ችግር ምክንያት ሊጠፉ የተዘጋጁ ጓደኞች ነበሯትና ተነጋግረው በአንድ ምሽት ከቤት አመለጡ። መድረሻቸውንም አዲስ አበባ አደረጉ።

እነ ሰላም አዲስ አበባ ሲደርሱ ማንም የሚቀበላቸው አልነበረም፤ የሚያውቁት ዘመድም የለም። አዲስ አበባን እንደሰሟት አይነት ገነትም አይደለችም። በወከባ የተሞላች ነች። ሲመችም የሚያታልለው ብዙ ነው። እናም እነሰላም ይህንን ሲያዩ ምን እንደሚያደርጉ ግራ ተጋቡ።

ማንን ማናገርና ማንን አምኖ መከተል እንዳለባቸው ግራ ገባቸው። በዚህም ጎዳና አዳሪነትን ለአንድ ቀን አዩት። በእርግጥ አውቶብስ ተራ ሌሊቱም ቀን ስለሆነ ብዙም አልተቸገሩም። ሆኖም ከአንድ ቀን በላይ ግን በዚያ አልቆዩም። በአንድ ቀን አዳር ቅጽበት ብዙ ተምረዋል። ስለዚህም አንድ ውሳኔ ላይ ደረሱ። ይህም ወደ ደላላ ቤት ሄዶ ሰው ቤት ተቀጥሮ ሕይወትን መግፋት። ደላላው ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ገንዘቡ ነውና ታስተምርሻለች በሚል ሰላምን ለአንዷ የመሸታ ቤት ባለቤት አስረከባት። ጓደኞቿንም እንዲሁ ለመጣው ሰጥቷቸው ተበታተኑ። በወቅቱ ስልክ አልነበራቸውም። ሁሉም መማር ነውና አላማቸው እንደቀያቸው ሰው ሰው ሁሉ ቃሉን አክባሪ ነው በሚል ደላላው ወደ መራቸው ቤት ነጎዱ።

እንደአጋጣሚ ሆኖ የሰላም አሰሪ መጥፎ የሚባል ባህሪ ያላት ናት። ሰው ጤፉ የሚሏት አይነት ናት። በረባ ባልረባው መነታረክና ባስ ሲልም መደባደብ የምታዘወትር ሴት ናት። ከዚሁ ባህሪዋ የተነሳ አስተምርሻለሁ ያለቻትን ሁሉ ትታ መሸታ ቤቷን እንድታሟሙቅ ፈረደችባት። በእርግጥ ለወር ያህል ስትሰራ ምንም አልመሰላትም። ሥራ እንደሆነ ብቻ ነው የተሰማት። በዚህም የታዘዘችውን ማድረጓን ቀጠለች። ሁኔታው እያደር ነው ያማረራት። ጉንተላውና ያም ለኔ ያም ለኔ ማለቱ አሰቃያት፤ አሳቀቃትም።

ለሰላም ከዚያም የባሰባት ግን የባለቤቷ ድብደባ ነበር። እርሷን ያስገባቻት ለአሻሻጭነት በመሆኑ የምትፈልገውን ልትከውንላት አልቻለችምና በአገኘችው እቃ ሁሉ አናቷን ለማለት ትጋበዛለች። ከወንዶች ጋር እንድታድር ትገፋፋታለች። አንድ ቀንም እንደምትገላት ታስባለች። ስለሆነም በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደማትችል ስታውቅ ከዚያ መውጣቱ አማራጭ እንደሆነ ታያት። ማቄን ጨርቄን ሳትልም ደሞዝዋን እንኳን ሳትቀበል ነበር ከቤቱ ትታ የጠፋችው። ግን የት እንደምትሄድ እንኳን አታውቅም። ማረፊያና ጊዜ ማሳለፊያ የሚሆናት ሰውም የላትም። አብራቸው ከሀገሯ የተሰደዱት ጓደኞቿ እንኳን ዛሬ ከአጠገቧ የሉም። እናም ብቻዋን ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ የተጋባችበት ጊዜ ነበር።

እግሯ ያደረሳት ቦታ ድረስ ስትጓዝ ያደረችው ሰላም ሊነጋጋ ሲል ጨርቆስ አካባቢ ወደአለ አንድ ድለላ ቤት ገባች። ለመኖር መስራት ግድ እንደሆነ ታውቃለችና መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎቿን አስቀድማ ሰው እንዲያገናኛት ጠየቀችው። በዚህ ውስጥ ግን ከሀገር ቤት የተሰደደችበት የትምህርት ጉዳይ የመጀመሪያው መሰረታዊ ነገሯ ሆኖ ቀርቧል። ምክንያቷ ደግሞ አንድ ነገር ነው፤ ይህንን እድል የሚሰጥ ሰው አዋቂና



ሰላም እንዳየሁ

መልካም ሰው ነው የሚል እምነት አላት። እናም ያለፈው አይነት ስቃይና መከራ እንዳያጋጥማት ወደ ፈጣሪዋ በመጸለይ ጭምር ለደላላውም አደራ አለችው። ደላላውም በሀሳቧ ተስማማና አንዲት ሴት ስትመጣ አስተዋወቃት።

ስትታይ መልካም ትመስል ነበርና ሰላም እንዳለፈው እንዳይገጥማት እየጸለየች ነበር ወደ ሁለተኛዋ አሰሪ ቤት የሄደችው። ግን ደላላውም ሆነ ሴትየዋ እንደዋሿት ገና የሴትዮዋ ቤት እንደደረሱ ነበር ያረጋገጠችው። በፈጣን ምላሳቸው እንዳታለሏትም ተገነዘበች። ግን ደግሞ ከዚህ ብትወጣ የት ልትደርስ ትችላለች። ስለዚህም ልሞክረው በሚል ሁለተኛውን የስቃይ ቤቷን ጀመረች።

‹‹እኔ የማሰራሽ ሥራ በአንድ ጊዜ የሚለውጥሽን ስራ ነው›› ስትላት ምን ለማለት እንደፈለገች አልገባትም ነበር። ሴተኛ አዳሪዎች ከሞሉበት ቤት ከስር ከስር እያለች ስራዋን ቀጠለች። ወጣ ያሉ ተግባራትን ስታይ ጭምር ትሳቀቃለች። በተለይም ቤቱን የሞሉት ሴቶች አለባበስና አኳኋል እጅጉን ያስገርማል። ሆኖም በእነርሱ አካል ምን አገባኝ እያለች ሥራዋ ላይ ታተኩራለች።

አንድ ቀን ግን ይህ ከፉ አጋጣሚ ወደ እርሷም መጣ። አሰሪዋ ዛሬ ለየት ያለ ሰው ስለምታገኚ መዋብ አለብሽ አለቻት። ለምን የሚል ጥያቄዋን እንኳን አልመለሰችላትም። እየጎተተች ወደ መኝታ ቤቷ አስገብታ አይታቸው በማታውቀው መዋቢያዎች አሽቀረቀረቻት። አጭር ቀሚስ እንድትለብስም ታዘዘች። አጭር ቀሚስ በሌሎቹ ላይ ስታየው እንኳን ያስጠላታል፤ ያሸማቅቃታልም። ግን ምርጫ አልነበራትምና ብዙ ታግላ ተሸነፈች።

ቀጣሪዋ ከፍተኛ ገቢ እንደምታመጣላት ታውቃለችና ገና ከገባች ጀምሮ ነበር ስትንከባከባት የቆየችው። ‹‹ ድንግል›› የሚፈልግና ከፍተኛ ገንዘብ የሚሰጣትን ሰውም ስታማርጥ ወራትን አሳልፋለች። በስተመጨረሻ ዋጋው ተተመነና ልጅቷ ቀረበች። ሰላም አብሯት ከሚያድረው ሰው ጋር ስትገናኝ ነበር ጉዷን የተረዳችው። ሰውዬው በአለባበሱ በጣም የሚያምር ነበር። ምንም የማይጎድለው አይነት ሰው ነው። ለሰላም ግን ምንም አልተመቻትም። እየደባበሰ ሲያሰቅቃትና ውስጧ አልታዘዝ ሲላት ትታው ለመውጣት ተገደደች። ሆኖም ብዙ ርቃ መሄድ አልቻለችም። ምክንያቱም መሽቷል። ሰካራም በበዛበት አካባቢ ላይ የብዙዎች መጫወቻ መሆኗ አይቀርም። ስለዚህም ይህ ከመሆኑ በፊት መመለስና ከአንዱ ጋር ማደር እንደሚሻላት አመነች፤ አደረገችውም።

ሴትዬዋ ከተስማማችው ሰው ጋርም አደረች። አዳሯ ግን ስቃይ የበዛበት ነበር። ሆኖም ብዙውን ገንዘብ የወሰደችው ቀጣሪዋ በመሆኗም ተንከባክባት ነበርና ነገሮችን እያደር አስረሳት። እርሷም ብትሆን ያገኘችው ገንዘብ ብዙ ነበርና ብዙም አልተከፋችበትም። ዓመታትንም በዚህ አይነት ሁኔታ ቀጠለች። ነገር ግን የሚጠራቀም ቀርቶ በልቶ ለማደር የሚበቃ ገንዘብ አላገኘችም። ምክንያቱም ተፈላጊነቷ ትናንት አበቃ። ዛሬ ዋና ተግባሯ እንደሌሎቹ ሴተኛ አዳሪዎች መንገድ ላይ ቆሞ ወንድ መፈለግ ነው።

ሰላም አሁን ከቀጣሪዋ ውጭ ብትሆንም የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት መርታል። በተለይም አሁን እየሰራችበት ያለው መንደር ብዙ ገበያ የለውም። እናም ቦታ ለመቀየር ወሰነች። ከሳሪስ ሰፈር ወጥታም በሀዲድ ሰፈር መኖሪያዋን አደረገች። ኑሮው በዚህ አይነት ሥራ መቼም የሚገፋ እንዳልሆነ ስትረዳም ሌላ ሥራ ለመጨመር አሰበች። ይህም እንደልማዷ መሸታ ቤት መቀጠር ነው። ከመሸታ ቤት ሺያጭነቷ በተጨማሪም ሴተኛ አዳሪነቱን ትተዳደርበት ጀመር።

ሀዲድ ሰፈር ለሰላም ተጨማሪ ፈተናን ያመጣባት ነው። ራሷን ማኖር ባልቻለችበት ሁኔታ ላይ ሳለች ሌላ ተጨማሪ ነፍስ መጣባት። የመጀመሪያ ልጇን አረገዘች። ነገሩ የተከሰተው በአጋጣሚ ነበር። አውቃው ቢሆን ኖሮ ልጁን አትወልደውም፤ እንዳረገዘች የተረዳችው ወራት ተቆጥረው የተለየ ሕመም ተሰምቷት ለህክምና በሄደችበት ወቅት ነው።

በዚህ ኑሮ ላይ ልጅ ተጨምሮ ሕይወት የበለጠ አስከፊ እንደሚሆን ከወዲሁ ገባት። ሌላው በህክምና ክትትል ወቅት የተረዳችው መርዶ ደግሞ በደሟ ውስጥ የኤች አይ ቪ ቫይረስ የመኖሩ ጉዳይ ነው።

በጊዜው የኤች አይ ቪ ምርመራ ቀድሞ ማድረግ አይታወቅም። ወይንም ደግሞ ከቫይረሱ ነጻ የሆነ ጽንስ እንዴት መገላገል እንደሚቻል በቂ ግንዛቤ አልነበረም። ስለዚህም ከቫይረሱ እንዴት ነጻ አድርጋ እንደምትገላገለው ያሳስባት ገባ። የሕክምና ባለሙያዎች በተቻላቸው መጠን ደግፈዋት ነበር። ሆኖም አልተሳካም፤ እርሷም ልጇም በቫይረሱ ተይዘዋል። ስለዚህም ለሁለቱም ብዙ ነገር ያስፈልጋቸዋል። ማንም በሌለበት ይህንን ማድረግ ደግሞ መቼም አይታሰብም።

ከብቸኝነት ጋር ድህነትና በሽታ ሲታከልበት ሕይወት መራር ይሆናል። አርግዞ በሰላም መገላገልና መታረስ ለሰላም የቅንጦት ያህል ነው። በዚህም መታረስ እንኳን ሳያምራት ቀጥታ ወደ ሥራ ገባች። ሆኖም ህጻን ይዞ ባልጠነከረ ሰውነት ሴተኛ አዳሪ ሆኖ መቀጠል አዳጋች መሆኑንም ስለገባት ሰላም ሌላ ስራ መፈለግ ጀመረች። መነሻዋን የቀን ሥራም አደረገች። በየሰው ቤት እየዞረች አሻሮ ትቆላለች፤ ልብስ ታጥባለች በአጠቃላይ የተገኘውን ስራ ሳታማርጥ ትሰራለች።

የአካባቢው አስተዳደርም በሴፍትኔት ተደራጅታ እንድትሰራ ዕውድን አመቻቸላት። በዚህ ስራ ለአምስት አመታት ቀጠለች። ጥሩ ገንዘብም ቋጠረች። ከአምስት አመታት በኋላም በቋጠረችው ብር ለንግድ የሚሆን ቤት ተከራይታ የሻይና ቡና ሥራን ጀመረች። አሁንም በዋናነት መተዳደሪያዋ ይህ ሥራ ነው። ሆኖም አንድ አስከፊ አጋጣሚ ተከሰተ። ለችግር የፈጠራት ይህቺ ሴት አንዲት ልጇን በሞት አጣች።

ሰላም ልጇን በሞት ካጣች በኋላ መረጋጋት አልቻለችም። በዚህም አዕምሮዋን ለማሳረፍ በሚል ራሷን በሥራ ትወጥር ነበር። በሞት ያጣቻትን አንዲት ልጇን እያሰበች በሃሳብ ትብሰለሰል ገባች። ይህ ደግሞ ከኤች አይቪ ኤድሱ በተጨማሪ ለሌሎች በሽታዎችም ተጋላጭ እንድትሆን አደረጋት።

ለሰላም ፈተና የሆነው ጉዳይ በሽታዋ ብቻ አይደለም፤ የቤት ጉዳይም ነው። በሀዲድ አካባቢ የአልጋ ኪራይ ጉዳይ የተለመደ ነው። በዚህም እርሷ የአከራይ ተከራይ ሆና ነው የምትኖረው። ከአከራይዋ በኮምፖልሳቶ የተከፈለች አነስተኛ ክፍል ተከራይታ እሷ መልሳ በማከራየት ነው ሕይወቷን የምትገፋው።

የአከራይ ተከራይ ሕይወት በርካታ ፈተናዎች የተጋረጡበት ነው። ሰላምም በብዙ የተፈተነችበት ቤት ነው። ቤቷን ዘግታ ማደር አትችልም። በየቀኑ የሚያድሩትን ሰዎች ገንዘቡን ሰብስባ ማስረከብ ግዴታዋ ነው። የሚከራዩት ሰዎች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ሰካራምና በአሽሽ የደነዘዙ በመሆናቸው በጊዜ አይገቡም። እስከ ሰባት ሰዓት እነርሱን ትጠብቃለች። በዚህም መድኃኒቷን ወስዳ በጊዜ መተኛት አትችልም። ከፍዬሻለሁ ብሎ የማይሰጣትም ብዙ ነው። ይህንን ደግሞ የመክፈሉ ግዴታ የእርሷ ይሆናል። ይባስ ብሎ ሰክሮ የመጣ ሰው ይደበድባታል። ግን ቀን እስኪያልፍ ያለፋልና ይህንን ታግሳ እየኖረች ትገኛለች።

የቤቱ ባለቤትም ቢሆን ሌላኛው ፈተናዋ ነው። ሰካራም ነው፤ ስድቡና የዘወትር ውጪልኝ ጥያቄው ያሰጋታል። ምክንያቱም ሰፈሩ ሴተኛ አዳሪ የሞላበት አካባቢ በመሆኑ በቀን ኪራይ 200 ብር ያገኝበታል። ስለዚህም ቤቱን ልቀቂ በሚል ያንገበግባታል። ከሁሉም የሚብሰው ደግሞ ለፍታ ያመጣችውን ገንዘብ ሙሉ ባይከራይም የሙሉ አልጋ ዋጋ ይቀበላታል። ግን ቦታውን ብዙዎች የለመዱት በመሆኑ ከዚያ ለመራቅ አልፈለገችም። በሻይ ቡናው የምታገኘውን ገንዘብ ማጣትም አትሻም።

በአጠቃላይ ከገጠር የጀመረው የሰላም የሕይወት ውጣ ውረድ ቂርቆስ ድልድይ አካባቢም ቀጥሏል። ሆኖም እጅ ላለመስጠት ዛሬም እየታገለች ትገኛለች። ለዚህ ሁሉ እፎይታ የሚሆናት አንድ ነገር እንደሆነ ታስባለች። ይህም መንግስት ቤት ቢሰጣት ነው። ስለዚህ ‹‹ለእንቅልፌና ለህመሜ›› መከታ ሁኑኝ ስትል ትጠይቃለች። አዎ እነዚህ አይነት ሰዎች አጋዥን ይፈልጋሉ፤ ብዙ እጅ ዘርጊዎች ደግሞ አይጠፉምና ድረሱላቸው በማለት ለዛሬ የያዝነውን አበቃን። ሰላም!!

# ስፖርት



## በአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች የቴክኒክ ጉዳይ ዛሬም አልተቀረፈም

ብርሃን ፈይሳ

በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ለአምስት ቀናት የሚካሄደው የኢትዮጵያ ክለቦች አጭር፣ መካከለኛ፣ 3ሺ ሜትር መሰናክል፣ እርምጃ እና የሜዳ ተግባራት ቻምፒዮና ነገ ይጠናቀቃል። ይህ ዓመታዊ ውድድር የሚካሄደው ኢትዮጵያ እምብዛም በማትታወቅበት የአትሌቲክስ ውድድሮች የተሻለ መነቃቃት እንዲፈጠር ቢሆንም አሁንም ተስፋ የሚሰጥ ውጤት እየታየበት አይገኝም።

በረጅም ርቀት አትሌቲክስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስኬታማ ከሆኑ አገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ ለአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች የሚሆን የተፈጥሮ ጸጋ ቢኖራትም ውጤታማ ልትሆን አልቻለችም። አገር ውስጥ በሚካሄዱ መሰል ውድድሮች በተደጋጋሚ መገንዘብ እንደተቻለውም አትሌቶች በእነዚህ ስፖርቶች ከሌሎች ዓለማት ጋር መነጻጸር ከማይችሉበት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ነው። አትሌቶቹ ላይ ከብቃት ማነስ ባለፈ ጎልተው ከሚታዩት ችግሮች አንዱ ከህግ ጋር የተያያዙ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ናቸው። በነዚህ ውድድሮች ብዙ አትሌቶች ባለማወቅም ሆነ ባለመጠንቀቅ በውድድር ወቅት በሚፈጽሟቸው የቴክኒክ ስህተቶች ምክንያት ከተወዳዳሪነት ሲሰረዙ በተደጋጋሚ ታይቷል።

ከቀናት በፊት በተጀመረውና ነገ በሚጠናቀቀው ቻምፒዮናም በአንድ ውድድር ብቻ እስከ ሁለት የሚደርሱ አትሌቶች ከቴክኒክ ጋር በተያያዘ ከውድድር ውጪ ሲሆኑ ታይቷል። ይህ ሁኔታ ከአገር ውስጥ ውድድሮች ባለፈ በዓለም አቀፍ ቻምፒዮናዎችም ሊደገምና አገርን ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የስልጠና ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር



በአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች የሚስተዋሉ የቴክኒክ ችግሮች አሁንም አልተቀረፉም፣

አቶ ሳሙኤል ብርሃኑ፤ በዚህ ቻምፒዮና የቴክኒክ ጉዳዮች ኃላፊ በመሆን እየሰሩ ይገኛሉ። ውድድሩን እንደገመገሙት ከሆነም ከወትሮ የተለየ ነገር ያልታየበትና ቴክኒካዊ ችግሮችም በስፋት የሚታዩበት መሆኑን ያስረዳሉ። ለዚህም አትሌቶች በስልጠና ወቅት ከሚያገኙት ቴክኒካዊ ስልጠና ባለፈ ከዳኝነት ህጉ ጋር ያለውን ነገር አለማወቅ ዋነኛው ምክንያት መሆኑን ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ሳሙኤል ገለፃ፣ አንድ አትሌት ዓመቱን ሙሉ ስልጠና ላይ ቆይቶ በብቃት ዳብሮ ውድድር ላይ ቢገኝም፤ ከአነሳስ ጋር በተያያዘ በሚፈጽመው ስህተት ከውድድር ውጪ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ ከአጭር ርቀት ሩጫዎች ባለፈ በውርወራም ሆነ ዝላይ ስፖርቶችም በብዛት የሚከሰት ነው። በመሆኑም መሰረታዊ የሆነውን ቴክኒካዊ ጉዳይ አሰልጣኞች ከሚያገኙት የአሰልጣኝነት ስልጠና ጎን ለጎን ከዳኝነት ጋር የተያያዘ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማድረግን ይጠይቃል። ይህም ሲሆን አትሌቱ ህጉን ተከትሎ በጥንቃቄ ውድድሩን ሊከውን ይችላል። ፌዴሬሽኑ በዚህ ረገድ ቻምፒዮናዎች ሲካሄዱ በጥቂቱ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ጥረት ቢያደርግም፤ እንደ አጠቃላይ ከህግ ጋር ተያይዞ ያለው ነገር የተረሳ ሊባል የሚችል መሆኑን አቶ ሳሙኤል ያስገነዝባሉ።

ባደጉት አገራት አትሌቱን ከማብቃት እኩል ከህግ ጋር ተያይዞ ያሉ ጉዳዮች ላይ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይደረጋል። በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ በመሆኑ ከዚህ ቀደም በተሳተፉባቸው ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሳይቀር ከውድድር ውጪ የሆኑበት አጋጣሚ እንደነበረ የቴክኒክ ኃላፊው ያስታውሳሉ። ክለቦች ከችግሩ ጋር በተያያዘ የአሰልጣኞችን ብቃት፣ ዓመቱን ሙሉ ውድድሮች አለመኖራቸውን እንዲሁም ለእነዚህ ስፖርቶች የሚሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና ቁሳቁስ በተገቢው ሁኔታ አለመሟላትን እንደ ችግር ያነሳሉ። ነገር ግን ዘመናዊ ስልጠና አቅማቸውን ባሳደጉ አሰልጣኞች እንዲሁም በተሟላ ቁሳቁስ እየሰለጠኑ ባሉ አካዳሚዎችና የስልጠና ማዕከላት ያለው ሁኔታም ከዚህ የራቀ አለመሆኑን ዳይሬክተሩ ይጠቁማሉ።

እንደ ፌዴሬሽን ያልተሰራበትን ይህንን ዘርፍ ባለፈው ዓመት ከተካሄደው ቻምፒዮና የጀመረ ሲሆን፤ አሰልጣኞችን በማስገንዘብ አትሌቶቻቸውን እንዲቀርጹ ለማድረግ እየተሞከረ ነው። መሰረታዊ የሆነውና የዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆነውም የአሰልጣኞች ስልጠና ላይ ከዳኝነትና ከህግ ጋር ዕውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ አሰልጣኞች በራሳቸው ጥረት ዕውቀታቸውን ማሳደግ እንደሚገባቸውም ዳይሬክተሩ ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ስፖርቱን ከህጻናት አለመጀመር ለችግሩ አንድ መንስኤ ሊሆን ይችላል፤ ይኸውም ቴክኒካዊ ጉዳዮችን ይበልጥ ለመረዳት በታዳጊነት እድሜ ላይ መስራት የተሻለ በመሆኑ ነው።

እንደ አጠቃላይ ኢትዮጵያ በአጭር ርቀት፣ ዝላይና ውርወራ ያለባትን ክፍተት ለመሙላት በአፍሪካ ደረጃ የተሻለ ልምድ ካላቸው አገራት (ናይጄሪያ፣ ኡጋንዳ፣...) ተሞክሮ ለመቅሰም በፌዴሬሽን ደረጃ ጅማሬዎች አሉ። ከዚህ ባሻገር ከልምድ አሰራር ባለፈ ዘመናዊ የሆኑ መሳሪያዎችን ለመጠቀምም እንዲሁም ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ባለሙያዎቹ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል። በመሆኑም በእነሱ በኩል ዝግጁ ሲሆኑ የልምድ ልውውጡ የሚከናወን መሆኑንም ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት እነ ወ/ሮ ፈቲያ መሀመድ እና በፍ/ባለዕዳ እነ አቶ ሲጎ ሙዘይን መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 199840 በ5/3/2011 ዓ.ም እና በመ/ቁ 04772 19/10/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤ.ቁ 710 በሆነው ቤት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር ካ/ቁ AA00040201256 በወ/ሮ ፈቲያ መሀመድ ስም የተመዘገበ የይዞታ ስፋት 215 ካ.ሜ የሆነ ቤት ባለ 3 ወለል ጅምር ህንፃ ያለበት ሆኖ ቤቱ የቤት አገልግሎት ለአገልግሎት ለድርጅት እና ለመኖሪያ ቤት መሆኑ ታውቆ ካፒታል ጌን ከሽያጭ የሚቀነስ ሆኖ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 5,153,646 (አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ስድስት ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል፣ ካፒታል ጌን ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

## የምስክር ወረቀት መጥፋት ማስታወቂያ

አሸናፊ ፍቃዱ የተሰኙ የማህበሩ ስራ ስራ አስኪያጅ በቀን 15/07/2015 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የምዝገባ ቁጥር፡ BO/CAE -V/99 የሆነ ኤ.ኤስ.ኢ.ኤሰ አማካሪ አርክቴክቶች እና መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በደረጃ 5 የተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ የጠፋባቸው መሆኑን ገልፀው ተለዋጭ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በጥያቄያቸው መሰረት ከማህደራቸው BO/CAE -V/99 የሆነ የብቃት ማረጋገጫ ኤ.ኤስ.ኢ.ኤሰ አማካሪ አርክቴክቶች እና መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በደረጃ 5 ከመስሪያ ቤታችን የተሰጣቸው መሆኑን እያረጋገጥን በዕዳ ይገፍዋለሁ የሚል ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን መረጃና ዶክመቴሽን አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ድረስ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እየገለጽን በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ባይቀርቡ ተለዋጭ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአ/አ/አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን**

## ሶማሊ ክልል

ንብረትነቱ በታምራት ረጋሳ ተስፋዬ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር 01-02956 ሱማ የተሽከርካሪው አይነት ባጃጅ የሻንሲ ቁጥር MD2A25BZ6EWL83089 የሞተር ቁጥር AZZWEL-50892 የሊብሬ ቁጥር 0668 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ የፊት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ10/5/2015 ዓ.ም አመልክተዋል ፡፡ የፊት ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገፍዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የሶ/ክ/መንግስት ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ኢ/ቴ/ኮ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-11857 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JTFEG42680-005672 ሞዴል RZN147LPRMDS የሞተር ቁጥር 1R2-3347814 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ5/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም የኢትዮጵያ ቴሌኮሚንኬሽን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-25337 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር ADNCPUD22Z0054518 ሞዴል CVLULCFD22UANK-F-VH የሞተር ቁጥር YD25635876T የሊብሬ ቁጥር 0183252 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ5/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅ/ጽ/ቤት**